Green

መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቶች ቀን

በአዋሳ

የፓነል ውይይት ሰነድ

ታህሣሥ 5 - 7 ቀን፣ 1994 ዓ.ም

አዋሳ

CCRDA

አዘጋጆች:-

የክርስቲያን በጎ አድራጐትና የልማት ድርጅት

አክሽን ኤድ ኢትዮጵያ

ፓክት ኢትዮጵያ

አየርላንድ ኤድ

የኔዘርላንድ የልማት ድርጅት /ኤስ.ኤን.ቪ/

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ

1. የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት 1

2. የፓነል ውይይቶች 21

2.1 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል በሚያካሂዷቸው የልማት ሥራዎች ያጋጠሙ አመቺ ዕድሎችና ተፈታታኝ ችግሮች 22

2.1.1 በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል ያለ ግንኙነት፣ ዋና ዋና ችግሮችና በቀጣይ የታሰቡ ምቹ ሁኔታዎች 23

2.1.2 የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ፣ በተለይ ደግሞ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል የምታካሂደው የእርዳታና የልማት ሥራ 27

2.1.3 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ድህነትን ለማቃለል ያላቸው ሚና 29

2.1.4 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በደቡብ ክልል ልማት ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ 34

2.1.5 አጠቃላይ ውይይት 39

2.2 የድህነት ቅነሳ ሰነድና ድህነትን መቋቋም 49

2.2.1 የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል 53

2.2.2 የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚኖረው ጠቀሜታና ሚና 57

2.2.3 የሲቪሉ ማህበረሰብ በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት የሚኖረው የተሳትፎ ዕንሰ ሃሳብ 60

2.2.4 አጠቃላይ ውይይት 65

2.3 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደርና በሰላም ግንባታ ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ 72

2.3.1 መያዶች ለዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ ያላቸው ሚናና አስተዋፅ 72

2.3.2 ሰላምን በማስፈንና በማዳበር ረገድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚና 78

2.3.3 የሰብአዊ መብት ትምህርትን ለማስፋፋትና ሕግጋቱን ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ያላቸው ሚና፣ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦና የሚያጋጥሟቸው ችግሮች 80

2.3.4 አጠቃላይ ውይይት 84

CCRDA

መግቢያ

በኢትዮጵያ፣ ለሁለተኛ ጊዜ፣ በክልል ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው፣ «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንሜ ከታህሣሥ 5 እስከ 7 1994 ዓ.ም. አዋሳ ውስጥ ተካሂዷል::

የዚህ መድረክ መፈጠር፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ በሕብረተሰቡ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ውስጥ ስላላቸው ሚናና ስለሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የሚመለከታቸው ወገኖችን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ፣ የውይይት ባህልን ለማሳደግና ከመንግሥት፣ ከለጋሾችና በልማት ሥራ ተሳታፊዎች ከሆኑ ወገኖች ጋር የልማት አጋርነትን ለማጠናከር ልዩ ዕድል አስገኝቷል::

«መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንሜ ዝግጅት ላይ የሚካሄዱ የፓነል ውይይቶችም ልዩነቶችን አንጥሮ በማውጣት ለማስወገድና የተሟላ ስምምነት ላይ ለመድረስ፣ እንዲሁም በየወቅቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማቃለል የሚያስችሉ ስልቶችን ለመንደፍ የሚረዱ ሆነው ታይተዋል::

በዚህ ዓመት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች፣ ክልል ዋና ከተማ አዋሳ ውስጥ በተካሄደው «መንግሥታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች ቀንሜ በተደረጉት የፓነል ውይይቶች ላይ አንድ ዋነኛ ርዕስ ሆኖ የቀረበው፣ የድህነት ቅነሳን ስልት የሰነድ ዝግጅት ሂደትን የሚመለከት ነበር:: ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሀገሮች የዕዳ ቅነሳ እንዲደረግላቸውና ለወደፊቱም ተጨማሪ የልማት ብድር ለማግኘት እንዲችሉ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነዱን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል:: በሰነድ ዝግጅቱ፣ የሲቪሉን ማህበረሰብ ማሳተፍ አንዱ አስፈላጊ ሁኔታ በመሆኑ፣ የልማት አጋሮች የሆኑት መያዶች በሰነድ ዝግጅቱ፣ በአፈጻጸሙ፣ እንዲሁም በክትትልና በግምገማው ሥራ ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ ዕድል እንዲሰጣቸው የፓነል ውይይቱ ተሳታፊዎች በአዕንኦት ጠይቀዋል::

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በሰብአዊ መብት ጥበቃ፣ እንዲሁም በሰላምና ዲሞክራሲ ግንባታ ንቁ ተሳትፎ ኖሯቸው፣ በአገራችን በኢትዮጵያ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የመልካም አስተዳደር ሥርዓትን ለማስፈን እንዲያግዙም አመቺ የሥራ ሁኔታ ይፈጠርላቸው ዘንድ፣ በበዓሉ ላይ ንግግር ያደረጉ የመያዶች ተወካዮች አሳስበዋል::

የመያዶች ቀን በየዓመቱ በተለያዩ ክልሎች የሚከበር ሲሆን፣ ዝግጅቱን በቅደም ተከተል ለማስተናገድ ፈቃደኝነቱን ለሚያሳይና ለመያዶች አመቺ የሥራ ሁኔታን ለሚፈጥር ክልል ቅድሚያ ይኖረዋል::

CCRDA

1. የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት

በኢትዮጵያ በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት የሕይወት ማዳን ተልዕኳቸውን በመወጣትና ድህነትን ለማስወገድ ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን፣ አሁንም «ድህነትን ማጥፋት ይቻላል፣ ቃል ኪዳናችንን እናድሳለንሜ በሚል መርህ ከታህሣሥ 5 እስከ 7 ቀን፣ 1994 ዓ.ም አዋሳ ውስጥ ተከብሯል::



በበዓሉ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ አቶ ፍቅሩ አበበ፣ የክርስቲያን ችልድረንስ ፈንድ ሐሲ.ሲ.ኤፍሐ ዳይሬክተርና ፕሮግራም መሪ ዝግጅቱን በሚመለከት አጠር ያለ ገለጻ አደረጉ:: ከዚያም አቶ ከበደ አሥራት የክርስቲያን በጎ አድራጉትና የልማት ድርጅት የሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር፣ በበዓሉ ላይ ለተገኙት እንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር እንዲያደርጉ ጋበዙ:: አቶ ከበደ አሥራትም የሚከተለውን ንግግር አደረጉ::

ክቡር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣
የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር ፕሬዚዳንት፣
የተከበራችሁ እንግዶች፣

ጥሪያችንን አክብራችሁ በዚህ ታላቅ በዓል ላይ በመገኘታችሁ እንኳን ደህና መጣችሁ እያልኩ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመወከልና በራሴም ስም ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ:: የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳደር፣ በኢትዮጵያ ለሁለተኛ ጊዜ የተዘጋጀውን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን በማስተናገድ ያሳየውን የአጋርነትና የትብብር መንፈስ በማድነቅ፣ ለዚህ አርአያነቱ ጥልቅ ምሥጋናዬን እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ::

CCRDA

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን በታህሣሥ ወር 1993 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ ውስጥ፣ በብሔራዊ ደረጃ መከበሩ ይታወሳል። የዚህ ዓይነቱ ዓመታዊ ዝግጅት የሚካሄድበት ዋና ዓላማ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ እንዲሁም በልማት ሥራ የሚሳተፉ ወገኖችና ሕዝቡ በቅርብ ተገናኝተው የሚወያዩበትና የጋራ ሃሳብ የሚለዋወጡበት መድረክ ለመፍጠር ነው።

አዲስ አበባ ውስጥ የተካሄደውን የመጀመሪያውን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን የኤግዚቢሽን ዝግጅት፣ ከ25000 ሺህ የሚበልጥ ሕዝብ ተመልከቶታል። ተመልካቹም፣ ልጅ፣ አዋቂ፣ ሴት፣ ወንድ፣ ሳይል ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ያካተተ ነበር። በዚያ ወቅት ኤግዚቢሽኑን ከተመለከቱትና በተለያዩ የውይይት ፎረሞች ከተሳተፉት እንግዶች የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተው ነበር። ከእነዚህ ጠቃሚ አስተያየቶች አንዱ፣ «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንሚ በክልል ደረጃ በማዘጋጀት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግበረሰናይ ድርጅቶች በየተሠማሩባቸው ክልሎች ከሚገኙት የማህበረሰብ አባላት ጋር ሃሳብ ለሃሳብ ቢለዋወጡ፣ ሥራቸው ሁሉ የተሻለ ውጤታማ እንደሚሆን የሚያሳስብ ነበር።

በዚህም መሠረት፣ በዚህ በአዋሳ የተዘጋጀው "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" ዋና ዓላማ፣ በክልሉ ውስጥ በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች እንደ አንድ አጋዥ ክንድ የሆኑት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተሰማሩባቸውን የአርዳታ፣ የመልሶ ማቋቋምና የልማት ሥራዎች ዓይነት፣ የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸውን፣ እንዲሁም ጥንካሬና ድክመቶቻቸውን በግልጽ በማሳየት፣ ድክመቶቻቸውን ለማስወገድና ጥንካሬያቸውን ይበልጥ ለማጐልበት የሚያስችሉ ውይይቶችንና ምክክሮችን ለማካሄድ ነው።

እዚህ አዋሳ ውስጥ ለሦስት ቀናት የሚካሄደው የመያደች ቀን፣ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግብረጠሰናይ ድርጅቶች፣ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል ልማት ያላቸው ሚናና አስተዋዕኦ" በሚል መርህ ይከበራል። ይህ መርህ የወጣው "የአንድ ሀገር ልማትና በዚህም ሳቢያ የሚመጣው የሕዝቡ የኑሮ መሻሻል በአንድ ብቸኛ አካል ጥረትና ድካም ብቻ የሚሳካ አይሆንም፤ ልማት የዜጐችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ የጋራ ጥረት ውጤት ነው" ከሚለውና በስፋት ተቀባይነት ካለው አስተሳሰብ በመነሳት ነው።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድህነትን ለመቀነስ የሚካሄደውን ሀገራዊ ጥረት ያግዛሉ። መንግሥታዊ የአገልግሎት ተቋማት በማይደርሱባቸው አካባቢዎችም የህገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች በማራመድ ረገድ ወሳኝ አስተዋዕኦ ያበረክታሉ። እንደ

CCRDA

ለደድ አሳት ፎተቀጣጠለውንና በሀገሪቱ የሰው ኃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማስከተል ላይ የሚገኘውን የኤድስ ወረርሽኝ ለመግታት በሚደረገው ጥረትም፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወሳኝ ድርሻ በማበርከት ላይ ይገኛሉ። ወደፊትም በሁለም የልማት ዘርፎች ድርሻቸውን ለመወጣት የበለጠ ይሠራሉ።



እንደ ኢትዮጵያ ላይሆን፣ በሌሎች አዳጊ ሀገሮች ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መንግሥታዊ ድርጅቶች አሉ። በመያዶቹና በሚንቀሳቀሱባቸው ሀገሮች መንግሥታት መካከል ያለው ግንኙነትም በጋራ የመተማመን መንፈስ ላይ የተመሠረተ ነው። መያዶቹ በልማት ሥራ የሚያደርጉት አስተዋፅኦም በመንግሥታቱና በጠቅላላው ሕዝብ ዘንድ በስፋት ይታወቃል፣ ይደነቃልም።

በኢትዮጵያም ቢሆን፣ እርምጃው በተፈለገው መጠን ባይሆንም፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥቅምና በሀገሪቱ የልማት ሥራዎች የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ዕውቅና እያገኘ ነው። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት መሳተፋቸውና ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የቆየው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከት ሕግ ረቂቅ ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ደረጃ ላይ መገኘቱ፣ መያዶችን በሚመለከት በመንግሥት በኩል በመወሰድ ላይ ለሚገኙት አዎንታዊ እርምጃዎች ግልጽ ምልክቶች ናቸው።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚጫወቱት ወሳኝ ሚና የሚጠበቀውን ያህል ዕውቅና ያላገኘው፣ ስለአስተዋፅኦዎቸው በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ነው። ከዚህም በላይ፣ መረጃን ለመለዋወጥና የተሣቡ አመለካከቶችን ለማስወገድ የሚረዱ መድረኮች አለመኖር፣ እንዲሁም በመያዶች ዘርፍ ላይ በመከናወን ላይ ያሉ ሥራዎችን በቅርብ እየተከታተሉ ለማየት አለመቻል ሌላው የግንዛቤ እጥረት ያስከተለ ችግር ነው።

CCRDA

ይህም በመሆኑ «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንሚ ዋና ዓላማ፣ መያዶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ የማሕበራዊና የኤኮኖሚ ልማት ያላቸውን ሚናና የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ በሚመለከት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖችን ግንዛቤ ለማሳደግና ሕዝባዊ ውይይቶችንም ለማካሄድ ነው::

በክልል ደረጃ የመጀመሪያ የሆነውንና እዚህ አዋሳ ውስጥ የተዘጋጀውን የመያዶች ቀን በደመቀ ሁኔታ ለማካሄድ፣ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓቱን ጨምሮ በርካታ ተግባራት ይከናወናሉ:: በዚህም መሠረት፣ ከመክፈቻ ሥነ ሥርዓቱ ቀጥሎ፣ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል በሚያከናውኗቸው የልማት ሥራዎች ያጋጠሙ አመቺ ዕድሎችና ተፈታታኝ ችግሮች" "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ ያላቸው ሚናና አስተዋፅኦ" "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደርና በሰላም ግንባታ ያላቸው ሚናና አስተዋፅኦ" በተሰኙ ርዕሶች የፓነል ውይይቶች ይካሄዳሉ:: በዚህ በዓል ላይ የመያዶችን የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩ ፎቶግራፎች፣ የፕሮጀክት ሞዴሎች፣ የጥናትና ምርምር አትሞች፣ እንዲሁም ለገቢ ማስገኛ የተዘጋጁ የምርት ውጤቶች በኤግዚቢሽን መልክ ቀርበዋል::

እንደዚህ ያሉ መድረኮች፣ በሀገሪቱ የልማት ሥራዎች የሚሳተፉ ወገኖችን በአንድ ላይ ለማገናኘት እንደሚረዱ የመያዶች ዘርፍ ፅኑ እምነት ነው: ይህ ደግሞ፣ ድህነትን ለማቃለል የሚካሄደው የሚያቋርጥ ትግል የተፈለገውን ግብ እንዲመታ፣ አጋርነትን ለማጠናከር የሚያስችል መንገድ ይጠርጋል:: ከዚህ እምነት በመነሳት፣ የዚህ ዓይነቱ የመያዶች ቀን ክልሎችን በየተራ በማዳረስ የሚዘጋጅ ይሆናል:: የሚቀጥለው የመያዶች ቀን የሚዘጋጀው በዓሉን ለማስተናገድ በቅድሚያ ዝግጁነቱን በሚገልጸው ክልል ውስጥ ይሆናል::

የዚህ ዓይነቱን የመያዶች ቀን በዓል የማስተናገድ ዝግጁነትን ከሚያሳውቁት ወሳኝ ሁኔታዎች አንዱ፣ በክልሉ ውስጥ ለመያዶች የተፈጠረው አጠቃላይ አመቺ የሥራ ሁኔታ ይሆናል:: መቼም ለመያዶች የሥራ እንቅስቃሴ ያለው አመቺ ሁኔታ ከክልል ክልል እንደሚለያይ ሳይታለም የተፈታ ነው:: ይህም በመሆኑ፣ የመያዶች ቀን በየክልሎቹ በዙር እንዲዘጋጅ ማድረጉ፣ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ለመያዶች እንቅስቃሴ የሚፈጠረውን አመቺ የሥራ ሁኔታ ይበልጥ ለማሻሻል ይረዳል ብለን እናምናለን::

በዚህ "የመያዶች ቀን" የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኛችሁትን እንግዶች በድጋሚ እንኳን ደህና መጣችሁ እያልኩ፣ በዝግጅቱ ላይ ከቀረቡት ኤግዚቢሽኖችና በተከታታይ ከሚካሄዱት የፓነል ውይይቶች የዝግጅቱን ዓላማና መልዕክቶች በስፋት ለመገንዘብ

CCRDA

እንደምትችሉ እምነታችን መሆኑን እገልጻለሁ። የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝና ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ፣ ውድ የሥራ ጊዜያቸውን በመሰዋት ይህንን ታሪካዊ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" አከባበር ለመምራት መገኘታቸው፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበረሰብን ሞራል ከፍ የሚያደርግና መንግሥት ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት መስጠቱን በግልጽ የሚያሳይ ነው። ስለሆነም፣ ለሁለቱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የተለየ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። እንግዶቻችን በሙሉ ጥሪያችንን ተቀብላችሁ እዚህ በመገኘት ላሳያችሁን አክብሮት ልባዊ ምሥጋናዬን በድጋሚ አቀርባለሁ። በመጨረሻም፣ በአዋሳ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" ዝግጅት የተሳካ እንዲሆን ሳይታክቱ በመሥራት አስተዋፅኦ ያደረጉትን፣ የበዓሉ አዘጋጅ የሆኑ መያዶችን፣ የፓነል አቅራቢዎችን፣ የዝግጅት ኮሚቴ አባላትንና የክርስቲያን በጎ አድራጉትና የልማት ድርጅት ሠራተኞችን አመሰግናለሁ።

የበዓሉ የፕሮግራም መሪ አቶ ፍቅሩ አበበ፣ አቶ ከበደ አሥራትን አመስግነው፣ ክቡር ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ ንግግር እንዲያደርጉ ጋበዙ። ከዚያም፣ ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ።

በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ውስጥ በእርዳታና የልማት ሥራ ላይ የተሠማሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግብረሠሰናይ ድርጅቶች የተካፈሉበትን ይህንን "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ለመምራት እዚህ በመገኘቴ፣ ታላቅ ደስታና ክብር ይሰማኛል።

በክልል ደረጃ በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንሜ ዝግጅት ስኬታማና ዕውን ያደረጋችሁትን መያዶችና የበዓሉን አዘጋጆች "እንኳን ደስ ያላችሁ" አላለሁ። "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" በክልል ደረጃ ማዘጋጀት፣ ተጨባጭና ፍሬያማ የሆኑ የልምድ ልውውጦችን ለማካሄድና ለማጠናከር ጉልህና ጠቃሚ አስተዋፅኦ ያበረክታል። ይህም ሚዛናዊ የሆነ ክልላዊ ልማትን ዕውን ለማድረግ ያስችላል። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ ይህ አዋሳ ውስጥ የተዘጋጀው የመያዶች ቀን "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ድርጅቶች በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል ልማት ያላቸው ሚናና አስተዋፅኦ" በሚል መርህ መከበሩ፣ አግባብነት ያለው መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም። የበዓሉ አዘጋጆች፣ በክልል ደረጃ የመጀመሪያውን "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል ለማካሄድ የተነሳሱት አሳማኝ ምክንያት ይዘው እንደሆነ ለማረጋገጥ እወዳለሁ። ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግብረሠሰናይ ድርጅቶች

GCPDA

በክልሉ ውስጥ ስለሚሠሩ ነው:: የመረጃ ሰነዶች እንደሚያመለክቱት፣ በክልሉ ውስጥ በሰብአዊ እርዳታዎችና በልማት ሥራዎች የተሰማሩ ከ80 የሚበልጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ::

ባለፈው ዓመት አዲስ አበባ ውስጥ በብሔራዊ ደረጃ የተካሄደውና ዛሬ ደግሞ አዋሳ በክልል ደረጃ የሚካሄደው "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" ከተዘጋጁበት ዋና ዓላማዎች አንዱ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ በሕብረተሰቡ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ውስጥ ስላላቸው ሚናና ስለሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የሚመለከታቸው ወገኖችን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ የውይይት መንፈስን ለማነቃቃትና ከመንግሥት፣ ከለጋሾችና በልማት ሥራ ተሳታፊዎች ከሆኑ ወገኖች ጋር የልማት አጋርነትን ለማጠናከር ነው::

በአሁኑ ጊዜ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መልዕክት ትክክለኛው ጆሮ ላይ መድረስ ጀምሯል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ:: የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት፣ መላው የሀገሪቱ ሕዝብ በተደራጀ መልክም ሆነ በተናጠል፣ ብሔራዊ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅትን አስመልክቶ ሃሳቡን የመግለጽ ወይም ሃሳብ የማቅረብ ሥልጣን እንዳለው በግልጽ አሳውቋል:: በዚህ ጉዳይ ላይ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚኖራቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ለዚህ አባባል መሠረታዊ መነሻው፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተቀዳሚ ራዕይ ድህነትን ማስወገድ የመሆኑ ዕውነታ ነው::


መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ብሔራዊ የአደጋ መከላከል ፈንድ የማቋቋሙን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱም እምነት ተጥሎባቸዋል:: ፈንዱ የሚቋቋምበት ዋና ዓላማ፣ በሀገሪቱ ላይ በተደጋጋሚ የሚደርሱት የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆኑ ለመከላከልና የሚያስከትሉትንም ጉዳት ለመቀነስ ነው::

የዚህ ዓይነቶቹ የሥራ ግንኙነቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመንግሥት ዘንድ እንደ አንድ የልማት አጋር ተደርገው ለመታየታቸው በግልጽ የሚያመለክቱ ናቸው::

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ጉዳዮች ላይ በነቃ ተሳትፎ አስተያየታቸውን የገለጹባቸውን ሌሎች ተመሳሳይ ምሳሌዎችንም መጥቀስ ይቻላል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በሁለተኛው አገር አቀፍ የምርጫ ሥነሥርዓት ላይ የተካሄዱ ክርክሮችን በታዛቢነት ደረጃ

CCRDA

ተከታትለዋል። የፌዴራል መንግሥት መደጎሚያ የሚመለከት ሕግ ለማውጣት ባካሄዳቸው ውይይቶች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ተደርገዋል። የሰብአዊ መብት ጥበቃ ኮሚሽንና የአንባ ጠባቂ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ዝግጅት ላይም ተሳትፈዋል።



መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህንን ዕውቅና ያተረፉት ከሕብረተሰቡ ጋር የልማት አጋሮች ሆነው በመሥራታቸው ነው። ዳሩ ግን፣ ይህ ራሱ ብቻውን በቂ እንዳይደለ በአፅንኦት ለመግለጽ እወዳለሁ። ከተጫኑን ችግሮች ክብደት አንፃር ማለትም፣ አስከፊ ድህነትና እጦት በሰፈነባት ሀገር፣ በተደጋጋሚ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች በምትጠቃ ሀገር፣ አስከፊ ጥፋት በማድረስ ላይ ያለው የኤች አይ ቪ ኤድስ የልማት ደንቃራ በሆነባት ሀገር፣ ይበልጥ ተባብረን የምንሠራቸው ገና ብዙ ሥራዎች ይጠብቁናል። የተጋረጡብን ፈተናዎች አስቸጋሪዎች ናቸው። ሆኖም ግን፣ መፍትሔ የማይገኝላቸው ችግሮች አይደሉም። እንዲሁ ሲታይ የማንወጣቸው ወይም የማይበገሩ ችግሮች ይመስላሉ። ዳሩ ግን በልማት አጋርነት መንፈስ እጅ ለእጅ ተያይዘንና ተባብረን ከሠራን፣ በቀላሉ ልንወጣቸው እንችላለን። ስለሆነም፣ እንደነዚህ ያሉ ዝግጅቶች፣ የጋራ ዓላማ ያላቸውንና ለጋራ ግብ የሚሠሩ ሰዎችን አንድ መድረክ ላይ በማገናኘትና ጠቃሚ ድርሻ ያበረክታሉ። እንደነዚህ ያሉ ዝግጅቶች፣ ልዩነቶችን አንጥሮ በማውጣት አማለጃነድና የተሟላ ስምምነት ላይ ለመድረስ፣ እንዲሁም በየወቅቱ የሚያጋጥሙ ችግሮችን አማቃለል የሚረዱ ስልቶችን ለመንደፍ የሚያስችሉ ሙይይቶችን ለማካሄድ የሚያገለግሉ መድረኮች ይሆናሉ።

CCRDA

ከበዓሉ አከባበር ፕሮግራም እንደተረዳሁት፣ ይህ ያሁኑ ሥነ ሥርዓት፣ ለሦስት ቀናት የሚካሄደው "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ነው። የበዓሉ ፕሮግራም፣ በስፋት ተወያይታችሁ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያስችሏችሁን የተለያዩ አርዕስተ ጉዳዮችንም ያካተተ ነው። ስለሆነም፣ በውይይቶቹ ወቅት የተሟላ ተሳትፎ እንደሚኖርና በአዘጋጆቹ የተተለሙት ዓላማዎች በተሟላ ሁኔታ እንደሚሳኩ እምነት አለኝ።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፣ መሥሪያ ቤቴ ከመያዶች ጋር የልማት አጋር ሆኖ ለመሥራት ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ አረጋግጥላችኋለሁ።

በመጨረሻም፣ የበዓሉ አዘጋጆች የሆኑትን፣ የክርስቲያን በጎ አድራጉትና የልማት ድርጅት፣ ፓክት ኢትዮጵያ፣ የኔዘርላንድ የልማት ድርጅት /ኤስ.ኤን.ቪ/፣ የአየርላንድ ኤድ እና አክሽን ኤድ ኢትዮጵያን ከልብ አመሰግናለሁ። እንደገናም፣ ለተዋጣለት ዝግጅታችሁ፣ ሁላችሁንም እንኳን ደስ ያላችሁ እላለሁ። አመሰግናለሁ።

በመክፈቻ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ሌላዋ ተናጋሪ ሲስተር ዘቢደር ዘውዴ ነበሩ። ሲስተር ዘቢደር፣ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ወክለው ያደረጉት ንግግር የሚከተለው ነው።

ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች
ክቡራትና ክቡራን

በዚህ አዋላ ውስጥ በሚከበረው "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" ላይ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ወክዬ ንግግር እንዳደርግ ስለተፈቀደልኝ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የበጎ ፈቃደኞች ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት መስጠት የጀመሩት ከ80 ዓመታት በፊት ነው። ድርጅቶቹ በአብዛኛው በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ፣ ልዩ ትኩረት የሚያደርጉትም በትምህርትና በጤና ዘርፍ ላይ ነበር።

ብዙዎች የበጎ ፈቃደኞች ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚል መታወቂያቸው ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት ገብተው መንቀሳቀስ የጀመሩት፣ የድርቅ አደጋ ተከስቶ በነበረበት ወቅት ነው። ይኸው ድርቁን ለመቋቋም የተጀመረው የመያዶች እንቅስቃሴ፣ ቀስ በቀስ ትኩረቱን ወደ መልሶ ማቋቋምና የልማት ሥራ ላይ አደረገ።

CCRDA

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከ360 በላይ የሚሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በገጠርና በከተማ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ::

እነዚሁ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በማህበራዊ አገልግሎት /ለጤና፣ በንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ በትምህርት ወዘተ./፣ በእርሻና በአነስተኛ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች፣ በአቅም ግንባታ፣ በኤች. አይ. ቪ ኤድስ፣ በሥነ ተዋልዶ፣ በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲሁም በሌሎች የልማት ዘርፎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች "የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ" በሚል እምነት የበኩላቸውን ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛሉ:: በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ 250 የሚጠጉ አገር በቀል መያዶችና 118 ዓለም ዓቀፍ መያዶች ይገኛሉ:: ይህ ደግሞ፣ በሌሎች ሀገሮች ውስጥ ከሚገኙት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛ ነው:: ለምሳሌ ያህል እንጥቀስ:ጠ በእንግሊዝ 500000፣ በአሜሪካ 600000፣ በአውስትራሊያ 12000፣ መያዶች አሉ:: በአዳጊ አገሮች ውስጥ ደግሞ፣ በሕንድ 300000፣ ደቡብ አፍሪካ 54000፣ ባንግላዲሽ 15000፣ በኬንያ 3000፣ ኡጋንዳ 1500፣ ዚምባብዌ 800 መያዶች አሉ:: በኢትዮጵያ ውስጥ ከቸግሩ አኳያ ስንመለከት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው:: ስለሆነም፣ መንግሥትና ሕብረተሰቡ ከፍተኛ ድጋፍ ሰጥተው የመያዶች ቁጥር እንዲጨምር ቢደረግ የልማት አጋሮችን ማብዛት ይቻላል::

ከክልሉ ፕላንና ኢኮኖሚ ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል የሚንቀሳቀሱት መያዶች በ1993 ዓ.ም ከ350 ሚሊዮን ብር በላይ ለድንገተኛ አደጋ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ሥራ አውለዋል:: ይህ በጀት መንግሥት ከመደበው አጠቃላይ በጀት ጋር ሲነፃፀር 26 በመቶ፣ እንዲሁም የካፒታል በጀቱን 45 በመቶ ይሸፍናል:: በዚሁ አንፃር በክልሉ ከፍተኛ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ሕብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጓል::

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአጠቃላይ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ የመንግሥት አስተዋፅኦና ድጋፍ እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን፣ ለወደፊቱም ይበልጥ በትንሽት የመሥራት ባህል የማዳበሩ ሁኔታ ደግሞ ከሕብረተሰቡ፣ ከመንግሥትና ከመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይጠበቃል:: በተለይም መንግሥት፣

- ግልጽ የሆኑ መመሪያዎችንና ደንቦችን ማውጣት፣
- የፕሮጀክት ስምምነት ውል ለመፈፀም የሚወስደው ጊዜ በአጭር ቀን እንዲፈጸም መመሪያ መስጠት፣

CCRDA

- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ድጋፍ ለማስጠት የሚያስችል አቅምን ማዳበር፣
- ዘላቂ ልማትን ለማስፈን ይቻል ዘንድ፣ ለመያዶች የልማት ገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎችን መፍቀድ ወዘተ. ይጠበቅበታል::

ሕብረተሰቡም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በልማት አጋርነት የመሥራትን ባህል ማዳበር የሚጠበቅበት ሲሆን፣ እኛም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበረሰብ አባላት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራርን ለማስፈን በቅንነትና በትጋት መሥራት ይኖርብናል:: ይህንን ዕውን ለማድረግ ደግሞ፣ ላወጣነው የሥነ ምግባር መመሪያ ተገዥ መሆን ይጠበቅብናል::

በመጨረሻም እኛ አገር በቀል መያዶች ለተቀናጀ አሠራር፣ ማለትም ከሕብረተሰቡና ከመንግሥት ጋር ለመሥራት ያለንን ተነሳሽነት እያረጋገጥን፣ በጋራና በቁርጠኝነት ለልማት እንድንነሳ ጥሪያችንን እናቀርባለን:: አመሰግናለሁ::

የሚቀጥሉት ተናጋሪ አቶ ፀጋዬ ቸርነት፣ የፓክት ኢትዮጵያ ተባባሪ ዳይሬክተር ነበሩ:: አቶ ፀጋዬ፣ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል የሚሠሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን ወክለው የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል::

በዚህ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኛችሁ የተከበራችሁ እንግዶች፣

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ፣ በተለይ ደግሞ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ የሚሠሩ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶችን ወክዬ ስናገር ታላቅ ደስታና ክብር ይሰማኛል::

በኢትዮጵያ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ታሪክ የአጭር ጊዜ ክስተት ነው:: በጣም ቀደም ባሉት ዓመታት የምዕራቡ ዓለም ሚሲዮናውያን በኢትዮጵያ የገጠር አካባቢዎች ይሠሩ ነበር:: ሥራዎቻቸውም በይበልጥ የሚያተኩሩት በትምህርትና በጤና ዘርፎች ላይ ነበር:: ይሁን እንጂ፣ የዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ያደገው፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሕዝብ እለቂት ባሰከተሉት የድርቅ ወቅቶች ነው::

CCRDA

ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች በ1960ዎቹ፣ 80ዎቹና፣ በ90ዎችም ጭምር፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ተከታታይ የድርቅ አደጋዎች በደረሱባቸው ወቅቶች፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት በማትረፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። በተለይም በ1977 ዓ.ም እና በ1978 ዓ.ም ከባድ የድርቅ አደጋዎች በተከሰቱባቸው ወቅቶች፣ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች በችግሩ ለተጐዱ ወገኖች አስቸኳይ እርዳታ በማቅረብ፣ ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች ጊዜያዊ መጠለያዎችን በመሥራት፣ እንዲሁም ወላጅ ያጡ ሕፃናት መርጃዎችን በማቋቋም፣ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። በዚህም መሠረት፣ የዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች፣ ከሀገር ውስጥ አቻዎቻቸው ጋር በመተባበር ባከናወኑት ተግባር፣ ሰብአዊ እልቂትን በመግታት ረገድ በሀገሪቱ ታሪክ ልዩ ሥፍራ አላቸው።

ከእርዳታ አቅርቦትና የድንገተኛ ጊዜ እርዳታ ሥራዎች ወደ ልማት ሥራዎች የመሸጋገሪያው ጊዜ መሆኑን በመረዳት፣ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በተራዘመ የዕለት ደራሽ እርዳታ ምክንያት ተንሰራፍቶ የቆየውን የጥገኝነት ባህልን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ለጋሾችና ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ ድርጅቶች በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ ዓላማቸው ያደረጉት ዘላቂ ልማትን ነው። ዓለም አቀፍ ማህበረሰብና መንግሥት፣ የሰው ኃይል ሥልጠናን ጨምሮ፣ በአጠቃላይ የልማት ሥራዎች ላይ በቂ መዋዕለ ንዋይ ካፈሰሱ፣ የአስቸኳይ ጊዜ የእርዳታ ሥራዎች በዚያው ልክ እየቀነሱ ይሄዳሉ። ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች በይበልጥ ትኩረት ሲሰጡ የቆዩት፣ በሁሉም የልማት መስኮች የሕዝቡን ሕይወት ሊለውጡ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በማካሄድ ላይ ነበር። ለዚህም፣ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል በሚሊዮን ለሚቆጠር ሕዝብ እርዳታዎችን ሲያቀርቡና የልማት ሥራዎችን ሲያካሂዱ የቆዩትንና አሁንም ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውኑትን ወርልድ ቪዥንን፣ አክሽን ኤድ ኢትዮጵያን፣ ሬድ ባርናን፣ ኬር ኢትዮጵያን፣ የካቶሊክ የእርዳታ አገልግሎትንና ሌሎች ኢየሌ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ ልማት ድርጅቶችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

የዓለም አቀፍ በጎ አድራጐት የልማት ድርጅቶች የመጀመሪያ ትኩረት፣ ነባር አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና መንግሥታዊ ድርጅቶችን ከመደገፍ በተጨማሪ፣ በራሳቸው ሠራተኞች በመጠቀም ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ ነበር። ይሁን እንጂ፣ በ1990ዎቹ ሌላ የአሠራር ዘይቤዎችን ተከትለዋል። ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችን ራሳቸው ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ፣ አሠራራቸውን በመለወጥ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አገር በቀል ድርጅቶችን ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ በመርዳት ላይ ይገኛሉ። ስለሆነም፣ የዓለም አቀፍ የበጎ

CCRDA

ፈቃድ የልማት ድርጅቶች የቆየ የአሠራር ባህል ሙሉ በሙሉ ተለውጧል። ዛሬ በአብዛኛው ትኩረት የተሰጠው ለአገር በቀል ድርጅቶች የአቅም ግንባታ የመስጠቱ ሥራ ነው። ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ሙሉ በሙሉ የአገር በቀል ድርጅቶችን አቅም በመገንባት ላይ የሚገኙ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች አሉ። ሌሎች ደግሞ፣ ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የገንዘብ ድጋፍ ከመስጠት በተጨማሪ፣ አቅምን ማሳደግ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የሕዝቡን ተደማጭነት ለማጐልበት ወሳኝነት ያለው የልማት ስልት አድርገው ያራምዳሉ። ይህ ስልት ወደ ዘላቂ ልማት የሚያመራ ጥሩ አማራጭ መሆኑንም በጥብቅ እናምንበታለን።



በኢትዮጵያ የሚገኙ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች፣ አሠራራቸውን ለውጠው ዘላቂ ልማትን የማራመድ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። አገር በቀል ድርጅቶች እርዳታ ተቀባዮች ብቻ ሳይሆኑ፣ በአጋርነት መንፈስ ተነሳስተው፣ የዘላቂ ልማት ዕቅዶችን በማመንጨት፣ የልማት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ በማድረግና በመገምገም ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ፣ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች እርዳታና ድጋፍ ሰጥተዋቸዋል። በግሉ ዘርፍና በሲቪሉ ማህበረሰብ መካከል የተጠናከረ ትብብር እንዲኖር የተመቻቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ረገድም፣ ድርጅቶቹ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች፣ በተለያዩ የልማት ሥራዎቻቸው አማካይነት ድህነትን ለማጥፋት ጉልህ ድርሻ በማበርከት ላይ ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ ለዘላቂ ልማት ወሳኝ የሆኑትን ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ማስፈንን፣ በማህበረሰቦች መካከልና በድርጅቶች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን ማስወገድን፣

እንዲሁም የሰብአዊ መብት ጥበቃን በሚመለከት በምዕራቡ ዓለም የተካበቱ ልምዶችን ለሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ለመንግሥታዊ ድርጅቶች ለማጋራት ችለዋል። ይህ ደግሞ፣ ቀስ በቀስ፣ በሂደት እንጂ፣ በአንድ ጀምበር የተሠራ ሥራ አይደለም።

ማርግሬት ሚድ «በቆራጥነት የተነሳሱ ጥቂት ዜጐች ዓለምን ሊለውጧት ይችላሉ... ብዙ ጊዜ ሲሆን የሚታየው ሀቅም ይሄው ነውሚ ብለዋል። ይህንን ሀቅ በመረዳት፣ አገር በቀል ድርጅቶችና ልማቱ የሚታለምላቸው ማህበረሰቦች፣ ድህነትን ለማጥፋት የሚያስችል ሚና እንዲጫወቱ፣ የመንግሥት ፖሊሲ እንዲወጣ ለመገፋፋት የሚያስችል ተሰሚነት እንዲኖራቸውና የፖሊሲውን አፈጻጸምም መከታተል እንዲችሉ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ ድርጅቶች የአቅም ግንባታ እየሰጡ በማጠናከር ላይ ይገኛሉ።

ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች፣ በአሁኑ ጊዜ በአጠቃላይ በሀገሪቱ ውስጥ፣ እንዲሁም በተለይ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል ያለውን አመቺ የሥራ ሁኔታ እያደነቁ፣ ለወደፊቱም የበለጠ የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር ይጠይቃሉ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከት ሕግ ማውጣት፣ የግሉ ዘርፍ በልማት ሥራዎች የሚያደርገውን ተሳትፎ ለማጠናከርና ለኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ግንባታዎች ጥሪቱን እንዲያፈስ አበረታች የሆነ የታክስ ሥርዓት እንዲኖር ማድረጉ፣ የህገሪቱን ልማት ያሳድጋል። የዚህ ዓይነቱ እርምጃ ቢወሰድ፣ የሲቪሉ ማህበረሰብ ራሱን ሙሉ በሙሉ የመንግሥት የልማት አጋር አድርጉ የመቁጠር ስሜት የሚሰማው መሆኑን ያለምንም ጥርጥር እናምንበታለን።

እስከዛሬ ድረስ፣ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ሥራችን የተቀላጠፈ እንዲሆን እገዛ ላደረጉልን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ግለሰቦችና አጋሮቻችን ሁሉ ምሥጋናችንን እናቀርባለን። የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር፣ ይህንን ታላቅ በዓል በማስተናገዱም የተለየ ምሥጋናችንን እናቀርባለን።

በመጨረሻም፣ ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃድ የልማት ድርጅቶች፣ ድህነትን ለመቀነስና ኢትዮጵያ ለሁሉም የበለፀገች ሀገር እንድትሆን ጉልህ ሚና ለመጫወት፣ በዚህ መድረክ ላይ የልማት አጋርነት ቃል ኪዳናችንን እንድናድስ ይፈቀድልን ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን።

እንደዚህ ያለው "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" በየክልሎቹ በሚንቀሳቀሱና በአጠቃላይም ለሀገሪቱ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ልማት በሚሠሩ ወገኖች መካከል የቅርብ ትብብር ለመፍጠርና ለማጠናከር እንደሚረዳ ተስፋ እናደርጋለን። ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

CGRDA

ከአቶ ፀጋዬ ቀጥለው በአዋሳው "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" በዓል ላይ ንግግር ያደረጉት ሚስተር ሔሊናን ነበሩ። ሚስተር ሔሊናን ድርጅታቸውን የአየርላንድ ኤድን ወክለው የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል።

አየርላንድ ኤድ ረዘም ላለ ጊዜ የልማት አጋር ሆኖ በሠራበት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሚከበረው "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" ድርጅቴን ወክዬ ስናገር ከፍ ያለ ደስታ ይሰማኛል።

በ1984 ዓ.ም ከኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ጋር የልማት አጋርነት ስንመሠርት፣ ሥራችንን ከጀመርንባቸው አካባቢዎች አንዱ ይህ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የልማት አጋርነታችን ይበልጥ ተጠናክሮ፣ በሦስት ዞኖች ውስጥ ድጋፍ እንሰጣለን። በክልልና በዞን ደረጃ ያለንን የልማት ተሳትፎም በማጠናከር ደረጃ ላይ እንገኛለን። አየርላንድ ኤድ፣ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል ፍሬያማ ትብብር እንዲኖር ለማበረታታትና ለማጠናከር፣ እንዲሁም የሲቪሉን ማህበረሰብ የሥራ ሁኔታ ለማሻሻል ከፍተኛ ፍላጐት አለው። ይህንን በሚመለከት ተሳትፎ የምናደርግበትን ሁኔታ ስናመቻች፣ የክርስቲያን በጎ አድራጎትና የልማት ድርጅት፣ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን፣ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" በዓል በዚህ ክልል ውስጥ ለማዘጋጀት ጠቃሚ የሆነ ሃሳብ አቀረበ። ይህንኑ ሃሳብ እኛም በፅኑ ስላመንበት፣ ሃሳቡን ተግባራዊ ለማድረግ አብረን ተሰለፍን። ይህንን "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" የክርስቲያን በጎ አድራጐት ድርጅትን፣ ፓክት ኢትዮጵያን፣ ኤስ. ኤን. ቪንና አክሽን ኤድ ኢትዮጵያን ከመሳሰሉ ታዋቂ ድርጅቶች ጋር አብረን የማዘጋጀት ዕድል በማግኘታችን የተለየ ደስታ ሰጥቶናል።

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ሰፍኖ የሚታየው የዓለም አቀፍ ትብብር ዋና የመገለጫ ባህሪ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በልማት ሥራዎች ማሳተፍ ነው። የለጋሾች ማህበረሰብና የልማት ድርጅቶች በበኩላቸው፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መንግሥት የቀየሳቸውን የልማት ግቦች ተፈጻሚ ከማድረግ ያለፈ አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው የሚል ግንዛቤ ላይ ደርሰዋል።

እነዚህ ድርጅቶች፣ በመንግሥታት የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ በሚካሄዱ ውይይቶችና ከዚያም አልፎ በፖሊሲ ዝግጅቶች ላይ የሚያደርጉት የተሟላ ተሳትፎ፣ ጠንካራ የባለቤትነት ስሜት መፍጠርንና ዘላቂ ልማት ማስፈንን ጨምሮ፣ ከፍተኛ የልማት ጥቅሞችን ያስገኛል።

CCRDA



ተሳትፏዊ የፖሊሲ ዝግጅት፣ በአውሮፓ አንድነት፣ በአፍሪካ፣ በካሬቢያንና በፓስፊክ ሀገሮች መካከል በሰኔ ወር 1992 ዓ.ም ኮቶኑ ውስጥ የተደረሰው የአጋርነት ስምምነት አንዱ አካል ነው። የድህነት ቅነሳን አስመልክተው የወጡት የልማት እርዳታ ኮሚቴ መመሪያዎች፣ የድህነት ቅነሳ ስልቶችን በመንደፍና ተግባራዊ በማድረጉ ሥራ፣ የልማት አጋሮችን በአንድ ላይ የማሰለፍ አስፈላጊነትን አፅንኦት ሰጥተውታል።

የሁለትዮሽ ስምምነቶች፣ በእርዳታ ተቀባይና በለጋሽ ሀገሮች መካከል ለሚኖረው ትብብር መሠረት የሚጥሉ ናቸው። በማንኛውም አቅጣጫ ሲታይ፣ ልማትን በኃላፊነት ማራመድ ያለባቸው መንግሥታት ራሳቸው ናቸው። ይሁን እንጂ፣ የሲቪል ማህበረሰቦችም በሀገሮች የልማት ሥራዎች ወሳኝ የሆነ ሚና መጫወት ያለባቸው መሆኑን አየርላንድ ኤድ ያምንበታል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ በተለይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ከልማት የተገለሉ ማህበረሰቦችን ይዞታ በሚገባ የሚረዱና እገዛም የሚያደርጉ ናቸው። ለእነዚህ ወገኖች እገዛ ካልተደረገ ድህነት ድምፅ-አልባ አድርጉ ያስቀራቸዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ድምፅ የለሽ የሆኑ የሕብረተሰብ አባላትን ለመድረስ ከቻሉ፣ ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩበትና ዲሞክራሲ

CCRDA

የሰፈነበት መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር የሚያስችል ወሳኝ ቦታ ያስገኙላቸዋል። እነዚህ ድርጅቶች፣ በአንድ የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ከልማት የተገለሉ ወገኖች ከዕይታ የሚወጡበትን ክፍተት ለይተው የማሳየት ልዩ ሚና አላቸው።

ግልጽና ውጤታማ የሆነ የልማት ስልት ለመንደፍና ደካማ ድምጽ ያላቸውን ወገኖች ድምጻቸውን ለማጐልበት፣ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል ጠንካራ የሥራ ትብብርና አጋርነት ያስፈልጋል። ይህም በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ለጋሽ ድርጅቶችና የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች፣ እርስ በርስ ለመተባበርና ለመደጋገፍ የሚያስችሉ ስልቶችን ለመቀየስ የሚያደርጓቸው ጥረቶች ከፍ ያለ ጠቀሜታን ያስገኛሉ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡባቸውን ሴክተሮች፣ ሌሎች የልማት አጋሮች ዕውቅና ሰጥተው ሲደግፏቸው፣ ይበልጥ ለመተባበር አዳዲስ ዕድሎች ይፈጠራሉ። ይህ ግን አስቸጋሪ ፈተናዎችን ሳይወጡ የሚሳካ አይደለም። እውነተኛ አጋርነት፣ በተለያዩ ለጋሾች፣ በመንግሥት፣ በራሳቸው መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መካከልና በሕብረተሰቡም ውስጥ የበለጠ ጠንካራ የሥራ ቅንጅትን ይፈጥራል። የሥራ ድግግሞሽንና እንደ ልብ የሚይገኘውን ሀብት ብክነት ለማስወገድ፣ የተቀናጀ አሠራር ወሳኝነት አለው።

በመካሄድ ላይ ያለው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት በመንግሥት፣ በለጋሾችና በሲቪሉ ማህበረሰብ መካከል አዳዲስ የትብብር ዕድሎችን በመፍጠር ረገድ ጥሩ ምሳሌ ነው። ድህነትንና ከልማት የመገለልን ችግሮች ማቃለል ስለሚቻልበት ሁኔታ በሚካሄዱ ውይይቶችና ክርክሮች ላይ፣ የአዳዲስ ድምጾችን አስተዋፅኦ እየሰማን ነው። የቁጥጥር ማዕቀፍ የሚኖረውንና የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ በመፍጠር፣ የሲቪሉ ማሕበረሰብ ለኢትዮጵያ ልማትና እድገት አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚያስችለውን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከተው ሕግ በቅርብ ቀን እንደሚወጣ በተስፋ እየጠበቅን ነው። የሕብረተሰቡን ተሳትፎና ተሰሚነት ለማረጋገጥ፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃዎችና ዲሞክራሲያዊ አሠራርን ለማስፈን በሚያስችሉ ሥራዎች ላይ የተሠማሩትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ሌሎች የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን ለማጠናከር፣ የመንግሥትና የለጋሾች ድጋፍ ወሳኝነት ይኖረዋል። ድጋፉም ከገንዘብ መዋጮ ያለፈና በመንግሥትና በሲቪሉ ማህበረሰብ መካከል ሰፊ የውይይት መድረክ መፍጠርን የሚጨምር መሆን አለበት።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ተሳትፏዊ የዕቅድ አወጣጥ ሂደትን በማራመድና ተሳትፏዊ የልማት አሠራርን በማመቻቸት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሕዝቡን ግንዛቤ በማሳደግ፣

CCRDA

እንዲሁም መንግሥታት በልማት ሂደት ውስጥ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን በማጠናከር እንዲተባበሩ ውይይት በማካሄድ፣ መልካም አስተዳደርን ያጠናክራሉ። መንግሥታትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሕዝብ ተሳትፎን የበለጠ ለማስፋፋት አብረው ከሠሩ፣ የአስተዳደሩ ሥርዓት በሕዝቡ ዓይን የበለጠ ሕጋዊነት ይኖረዋል። ይህም ሲሆን፣ ብዙው ሕዝብ በራሱ ጥንካሬ ላይ ተመሥርቶ በልማት ሥራዎች በመሳተፍ ሀገሩን ያሳድጋል። ሰላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ የሚከተለውን ንግግር በማድረግ "መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን" በዓልን በኦፊሲየል ከፍተዋል።

የተከበራችሁ እንግዶች

በክልል ደረጃ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከበረውን «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንሚ ለማስተናገድ ዕድል ስለተሰጠን፣ በክልሉ መንግሥትና ሕዝብ ስም፣ እንዲሁም በራሴ ስም አዘጋጆችን ክልብ እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። እንግዶቻችን፣ ሁላችሁም ወደ ክልላችን እንኳን ደህና መጣችሁ እላችኋለሁ።

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአብዛኛው ሥራቸውን የጀመሩት የዕለት ድራሽ ዕርዳታ በማቅረብ ቢሆንም፣ ከእነዚሁ መካከል አብዛኛዎቹ በሂደት በመልሶ ማቋቋምና የልማት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። ሌሎች ደግሞ በቀጥታ የልማት ሥራ ጀምረዋል።

አብዛኛዎቹ መያዶች መንግሥት በሚያካሂዳቸው የገጠር ልማት ሥራዎች ከፍተኛ አስተዋዕኦ እንዳበረከቱ ከበርካታ ጥናቶች ለመረዳት ችለናል። ወደፊትም ተመሳሳይ ጥናት ሊያበረክቱ እንደሚችሉ እምነታችን ነው። በቅርባችን እንዳሉት የአፍሪካ ሀገሮች ሁሉ በእኛም ሀገር የመያዶች ቁጥር በዓይነትም በብዛትም ጨምሮ፣ በጋራ ብዙ መሥራት እንዳለብን እናምናለን።

CCRDA



በኢትዮጵያ ድህነትን ለመቀነስ በምናደርገው እንቅስቃሴ፣ ሥልጣንን ሕዝቡን በቀጥታ ሊያሳትፉ ለሚችሉት መንግሥታዊ አካላት፣ ማለትም ለወረዳና ለቀበሌ መዋቅሮች ለማድረስ፣ ያልተማከለ አስተዳደርን ተግባራዊ የማድረጉ ሥራ እየተካሄደ ነው። ይህንኑ ሥውን በማድረግ ረገድ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቂ ልምድ ስላላቸው፣ መዋቅሮቹን የማጠናከር ሰፊ የሥራ ድርሻ ይጠበቅባቸዋል።

መያዶች፣ በልማት ሥራዎች የሕዝብ ተሳትፎን የማጐልበት ተሞክሮአቸውን በማስፋፋትና ዲሞክራሲን የማስፈን ጥረትን በማጐልበት ረገድ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉም ይጠበቃል። የገጠር ልማት፣ እንደሌሎች የልማት ሥራዎች ሁሉ መሠረቱ ሕዝቡ ስለሆነ፣ የሕዝቡን የማቀድና የማስፈጸም አቅም ማጐልበት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

ለመያዶች አመቺ የሥራ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በመንግሥት በኩል አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት እናምናለን። እንዲህም ሆኖ፣ ጥቂት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሥራ መፈለጊያ እንጂ ለሕዝብ አገልግሎት የተሰማሩ እንዳልሆኑ የሚያስመስሉ አዝማሚያዎች ስለሚታዩ፣ ይህ ሁኔታ መታረም እንዳለበት ይሰማናል። ከዚህ አመለካከት በመነሳት ቁጥር ለማብዛት የሚደረገው አካሄድ፣ በአብዛኛው በመልካም ተግባር ላይ የተሰለፉትን መያዶችም ቅር የሚያሰኝ ስለሆነ፣ ሁኔታውን እያስተካከለን መሄድ እንዳለብን ይሰማናል።

CCRDA

አገራችን ገና ብዙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አስተዋፅኦ ትፈልጋለች:: ያሉትም አቅማቸው የጐለበተ እንዲሆን ምኞታችን ነው:: ለመንግሥታዊ መዋቅሮች አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ችግሮችን በጋራ እየፈታን፣ የድህነት ቅነሳ ስልቱን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንደ ልማት አጋር ሳይሆን እንደ ባላንጣ የማየት አመለካከትን ለማስወገድ መጣርና ከመካከላቸው ለምንመኘው ልማት አጋር ሳይሆኑ እንቅፋት የሚሆኑ ካሉ፣ ለይተን ማስተካከልና መሥራት ያለብን ይመስለኛል::

መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ያወጣቸውን የአቅም ግንባታን፣ የገጠር ልማትን፣ የከተማንና የኢንዱስትሪ ልማትን፣ እንደዚሁም የሕዝብ ተሳትፎንና የዲሞክራሲ ሥርዓት የማስፈን ተግባራትን በጋራ ለመወጣት፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የተዘጋጀ በመሆኑ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዚህ መጠነ ሰፊ ሥራ ከእኛ ጐን እንደሚሰለፉ እናምናለን:: በመጨረሻም፣ ይህንን ሚድረክ በማዘጋጀት የተባበሩንን የክርስቲያን በጎ አድራጐትና የልማት ድርጅትን፣ አክሽን ኤድን፣ ፓክት ኢትዮጵያን፣ አየርላንድ ኤድንና የኔዘርላንድ የልማት ድርጅትን /ኤስ.ኤን.ቪ/ ከልብ እያመሰገንን፣ በምታከናውኗቸው የልማት ሥራዎች ሁሉ ከጐናችሁ የምንሰለፍ መሆኑን ልናረጋግጥ እንወዳለን:: አመሰግናለሁ::

የመክፈቻ ሥነ ሥርዓቱ ከተከናወነ በኋላ፣ በበዓሉ ላይ የተሳተፉትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጠቅላላ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያሳየውን ኤግዚቢሽን የከፈቱት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል ፕሬዚዳንት ሲሆኑ፣ ይህንኑ ለሦስት ቀናት ለሕዝብ ክፍት ሆኖ የቆየውን ኤግዚቢሽን ያቀረቡት 105 የሚሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ነበሩ::

በኤግዚቢሽኑ ላይ የቀረቡት ልዩ ልዩ ዝግጅቶች፣ የግብረሠናይ ድርጅቶቹን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ፎቶግራፎች፣ የቪዲዮ ፊልሞች፣ የፕሮጀክት ሞዴሎች፣ በቻርት የተደገፉ መግለጫዎች ሲሆኑ፣ የእያንዳንዱን ድርጅት ታሪክና የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልጹ ልዩ ልዩ ዕትሞችም ለኤግዚቢሽኑ ተመልካቾች ታድለዋል::

CCRDA

2. የፓነል ውይይቶች

ከመያዶች ቀን የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ቀጥሎ ለሦስት ተከታታይ ቀናት የፓነል ውይይቶች ተካሂደዋል:: የፓነል ውይይቶቹ ርዕሶችም የሚከተሉት ነበሩ::

- በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያካሂዷቸው የልማት ሥራዎች ያጋጠሙ አመቺ ዕድሎችና ተፈታታኝ ችግሮች፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደርና በሰላም ግንባታ ያላቸው ሚናና አስተዋፅኦ፣

CCRDA

የመጀመሪያው ቀን የፓነል ውይይት

ቀን፡ጠ ታህሣሥ 5 ቀን፣ 1994 ዓ.ም

ሰዓት፡ጠ ከ8:30 - 11:00 ሰዓት

የውይይት ፎረሙ አስተባባሪ፣ አቶ ፀጋዬ ቸርነት

አወያይ፣ አቶ ፍቅሩ አበበ

2.1 ዐቢይ ርዕስ፡-መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል በሚያካሂዷቸው የልማት ሥራዎች ያጋጠሙ አመቺ ዕድሎችና ተፈታታኝ ችግሮች

የፓነል አቅራቢዎች፡-

አቶ ማዕረግ ኃይለማርያም፣ /ከደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር/

ዶክተር ጥላሁን ደፈርሶ፣ /ከኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ/

አቶ ይጥና ተካልኝ፣ /ከአክሽን ኤድ/

አቶ ዘሪሁን በየነ፣ /ከወርልድ ቪዥን/

የውይይት ፎረሙ አስተባባሪ አቶ ፀጋዬ ቸርነት፣ የፓነል ውይይቱ ዋና ዓላማ፣ ለመያዶች የሥራ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ሃሳቦችን ለማቅረብና ለመመካከር፣ እንዲሁም ለወደፊቱ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ የሚያስችሉ ሃሳቦችን ለማሰባሰብ እንዲረዳ መሆኑን ገልጸው፣ መድረኩን ለአወያዩ ለአቶ ፍቅሩ አበበ አስረክቡ:: ከዚያም፣ አቶ ፍቅሩ አበበ፣ የፓነል ውይይት አቅራቢዎቹንና ተሳታፊ እንግዶችን በድጋሜ እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ፣ አቶ ማዕረግ ኃይለማርያምን የመጀመሪያ ተናጋሪ እንዲሆኑ በመጋበዝና የፓነል ውይይቱ አቅራቢዎች የተመደበላቸውን ጊዜ እንዲያከብሩ በማሳሰብ ውይይቱ እንዲጀመር አደረጉ:: አቶ ማዕረግ፣ ለውይይት መነሻ እንዲሆን አዘጋጅተው ያቀረቡት ጽሁፍ በአጭሩ የሚከተለው ነው::

CCRDA

2.1.1 የጋነል አቅራቢው ርዕስ፡ጠ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል ያለ ግንኙነት፣ ዋና ዋና ችግሮችና በቀጣይ የታሰቡ ምቹ ሁኔታዎች

በእኔ በኩል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሚመለከት ለውይይት መነሻ የሚያገለግሉ ነጥቦችን አጠር አጠር አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ። ክልላችን 13 ዞኖችና 8 ልዩ ወረዳዎች አሉት። የቆዳ ስፋቱም 113-539 ካሬ ኪ.ሜ ነው። ቁጥሩ ከ12 ሚሊዮን በላይ የሆነ ሕዝብ ይኖርበታል። በየዓመቱ ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ቁጥር እድገት ከሚታይባቸው ክልሎች ውስጥ አንዱ ነው። የአብዛኛው ሕዝብ መተዳደሪያ ግብርና ነው። ከ56ጠ57 ከመቶ የሚሆነው የክልሉ ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች የሚኖር ነው። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአብዛኛው ወደ ክልሉ የገቡት በድርቅ ወቅቶች ነው።

የድርቁ ችግር እንደተቃለለ መያዶቹ ትኩረታቸውን ወደ ልማት አዙረዋል። በደቡብ ክልል የአካባቢውን ሀብት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሀብት ጋር አቀናጅቶ ለመሥራት እንዲቻል፣ የማስተባበሪያ ሥራው የሚሠራው በክልሉ የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ነው።

በአሁኑ ወቅት 89 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በክልላችን ይንቀሳቀሳሉ። የፕሮጀክት ውል የተፈረመባቸው 246 ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች አሉን። አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች፣ በተቀናጀ ልማት፣ በግብርናና አካባቢ ጥበቃ፣ በህብረት ሥራ፣ በምግብ ዋስትና፣ በአደጋ መከላከልና መልሶ ማቋቋም፣ በመሰኖ ልማት፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ በገጠር መንገድ፣ እንዲሁም እጅግ አሳሳቢና አስከፊ እየሆነ በመጣው ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ላይ የሚሠሩ ናቸው።

የፕሮጀክት ዘመናችን በአብዛኛው ከ1 እስከ 5 ዓመት የሚደርስ ነው። 6 ዓመትም ያለው አለ። ከዚያም በታች ያለው አለ። በአጠቃላይ ከያዝነው 1994 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ የፕሮጀክት ውለታ ለተፈራረምንባቸው ፕሮጀክቶች ከ734 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ በጀት ነው የያዝነው። ከዚህ የበጀት ስምምነት ውስጥ እ.ኤ.አ አሁን እያገባደድን ባለነው 2001፣ ከ138 ሚሊዮን ብር በላይ ተመድቦ በሥራ ላይ እየዋለ ነው። የዓመቱን የሥራ አፈጻጸም በዚህ ዘገባ ውስጥ ማቅረብ ትንሽ ያስቸግራል። አንዳንዶቹ ሪፖርቶቹ ገና ያልደረሱ ስለሆነ ዘገባዬ አልተጠናቀቀም።


CCRDA

በክልላችን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስርጭትን በተመለከተ ሲዳማ 22፣ ጉራጌ 23፣ ሃዲያ 7፣ ኮንሶ 5፣ ዳውሮ 2፣ ሸካ 1 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። ኮንታ ልዩ ወረዳ አንድም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የለም።

በክልላችን ውስጥ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሀብት ከመንግሥት ሀብት ጋር እንዲቀናጅ ጥረት ይደረጋል። የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፖሊሲ መመሪያን መሠረት ያደረጉና ከውጭ አገር ለሚገቡ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ዕድል ወይም መብት እንሰጣለን። በፕሮጀክቱ ለሚያገለግሉ የውጭ አገር ዜጐች የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ይሰጣል። የተለያዩ የባለሙያዎች ድጋፍም እናደርጋለን። ከዚህም በተጨማሪ በአፈጻጸም ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮች ሲኖሩ፣ በተቻለ መጠን ከዞንና ከወረዳ ጋር በመገናኘት ችግሮቹን ለማቃለል ጥረት እናደርጋለን።

ተከታታይ የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማም ሥራ የሚከናወነው አሁንም በመንግሥት መዋቅሮች አማካይነት ነው። በክልሉ መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል የቅርብ ትብብርና መደጋገፍ አለ። ይሁን እንጂ፣ ክልላችን ካለበት መጠነ ሰፊ የሆነ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር አንፃር፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። ሥርጭቱም የተመጣጠነ አይደለም።

በዚህ ዓመት፣ የፌዴራሉን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፖሊሲና መመሪያ መሠረት ያደረገ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከት ክልላዊ መመሪያ ለማዘጋጀት ሞክረናል። መመሪያው የተዘጋጀው የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኤክስፐርቶችን፣ ባለሙያዎችንና ከፍተኛ የአመራር ኃላፊዎችን በየደረጃው በማሳተፍ ነው። የመመሪያው ረቂቅ በተለያዩ ዞኖች ውይይት ተካሂዶበታል። ከውይይቱ የተገኙት አስተያየቶች ተካተው ይኸው መመሪያ በቅርቡ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።



CCRDA

የክርስቲያን በጎ አድራጎትና የልማት ድርጅት ለመመሪያው ዝግጅት በራሱ ተነሳሽነት የበጀት እገዛ በማድረግ አብሮን ሠርቷል። እንደ አክሽን ኤድ፣ መካነየሱስ፣ ኤስ. አይ. ኤም፣ ኤስ. ኦ. ኤስ. ሳህል እና ሲ. ሲ. ኤፍ. አይ. የመሳሰሉ መንግሥታዊ ያልሆኑና በሃይማኖት ላይ የተመሠረቱ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የተቻላቸውን ያህል ድጋፍ ሰጥተውናል። በክልላችንና በመያዶች መካከል የቅርብ ትብብር መኖሩን ስንገልጽ፣ አንዳንድ ችግሮች መኖራቸውን ማመልከትም እንወዳለን። ስለሆነም፣ ዋና ዋና ችግሮችን ለመጥቀስ እሞክራለሁ። የምጠቅሳቸው ችግሮች በመንግሥትም በመያዶችም በኩል ያሉ ናቸው። በመጀመሪያ በመንግሥት በአጠቃላይ የሚታዩ ችግሮችን እጠቁማለሁ። ክልል አቀፍ የሆነ የመያዶች መመሪያ እስካሁን ድረስ አለማዘጋጀታችን እንደ አንድ ችግር የሚታይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከክልሉ ስፋትና በውስጡ ካሉት በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አንፃር አሁን ያሉት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር በጣም ትንሽ ነው። ስርጭቱም ሚዛናዊ አይደለም። ይህም በመሆኑ፣ በርካታ መያዶች ወደ ክልላችን ገብተው እንዲሠሩ አመቺ ሁኔታን መፍጠር እንዳለብን እናምናለን። በአንዳንድ የመንግሥት መዋቅሮች፣ በተለይም በወረዳና በዞን ደረጃዎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንደልማት አጋር ያለመቁጠር ችግርም ይታያል። ይህንን አመለካከት ለመለወጥ የግንዛቤ ለውጥ የሚያስገኝ ሥራ መሥራትን ይጠይቃል። በመንግሥት መዋቅሮች የሚሠሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ቶሎ ቶሎ ከቦታ ቦታ መቀያየራቸው ለጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ አስቸጋሪ ሆኖ በመታየቱ፣ መፍትሔ ሲሰጠው የሚገባ መሆኑን እናምንበታለን።

የምንከተላቸው አሠራሮች በአብዛኛው በማዕከልና በክልል ደረጃ የተንጠለጠሉ ናቸው። ያልተማከለ አሠራር እስካሁን ድረስ ውሱን ነው። ሌላው የመንግሥት ተቋማት የአቅም ውሱንነት ነው። የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስና የበጀት አቅሙ ውሱን ነው። እነዚህን በማዳበር ረገድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከፍተኛ እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ። ከመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሚቀርቡልን ሪፖርቶች የተቀላጠፈ መልስ በመስጠት ረገድም ችግር አለብን። ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም፣ ለክትትልና ግምገማ አምስት ኤክስፐርቶች የሚያስፈልገው ቡድን አለ። እኛ ግን ሁለት ኤክስፐርቶች ብቻ ናቸው ያሉን። የምንከተለው አሠራር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከለጋሾቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት መገምገም የሚያስችል አይደለም። ተጠያቂነት በአዲሱ መያዶችን የሚመለከት መመሪያ ውስጥ ሰፍሯል።

በመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በኩል ከሚታዩ ችግሮች መካከል ደግሞ የሚከተሉት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። ሕጋዊ ምዝገባና የፕሮጀክት ውል ሳይኖራቸው የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። ከፕሮጀክት ውል በ፫ላ የዓመታዊ ሰቅድ ሪፖርታቸውን የማያቀርቡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም አሉ።

GCRDA

ከውጭ አገር በሚገኝ እርዳታ ላይ ብቻ ከሚገባው በላይ የመተማመን ሁኔታ አለ። ስለሆነም በአገር ውስጥ የገንዘብ አቅምን ለማዳበር የሚደረገው ጥረት ውሱን ነው። የሀገር ውስጥ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ብዙ የተለመዱ አይደሉም። የፕሮጀክት ርክክብ ሲደረግ ለሚኖር ዝግጅት፣ ቀደም ብሎ ተገቢውን እሳቤ አለመውሰድም ሌላው ችግር ነው። የአንዳንድ ፕሮጀክቶች ዘላቂነትም ብዙ ጊዜ የሚያከራክር ጉዳይ ነው። አንዳንድ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፕሮጀክት ውል ከተፈራረሙ በኋላ ምንም የእርዳታ ገንዘብ አያገኙም፣ ወይም አነስተኛ ገንዘብ ብቻ ይፈቀድላቸዋል። በሕዝቡ ስም የሚያገኙትን ገንዘብ ከፕሮጀክት ስምምነት ውጭ የሚጠቀሙ መያዶችም አሉ። በፕሮጀክት መረጣ ወቅት፣ መያዶች እንደልብ ለሚደረስባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸው፣ ኋላ ቀር የሆኑ አካባቢዎችን ይበልጥ እንዲረሱ አድርጓቸዋል። በክልላችን በኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቅንጅት ደካማ ነው። ሁሉም በየራሳቸው ነው ጥረት የሚያደርጉት።

በሌላም በኩል፣ በክልላችን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የልማት ተሳትፎን ለማጠናከር የተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች አሉ። በመጠናቀቅ ላይ የሚገኘው ክልላዊ የሥራ አፈጻጸም መመሪያ፣ ላልተማከለ አስተዳደር ትኩረት የሰጠ፣ የተጠያቂነት መርህን ከግምት ውስጥ ያስገባ፣ ለሥራ ቅልጥፍና እንዲረዳ የእያንዳንዱን አካል ተግባር ለይቶ ያመለከተ ስለሆነ፣ ይህ በክልላችን ለመያዶች የተፈጠረ ምቹ የሥራ ሁኔታ ነው ብለን እንገምታለን።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በሚመለከት ቀደም ሲል የነበረው የተሳሳተ ግንዛቤ፣ ተለውጦ የተሻለ ግንዛቤ እየተፈጠረ መምጣቱ፣ ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አንፃር አንድ ታላቅ እርምጃ ነው ብለን እናምናለን።

አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አቅማቸውን አዳብረው ውጤታማ እንዲሆኑ ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ መዘጋጀታችንም አንድ ራሱን የቻለ ምቹ ሁኔታ ነው ብለን እናምናለን። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በሚመለከት ቀደም ሲል የነበረው አመለካከት ተቀይሮ የልማት አጋሮቻችን እንደሆኑ ማረጋገጣችን፣ በክልላችን የመያዶችን የሥራ እንቅስቃሴ ለማጠናከር የተፈጠረ አንድ ምቹ የሥራ ሁኔታ ነው። ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

አወያዩ አቶ ፍቅሩ አበበ አቶ ማዕረጉ ላቀረቡት ሰፊ መረጃ የሰጠ ጽሁፍ አመስግነው፣ የሚቀጥሉትን ተናጋሪ ጋበዙ። ከአቶ ማዕረጉ ኃይለማርያም ቀጥለው የጽሁፍ ዝግጅታቸውን ያቀረቡት ዶክተር ጥላሁን ዳፈርሶ ነበሩ። ዶክተር ጥላሁን ያቀረቡት ጽሁፍ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው።

CCRDA

2.1.2 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ፣ በተለይ ደግሞ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል የምታካሂደው የእርዳታ የልማት ሥራ

እኔ በቅድሚያ የማቀርበው አጠቃላይ የቤተክርስቲያኒቷን ሥራ የሚመለከት ይሆናል። የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ፣ ብሔራዊት ቤተክርስቲያን ሆና ከመመሥረቷ በፊት፣ አምስት የሉተራን ሚሲዮኖች ነበሩ። እነዚሁ ሚሲዮናዊያን ድርጅቶች ልማቱንና የወንጌሉን ሥራ ለየብቻቸው ሲሠሩ ከቆዩ በ፲ላ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ በሀገር ደረጃ ብሔራዊት ቤተክርስቲያን ሆና እ.ኤ.አ ጃንዋሪ 21 1959 ዓ.ም ስትቋቋም፣ ሥራዎቹን አጠቃልላ መሥራት ጀመረች። ቤተክርስቲያኒቷ የምታካሂዳቸው የልማት ሥራዎችም ትምህርት፣ ጤና፣ የወጣቶችና ሕፃናት እንክብካቤ፣ የውሃ ሥራ፣ ሁለገብ የገጠር ልማት፣ ተስማሚ ቴክኖሎጂን ማስፋፋት፣ የሥነ ተዋልዶ እንዲሁም፣ ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች ናቸው።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ በአጠቃላይ በሀገሪቱ ውስጥ 36 አንደኛ ደረጃና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሏት። የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ቤቶችም አሏት። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 13-450 ተማሪዎች አሉ። ቤተክርስቲያኒቷ 59 የጤና ድርጅቶች ያሏት ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ሆስፒታሎች 2፣ ጤና ጣቢያዎች 8፣ ክሊኒኮች 49 ናቸው። የጤና ድርጅቶቹ በክልል ደረጃ ሲከፋፈሉ በኦሮሚያ 29፣ በደቡብ ክልል 23፣ አማራ ክልል 1፣ በጋምቤላ ክልል 4፣ ቤንሻንጉል 2 ናቸው። ተጠቃሚው ህብረተሰብ 1.5 ሚሊዮን ይሆናል።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ በአጠቃላይ 27 ሁለገብ የገጠር ልማት ፕሮጀክቶች አሏት። እነዚህም በኦሮሚያ ክልል፣ በአማራ ክልል፣ በቤንሻንጉል ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ በትግራይ ክልል፣ በአዲስ አበባ ክልል፣ የሚካሄዱ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል 12፣ በደቡብ ክልል 6፣ በአማራ ክልል 4፣ በቤንሻንጉል 2፣ በጋምቤላ 1፣ በትግራይ 1፣ በአዲስ አበባ 1 ይገኛሉ። ተጠቃሚው ህብረተሰብ ከሰባት መቶ ሺህ በላይ ይሆናል። የወጣቶችና የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራሞች በአጠቃላይ ወደ 41 ይደርሳሉ። እነዚህም ደግሞ በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በትግራይ ክልል፣ በአማራ ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ በአዲስ አበባ ክልል፣ የሚገኙ ናቸው።

CCRDA

የውሃ ልማት ፕሮግራምን በተመለከተም፣ ቤተክርስቲያኒቱ ሥራ በምታካሂድባቸው አካባቢዎች ሁሉ፣ ማለትም በየሲኖዶሱ የውሃ ሥራ ይሠራል። በዚህም መሠረት በርካታ ጥልቅ ጉድጓዶችና የእጅ ጉድጓዶች በየአካባቢው ተቆፍረው አገልግሎት ይሰጣሉ። በርካታ የምንጭ ማጎልበት ሥራዎችም ተካሂደዋል። አስቸኳይ የዕርዳታ ሥራን በተመለከተም፣ ቤተክርስቲያኒቷ በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል፣ በአማራ ክልል፣ በሶማሌ ክልልና በሌሎችም አካባቢዎች በርካታ የአስቸኳይ ዕርዳታ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ትገኛለች። በዚህም ዕርዳታዋ የበርካታ ወገኖቻችንን ሕይወት አትርፋለች።

በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ እርዳታ የሚካሄዱት ትምህርት ቤቶች በአብዛኛው የተሠሩት በገጠር በመሆኑ፣ በስፋት እያገለገሉ ያሉት የገጠሩን ሕብረተሰብ ወይም ገበሬውን ነው። ትምህርት ቤቶቹም በሕዝብም ሆነ በመንግሥት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በደቡብ ክልል በቤተክርስቲያኒቱ እርዳታ የሚካሄዱ 8 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና 2 መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ፣ የተማሪዎቹ ብዛት 3-955 ይሆናል። የትምህርት ቤቶቹ ሥራ የተቃና እንዲሆን የክልሉ ትምህርት ቢሮና የዞኖችና የልዩ ወረዳ ትምህርት ቢሮ ጽሕፈት ቤቶች አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ላይ ናቸው።

በደቡብ ክልል የጤና አገልግሎትን በተመለከተ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ ያቋቋመቻቸው 3 ጤና ኬላዎች፣ 15 ክሊኒኮች፣ 2 ጤና ጣቢያዎችና 1 የገጠር ሆስፒታል ይገኙሉ። በሁሉም የጤና ድርጅቶች በአጠቃላይ 401-519 ተጠቃሚዎች አገልግሎት ያገኛሉ። በሁሉም የጤና አገልግሎቶች ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን ጨምሮ የጤና ትምህርት ይሰጣል። ለጤና አገልግሎቱ ሥራ ከክልሉ ጤና ቢሮ፣ ከየዞኖቹና ከየወረዳዎቹ የጤና ጽሕፈት ቤቶች ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣል።

እንዲያም ሆኖ፣ በጤናው መስክ ያጋጠሙን ችግሮች አሉ። በአዲሱ የጤና ፖሊሲ ክሊኒክ በመዋቅር ውስጥ የለም። ከኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ የጤና ድርጅቶች አብዛኛዎቹ ክሊኒኮች በመሆናቸው፣ ወደ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ለማሳደግ ወጪ ስለሚጠይቅ፣ ይህንን ለማድረግ አልተቻለም።

በደቡብ ክልል የወጣቶችና ሕፃናትን እንክብካቤ በተመለከተም፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ወላጅ አልባ የሆኑ ወጣቶችንና ሕፃናትን በሆስቴሎች ውስጥ ሰብስባ በየትምህርት ቤቶች እያስተማረችና እየተንከባከበች ትገኛለች። በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ክልላዊ መንግሥት 7 ሆስቴሎች ሲኖሩን ተጠቃሚ ወጣቶችና ሕፃናት ቁጥር 792 ነው። እነዚህም ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና የድሃ ቤተሰቦች ሕፃናት ናቸው።

CCRDA

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነየሱስ የምታካሂዳቸው የልማት ሥራዎች በሙሉ ለድህነት ቅነሳ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው:: በደቡብ ክልል አመቺ የሥራ ሁኔታዎች የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ከመንግሥት የተለያዩ ቢሮዎችና መምሪያዎች ጋር ያለው ጥሩ ግንኙነት፣ ከሕብረተሰቡ ተቀባይነትን ማግኘት፣ መካነየሱስ ከሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ከተለያዩ ረጂ ድርጅቶች ጋር ያላት ጤናማ የሥራ ግንኙነት ናቸው:: ዋና ተፈታታኝ ችግሮች ሆነው የተገኙት ደግሞ፣ የጤና ፖሊሲ ክሊኒክን ከመዋቅር ማስቀረቱና በፖሊሲው መሠረት ክሊኒክን ወደ ጤና ጣቢያ ለማሻሻል አለመቻል ናቸው::

በአዲሱ ትምህርት ፖሊሲ መሠረት፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ወይም እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ለማሻሻል አለመቻልም፣ ሌላው መካነየሱስን በልማት ሥራዋ ላይ ያጋጠማት ችግር ነው::

የምናገለግለው ሕብረተሰብ አንድ እንደመሆኑ ይህ የመንግሥት ነው፣ ይህ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ጉዳይ ነው ሳንል፣ ድህነትን ለመቀነስና ሀገራችንን ከኋላ ቀርነት ለማላቀቅ እጅ ለእጅ ተያይዘን እንሥራ:: ሕዝባችንን በከፍተኛ ደረጃ እየጨረሰ ያለውን ኤች አይ ቪ ኤድስንም በጋራ እንከላከል:: ይህንንም ሁሉ እንድናደርግ አምላካችን በኃይሉ ይርዳን:: አመሰግናለሁ::

አወያዩ አቶ ፍቅሩ አበበ፣ ዶክተር ጥላሁንን አመስግነው፣ አቶ ይጥና ተካልኝ አክሽን ኤድ ኢትዮጵያን በመወከል ያዘጋጁትን ጽሁፍ እንዲያቀርቡ ጋበዙ:: አቶ ይጥና ያቀረቡት የውይይት መነሻ ጽሁፍ ባጭሩ የሚከተለው ነው::

2.1.3 **የፓነል አቅራቢው ርዕስ:- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል ድህነትን ለማቃለል ያላቸው ሚና**

እኔ የማቀርበው ጽሁፍ አክሽን ኤድ በዓለም አቀፍ ደረጃና በአገር ደረጃ ካገኛቸው ልምዶች በመነሳት፣ የድርጅቱን አመለካከት የሚያንፀባርቅ ነው:: ጽሁፉ መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በልማት የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች፣ በተለይም ድህነትን ለመቀነስ የሚጫወቱትን ሚና በሚመለከት መጠነኛ ጭብጥ ለማስያዝም ይሞክራል::

አክሽን ኤድ ወደ ደቡብ ክልል የገባው እ.ኤ.አ. በ1989 መጀመሪያ ላይ ነው:: የልማት ፕሮግራም የጀመረውም በዳሎቻ ነው:: አክሽን ኤድ የሠራቸውን ሥራዎች በሚመለከት

CCRDA

ኤግዚቢሽኑ ላይ በዝርዝር የቀረቡ መግለጫዎች ስላሉ፣ እኔ በጽሁፌ ለማንፀባረቅ የምሞክረው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚናቸው ምን መሆን አለበት? መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን መንግሥት እንዴት ነው ማየት ያለበት? ወደፊትስ በምን ዓይነት መልክ አብረን መሥራት እንችላለን? እንዴት ዓይነት አመቺ የሆነ የፖሊሲና የሥራ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይቻላል? የሚሉትን ብቻ ይሆናል::

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትልቅ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ የልማት አጋሮች ናቸው:: የመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትልቁ ራዕይ፣ ድህነትን መቀነስና ልማትን ማስፈን ነው::

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሥራ ባሕሪያቸው የተነሳ አብዛኛዎቹ በቀጥታ ከሕብረተሰቡ ጋር ይገናኛሉ:: የአሠራር ዘዴያቸው የተፋጠነና እንደየአካባቢው ሁኔታ ሊለዋወጥ የሚችል በመሆኑ፣ አማራጭ የሥራ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ስለሆነም፣ መንግሥት እሱን ያግዙት ዘንድ ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት፣ አመቺ የሥራ ሁኔታዎችን መፍጠር ይኖርበታል::

እንደሚታወቀው ልማት የዜጐች ሁሉ መሠረታዊ መብት ነው:: ይህም በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ውስጥ በግልጽ ተመልክቷል:: ድህነት፣ ልማት በአግባቡ ባለመዳረሱ ምክንያት የሚመነጭ እንደመሆኑ፣ አክሽን ኤድ ይህንን ሁኔታ የዜጐችን መሠረታዊ መብት እንደማንደል አድርጐ ነው የሚያየው:: ከዚህ አንፃር መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድህነትን በመቀነስ፣ ብሎም በማጥፋት ትልቅ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ አክሽን ኤድ በጥብቅ ያምናል::

ከድሆች ጋር ለመሥራት የድህነትን መንስኤዎች በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል:: ድሆች ስለድህነት ያላቸውን ግንዛቤና አመለካከትም መረዳት ያስፈልጋል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሕብረተሰቡ ጋር በቅርብ የሚሠሩ እንደመሆናቸው መጠን፣ ለመንግሥት ማካፈል የሚችሏቸው ብዙ ልምዶች እንዳሏቸው ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት ከመያዶች ጋር ምክክር ማድረግ፣ ውጤታማ የሆነ ፖሊሲ ለማዘጋጀት እንደሚያስችል የአክሽን ኤድ እምነት ነው:: ለመሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስንል እነማንን ማለታችን ነው? ይህ ጉዳይ በሕግ አወጣጥና በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት አንዳንዴ ሲያደናግር ይታያል:: እድርንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አንድ ላይ የማየት ሁኔታ አለ:: የሕብረት ሥራ ማህበራትንና የሙያ ማህበራትንም ከመያዶች ጋር አንድ ላይ የማየት ሁኔታ አለ:: እና ይህንን ለመለየት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምንድናቸው? ምን ዓይነት ዐበይት ባሕሪያት አላቸው? የሚለውን

CCRDA

ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለሁ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አራት ዋና ዋና ባሕሪያት አሏቸው። አንደኛ መያዶች የተመሠረቱት ፈቃደኝነትን መሠረት በማድረግ ነው። ነፃና ገለልተኛም ናቸው። መያዶች በሀገሪቱ ሕግ የሚንቀሳቀሱ ሆነው፣ አሠራራቸውን በተመለከተ የራሳቸው የሆነ የሥነ ምግባር መመሪያ አላቸው። ይህ የሥነ ምግባር መመሪያም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አሠራር የሚገዛ ነው።

መያዶች ለትርፍ የማይሠሩ ናቸው። ወደ ንግድ ሥራ ገብተው ለትርፍ አይሠሩም። ዓላማቸው የሕብረተሰቡን ችግሮች ማንፀባረቅና ለችግሮች መፍትሔ ማስገኘት ነው። የገንዘብ ምንጭ ቢኖራቸውም፣ ያ የሚያገኙት ገንዘብ ለሕብረተሰብ በሚጠቅም መልኩ ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውል ነው።

ሌላው የመያዶች ዓላማና እሴት ራሳቸውን ማገልገል አይደለም። ስለሆነም፣ ከእነኚህ አራት መሠረታዊ ጉዳዮች ከተነሳን መያዶች ከእድር፣ ከሕብረት ሥራ ማህበራትና ከሙያ ማህበራት የሚለዩበት ሁኔታ ግልጽ ነው። ስለዚህ፣ ሕግ በሚወጣበት ጊዜ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በሚመለከት የሚወጣ ሕግና ሌሎች ማህበራትን በሚመለከት የሚወጣ ሕግ የተለያየ መልክ ሊኖረው ይገባል።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ዋና ዋና ሥራዎች ምንድናቸው? እነኚህን በአምስት ዋና ዋና ጉዳዮች ከፍለን ማየት እንችላለን። ከታሪካዊ አመጣጣቸው ጀምረን ስንመለከት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ ይሳተፋሉ። ሀብትን በማሰባሰብ ሥራ ላይ ይሰማራሉ። በምርምርና ፈጠራ ሥራ ላይ ይሰማራሉ። የሰው ኃይል አቅምን በማሳደግ ሥራ ላይ ይሰማራሉ። ትምህርትና ሥነ መንግሥትን እንዲሁም፣ ሥነ ሕግን በተመለከተ የሥራ ድርሻ አላቸው። መያዶች የለውጥ ኃይሎችም ናቸው። የልማት አጋሮችም ናቸው።

ወደ ዓለም አቀፍ ሁኔታ በምንመጣበት ጊዜ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ምን ዓይነት ገፅታ አላቸው? ምን ዓይነት ሚናስ አላቸው? የሚለውን ለመቃኘት እሞክራለሁ። ይህም የአገራችንን ሁኔታ፣ ማለትም እኛ ያለንበትን ደረጃ በመጠኑም ቢሆን ሊያሳየን ይችላል የሚል እምነት ስላለኝ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ስናይ፣ ለምሳሌ እንግሊዝ ውስጥ ወደ 500ሺህ የሚጠጉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። እነኚህም ድርጅቶች በዓመት በአማካይ እስከ 17 ቢሊየን ፓውንድ የሚያንቀሳቅሱ ናቸው። ወደ አፍሪካ ስንመጣ ደግሞ፣ ዚምባብዌ ውስጥ ወደ 800 የሚጠጉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። እነኚህም ባለን መረጃ መሠረት፣ ከ300 እስከ 400 ሚሊዮን ዶላር የሚያንቀሳቅሱ ናቸው። ስሪላንካ ውስጥ ያለ አንድ መንግሥታዊ

CCRDA

ያልሆነ ድርጅት፣ 9ሺህ የልማት ሠራተኞች አሉት። 41ሺ በቀበሌ ደረጃ የሚሠሩ ሠራተኞች አሉት። 10ሺህ መንደሮች ውስጥ ይሠራል። ብንግላዴሽ ውስጥ ግራሚን ባንክ የሚባለው ለድሆች ብድር አቅራቢ ድርጅት፣ ከተለያዩ 12ሺህ ተቋማት ጋር ይሠራል። 85ሺህ መንደሮች ውስጥ የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞችን ዘርግቶ ይሠራል። ይሄም አገሪቱ ውስጥ ካሉ መንደሮች 50 ከመቶ የሚሆነውን የሚሸፍን ነው።



እዚህ አቅርባችን ኡጋንዳ ውስጥ ከአንድ ሺህ በላይ መያዶች አሉ። ከእነኚህ ውስጥ 20ዎቹ ዓለም አቀፍ መያዶች ናቸው። ሌሎቹ በሙሉ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው። አንድ የተባበሩት መንግሥታት ሪፖርት እንዳመለከተው፣ በዓለም ውስጥ ያሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአጠቃላይ 250 ሚሊዮን ከሚሆኑ በድህነት ከሚማቅቁ ሕዝቦች ጋር ግንኙነት አላቸው። ይህም መያዶች በዓለም ውስጥ ሕይወታቸውን በድህነት ከሚመሩት ውስጥ 20 ከመቶው የሚሆኑትን እንደሚያገለግሉ የሚያሳይ ነው።

በሌሎች አገሮች፣ መንግሥታት መያዶችን የልማት አጋሮች አድርገው የሚያዩ በመሆናቸው፣ ቁጥራቸው እጅግ በርካታ ነው። ይህም በመሆኑ መያዶቹ ለሕብረተሰቡ በርካታ ጥቅም የሚያስገኙ ሥራዎችን እየሠሩ ነው።

ወደ አገራችን ስንመጣ፣ የመያዶች ቁጥር 350 ወይም በዚያ አካባቢ ያለ ነው። ትክክለኛው ቁጥር ምናልባት በውይይታችን ወቅት ይገለጣል። ቀደም ሲል

CRDA

እንደተገለፀው፣ በደቡብ ክልል ውስጥ 89 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሉ። ከእነኚህ 53ቱ አገር በቀል ድርጅቶች መሆናቸው ተገልጿል። እንደሚታወቀው መያዶች በልማት ሥራ እገዛ የሚያደርጉ እንጂ መንግሥትን ወይም ሕዝብን ተክተው የሚሠሩ አይደሉም። እንዲህም ሆኖ በመልካም አስተዳደርና በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ሊሠሩ የሚችሏቸው ብዙ ሥራዎች አሉ። እና ከዚህ አኳያ መንግሥት መያዶችን እንደ አንድ የልማት አጋር አድርጌ ማየት አለበት። በዚህም መሠረት መያዶችን በሚመለከት የሚወጡ መመሪያዎች ይህንን በሚያጠናክር መልኩ መቀረፅ ይኖርባቸዋል።

አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአብዛኛው መሥራት የሚፈልጉት አዲስ አበባ ዙሪያ ነው። ወይም በሌሎች ከተሞች ዙሪያ ነው። ወደ ገጠር ወጣ ብሎ የመሥራት ፍላጐትም የአቅም ችግርም አለ። አክሽን ኤድ ይህንን ሁኔታ እንደ አንድ ትልቅ ተፈታታኝ ችግር አድርጌ ነው የሚያየው። እኛ የምንፈልገው የአገር በቀል ድርጅቶችን አቅም ማሳደግ ነው። ይህም ሆኖ ግን፣ የአቅም ግንባታ ድጋፍ የሚሰጣቸው አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአብዛኛው ተሰባስበውና ትኩረት ሰጥተው የሚሠሩት በከተሞች ዙሪያ ነው። ወደ ገጠር ወጥቶ ለመሥራት የሚፈልጉት ቁጥራቸው አነስተኛ ነው።

ሌላው እንደ አንድ ተፈታታኝ ችግር ሆኖ የሚታየው፣ አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአብዛኛው የሰጋሾችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጥገኞች መሆናቸው ነው። በዚህም እርስ በራሳቸው የእርዳታ ገንዘብ የመሻማት ውድድር ይታይባቸዋል። ይህም በመሆኑ፣ በጋራ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በጋራ ለመወጣት መድረክም ሆነ አጋጣሚን ከማመቻቸት አኳያ እስካሁን የታየው ጥረት በጣም ዝቅተኛ ነው።

እንደ አመቺ ዕድል ሆኖ የሚታየው፣ በደቡብ ኢትዮጵያ በክልል ደረጃ የመያዶችን አዎንታዊ ገፅታ በማየት፣ አመቺ የሥራ ሁኔታን ለማጠናከር መያዶችን የሚመለከት መመሪያ መዘጋጀቱ ነው።

ያልተማከለ አሠራር እንዲኖር የሚደረገው ጥረትም ሌላው እንደ አመቺ ዕድል የሚታይ ነው። እስካሁን እንደሚታየው ያልተማከለ አሠራር ሂደት በክልል ደረጃ የቆመ ነው የሚመስለው። ዳሩ ግን ይህ አሠራር እስከ ወረዳዎች ድረስ መዝለቅ ይኖርበታል። መንግሥት በዚህ በኩል የሚገፋበት ከሆነ፣ ሕብረተሰቡ የራሱን ችግር አውቆ በራሱ የሚያቃልልበትንና ራሱን የሚመራበትን ሁኔታ ስለሚያመቻች፣ ይህ በልማቱ ሥራ ለሚሳተፉ ወገኖች ሁሉ አመቺ ዕድል ሆኖ የሚታይ ነው።

CGRDA

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚናቸውን በትክክል እንዲጫወቱ ለማስቻል፣ መልካም አስተዳደር መኖር አለበት። ትክክለኛ የሆነ የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት እስከታች ድረስ መውረድ አለበት። ይህም መያዶችንም መንግሥትንም ለሕዝብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል። ለሕዝብ ተጠያቂነት ሲኖር ሕዝቡ ለምሳሌ፣ የመንግሥት የወረዳ በጀት ምን ያህል ነው? የአንድ መያድ የዓመት በጀቱ ምን ያህል ነው? ብሎ እንዲጠይቅና ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ ያስችለዋል። በመንግሥትና በሕዝብ መካከል፣ በመያዶችና በልማት ፕሮጀክቶች ተጠቃሚዎች መካከል ግልጽነት ሲኖር ጠንካራና የሰመረ ግንኙነት ይፈጠራል።

እንግዲህ በዚህ መድረክ ተጠቅሜ ባቀረብኩት ጽሁፍ ላይ ዋና ዋና ነጥቦችን ለመግለጽ ምክሬያለሁ። የቀሩ ነጥቦች ካሉ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ ለማብራራት እሞክራለሁ። በጣም አመሰግናለሁ።

አወያዩ አቶ ፍቅሩ አበበ፣ አቶ ይጥና ተካልኝን አመስግነው፣ ለመጀመሪያው ቀን የፓነል ውይይት የመጨረሻው ተናጋሪ የሆኑትን አቶ ዘሪሁን በየነን ዝግጅታቸውን እንዲያቀርቡ ጋበዙ። የአቶ ዘሪሁን የውይይት መነሻ ጽሁፍ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው።

2.1.4 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በደቡብ ክልል ልማት ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ

የእኔ ጽሁፍ በመጀመሪያ፣ መያዶች በደቡብ ክልል ልማት ያላቸውን ሚናና የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ይቃኛል። ከዚያም በልማቱ ሥራ መያዶችን ያጋጠሙ ችግሮችንና አመቺ ዕድሎችን ይጠቃቅሳል። ይሁን እንጂ መያዶች ያጋጠሟቸውን ችግሮች የምገልጸው በወርልድ ቪዥን የተሠሩ ሥራዎች ውጤቶችንና ያጋጠሙ ችግሮችን እንደምሳሌ አድርጌ በማቅረብ ነው።

ወርልድ ቪዥን ወደ ደቡብ ክልል የገባው እ.ኤ.አ. በ1984 ነው። ከዚያ ቀደም ብሎ ግን ደቡብ አሞ በአሞራቴ አካባቢ አነስተኛ የዕለት እርዳታና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎችን ሲያካሂድ ቆይቷል። ወላይታ ውስጥ በሰለኖ ወንዝ አካባቢ፣ እንዲሁም በከምባታና ጠምባሮ ዞን አካባቢ በተጠቀሰው ዘመን ማለትም እ.ኤ.አ. በ1984 ሰፊ የዕለት ደራሽ እርዳታ ሥራዎችን አካሂዷል። ከዚያ በኋላ የልማት ፕሮግራሙን ቀጥሎ እስካሁን ድረስ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ይህም የ5 ዓመት የልማት ፕሮግራም ሲሆን፣ አሁን የመጨረሻው ዓመት ላይ ደርሰናል። የልማት ፕሮግራሞቹ ወደ 1.2 ሚሊዮን ሕዝብ ተጠቃሚ የሆነባቸው ናቸው። ስለ ወርልድ ቪዥን ይህን ያህል ከጠቀስኩ፣ ከዚህ በኋላ

CCRDA

ደግሞ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በክልሉ ውስጥ ሲንቀሳቀሱ ምን ያህል የልማት ሥራ አከናውነዋል? ምን ዓይነት አመቺ የሥራ ሁኔታዎች አሉ? የሚለውን ለመዳሰስ እሞክራለሁ::

በዚህ ክልል ውስጥ መያዶች በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ነው ያተኮሩት:: ሥርጭታቸውን ስንመለከት፣ በሦስት ዞኖች ውስጥ ብቻ ነው ያሉት:: በሲዳማ፣ ቀደም ሲል ሰሜን አሞ ተብሎ በሚታወቀው ወላይታና ጋሞጐፋ፣ እንዲሁም በጉራጌ ውስጥ ነው በአብዛኛው የሚሠሩት:: በሌሎቹ አካባቢዎች ያለው ሥርጭት በጣም ጥቂት ነው::

በክልሉ የሚገኙት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እስካሁን ድረስ በተለይ በግብርና፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በአነስተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ በብድር አገልግሎት፣ አነስተኛ ቴክኖሎጂዎችን በማስፋፋት፣ የአቅም ግንባታዎችን በመስጠት፣ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ የውሃ ሀብት ልማት፣ እንዲሁም በሥርዓተጠየታ ጉዳዮች ላይ ፕሮግራሞችን ሲያካሂዱ ቆይተዋል:: የፕሮግራሞቹ ተጠቃሚዎች እንደፕሮግራሙ ዓላማና እንደቦታው ሁኔታ ይለያያሉ:: ገጠሩን በተመለከተ ለምሳሌ፣ የእሣ አጥማጆችን በማደራጀት፣ ገበሬዎችንና አርብቶ አደሮችን በማገዝ፣ የመንግሥት ሠራተኞችን፣ ተማሪዎችን፣ በጠቅላላውም ወጣቶችንና ጐልማሶችን በተለያዩ ፕሮግራሞች በማሳተፍ የልማት ሥራው አጋሮችና መጠነኛ ተጠቃሚዎች ለማድረግ ተሞክሯል:: በከተሞች ውስጥ በፕሮግራሙ የታቀፉ የጐዳና ተዳዳሪዎችን፣ ወላጅ አልባዎችን፣ ሴቶችን፣ የኤች አይ ቪ ተጠቂዎችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የተፈጥሮ አደጋ ተጠቂዎችን ችግሮች ለማቃለል ተሞክሯል::

በአጠቃላይ፣ በደቡብ ክልል በገጠርና በከተማ በተለያዩ የልማት ዘርፎች የተሰማሩት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ እንዲሁም ዘላቂ የሆነ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በመፍጠር ብዙ ሚና ተጫዋተዋል::

መያዶቹ ከ1988 እስከ 1992 ዓ.ም ድረስ በአጠቃላይ ወደ 450 ሚሊዮን ብር የፈጁ የልማት ሥራዎችን ሲያካሂዱ ቆይተዋል:: በእነዚህ በተጠቀሱት ዓመታትና በተጠቀሰው ገንዘብ ወደ 248 ፕሮጀክቶችን ሥራ ሲያካሂዱ መቆየታቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ:: መያዶች ወደ ደቡብ ክልል ሲገቡ፣ የመጀመሪያው ትልቁ ሥራቸው የዕለት ደራሽ እርዳታ ማቅረብ ነበር:: በዚያ ወቅት በተለይ የኪንዶ ኮሻ፣ የወላይታ አካባቢ፣ የሰሜን አሞና ሌሎችም በርካታ ቦታዎች በድርቅ ተመትተው ነበር:: ስለሆነም የዕለት ዕርዳታ ሥራዎችንና አጣዳፊ የእርዳታ ሥራዎችን ለመሥራት ተሞክሯል::

CCRDA

በግብርና መስክ፣ የተለያዩ የግብርና ሥራዎች ሲካሄዱ ቀይተዋል። የእርሻ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ አነስተኛ የመስኖ ልማትን በማስፋፋት፣ የግብይት ዘዴዎችን በማጠናከር፣ በልማት ሥራ የሕዝብ ተሳትፎን በማሳደግ፣ የእንስሳት እርባታ ዘዴን በማሻሻል፣ የሰብልና የእንስሳት በሽታን በመቆጣጠር አያሌ ሥራዎችን ለመሥራት ተሞክሯል። ወርልድ ቪዥን በሚሠራበት አካባቢ፣ ለምሳሌ በአሞ ሸለቆና በቃጫ ቢራ ወረዳዎች፣ ከ140 ሄክታር በላይ በመስኖ ለማልማት ተሞክሯል። በዚሁ አካባቢ ምርታማነትን ለማሳደግ በተደረገው ጥረት በሄክታር 10 ኩንታል የነበረው የበቆሎ ምርት 25 ኩንታልና ከዚያም በላይ ደርሷል። እንደነዚህ ያሉ የልማት ሥራዎችን በየቦታው ለማካሄድ ተሞክሯል። በእንስሳት ሕክምና በኩል በተለይም የገንዲ በሽታ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች አንዳንድ የእንስሳት ሕክምናዎችን፣ እንዲሁም የበሽታ መከላከል ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት ተሞክሯል። በተለይ በሰሜን አሞ ውስጥ፣ አብዛኛው ቦታ የገንዲ ከብት በሽታ የሚያጠቃው ስለነበረ፣ በአሁኑ ጊዜ ያ በሽታ በአብዛኛው ተገቶና ከ60 በመቶ በላይ የበሽታው ሥርጭት ተቀንሶ፣ እንስሳት ያልነበራቸው ቤተሰቦች ብዙ እንስሳት እንዲኖራቸው ተደርጓል። በሌላውም ዘርፍ አያሌ ሥራዎች ተሠርተዋል። ለምሳሌ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን በተመለከተ፣ በየአካባቢው በርካታ የአፈር ጥበቃና የውሃ ሥራዎች ተካሂደዋል። ብዙ ውጤቶችም ተገኝተዋል። ብዙ አካባቢዎች በደን ተሸፍነዋል። ከደን ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ከተገኘው ገቢ የብዙ ቤተሰብ ኑሮ ተሻሽሏል።

ጤናን በተመለከተም እንደዚሁ አያሌ ሥራዎች ተሠርተዋል። የጤና ጣቢያዎችና የጤና ኬላዎችን የመሳሰሉ ተቋማት ተገንብተዋል። እንዲሁም ሥልጠናዎችንና ክትባቶችን በመስጠት የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። በዚህም ምክንያት የጤና ሽፋን ከፍ ብሏል።

የውሃ ሥራዎችን በተመለከተም አያሌ ሥራዎች ተሠርተዋል። ብዙዎች መያዶች በዚህ ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው። የውሃ ጉድጓዶችን በመቆፈር፣ ምንጮችን በማጐልበት ታላላቅ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶችን በመገንባት፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለብዙ ሕዝብ አዳርሰዋል። በዚህም ምክንያት በክልሉ ውስጥ የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በከፍተኛ መጠን አድጓል።

በትምህርት ዘርፍም እንደዚሁ ነው። ብዙ ትምህርት ቤቶች ተሠርተዋል። ድርጅታቸውም ተሟልቷል። ለምሳሌ በሶዶ አካባቢ የትምህርት ሽፋን ከተማሪዎች ምዝገባ አንፃር ከ32 በመቶ ወደ 39 በመቶ አድጓል።

CGRDA

ለሴቶች የተዘጋጁ ከእርሻ ውጭ የሆኑ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችም በስፋተኛ ደረጃ ተስፋፍተዋል። ለሴቶች የሙያ ሥልጠና፣ ብድርና ሌሎች ድጋፎችንም በመስጠት፣ ገቢዎችን ለማሳደግ ተሞክሯል። በዚህ ምክንያት ለምሳሌ፡ጠ በሰሜን አሞ፣ በሶዶና ቦንጎ ወረዳዎች፣ የአነስተኛ ብድር የገንዘብ መጠን ወደ 2.76 ሚሊዮን ብር ደርሷል። ይህ ደግሞ አነስተኛ የብድር ማስፋፊያ ዘዴን በሚመለከት ምን ያህል ሥራ እንደተሠራ ለማሳየት የሚረዳ አንድ ምሳሌ ነው።

የአቅም ግንባታዎችን በተመለከተ፣ በተለያዩ ዘርፎች ሥልጠናዎች ተካሂደዋል። በተለያዩ የልማት ሥራዎች የተሰለፉ ወገኖች የተለያዩ የሙያ ሥልጠናዎችን አግኝተዋል።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የልማት ፕሮጀክት ተጠቃሚዎችን ከዕቅድ አወጣጥ ጀምሮ እስከ አፈጻጸምና ግምገማ ድረስ በማሳተፍ ረገድ ጥሩ ልምድ አግኝተዋል። ለጋሾቻቸውን ጨምሮ ከልማት አጋሮቻቸው ጋር ጥሩ የግንኙነት ሰንሰለት በመዘርጋት በርካታ ልምዶችን ተለዋውጠዋል።

የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአደጋ መከላከል ዘዴዎችን በተመለከተም መያዶች ጥሩ ልምድ አግኝተዋል። በተለይ ተደጋጋሚ ድርቅ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአደጋ መከላከል ዘዴዎችን የሚመለከቱ ሥልጠናዎችን ለአካባቢው ነዋሪዎች ሰጥተዋል። ራሳቸው መያዶችም በዚህ መስክ በቂ ልምድ ቀስመዋል።

በአሁኑ ጊዜ በሁላችንም ዘንድ አሳሳቢ ሆኖ የተገኘው የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ወረርሽኝ ነው። ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ፣ እኛ የምንሠራባቸው አካባቢዎች ለተደጋጋሚ ድርቅ የመጋለጣቸው ሁኔታ ነው። ቀደም ባሉት ዘመናት ድርቅ በየ10 ዓመት ወይም በየ5 ዓመት ነበር የሚከሰተው። አሁን ግን በየዓመቱ እየተከሰተ ነው። ይህ ደግሞ ከሁሉም በላይ አሳሳቢ የሆነና በልማት ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድር ነው።

በሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ፕሮግራም ያለው እንቅስቃሴም በጣም ውሱን ነው። ከዘላቂ ልማት ፕሮግራሞቻችንም ውስጥ አንዳንዶቹ ቀጣይነታቸው አጠራጣሪ ሆኗል። ይህ ሌላው ተፈታታኝ ችግር ነው። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በልማት ፖሊሲ ቀረፃ ላይ ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑም እንደ አንድ ተፈታታኝ ችግር ሊቆጠር የሚችል ነው። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የመያዶች ሠራተኞች በየጊዜው ሥራቸውን የመልቀቅ ሁኔታም አሳሳቢ ችግር ነው። የመንግሥት ሠራተኞች፣ በተለይ በወረዳ ደረጃ ያሉት በየጊዜው መቀያየራቸው ለልማት ሥራ አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። አልፎ አልፎ የሚታየው ችግር ደግሞ፣ ከመንግሥት በኩል የሚታየው የትብብር ማነስ

CCRDA

ነው:: በተለይም አንዳንድ የሙያ ድጋፍ በምንጠይቅበት ጊዜ ከአንዳንድ ድርጅቶች የሚደረግልን ትብብር አነስተኛ ነው:: በተለይ ቅድም እንደተጠቀሰው፣ የክትትልና የግምገማው ሥርዓት ጠንካራና የተሟላ ባለመሆኑ፣ መያዶች አብዛኛውን ጊዜ የሚገመገሙት በጅምላ ነው:: አንዳንዴም በዘፈቀደ አሠራር ነው:: ስለሆነም የክልሉ የክትትልና ግምገማ የሥራ ክፍል በሚገባ አለመጠናከር ለመያዶች አንድ ተፈታታኝ ችግር ነው::

በወረቀት ላይ በጽሁፍ ከሚወጡ መመሪያዎች ይልቅ፣ በስብሰባ ላይ የሚነገሩት ናቸው የሚበልጡት:: እና ሞያዶች አንዳንድ ሥራዎቻቸውን ለማካሄድ ከመመሪያዎች ይልቅ በሰዎች ወይም በቃል በሚነገሩ ነገሮች ብቻ እንዲመሩ ይደረጋል:: ይህንንም እንደ አንድ ተፈታታኝ ችግር ነው የምቆጥረው:: አንዳንዴ በወረዳ ደረጃ የሚዘጋጁ የልማት ዕቅዶች አቅምን ያላገናዘቡ ስለሚሆኑ፣ ወረዳዎች መያዶችን አንዳንድ ሶርዳታዎች በመጠየቅና ተዕዕኖ በማድረግ፣ በመካሄድ ላይ ያሉ የልማት ፕሮግራሞቻቸውን እንዲለውጡ የሚያደርጉባቸው ጊዜዎች አያሌዎች ናቸው::

በደቡብ ክልል ለመያዶች የልማት ሥራ አመቺ የሆኑ ዕድሎችም አሉ:: እነዚህም፣ የጋራ ዓላማ መኖር፣ አንድ ዓይነት የልማት ስትራቴጂ መኖር፣ የመንግሥት ድርጅቶች፣ ወይም የመያዶች መዋቅር ታች ድረስ መውረድ ናቸው::

በአሠራር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የጋራ ውይይት አለ:: በጋራ የመነጋገር ፈቃደኝነትም አለ:: ይሄ ጥሩ ጅምር ነው:: መቀጠል ያለበትም ነገር ነው:: አንዱ ከአንዱ የመማርና የሥራ ድግግሞሽ እንዳይኖር የማድረግ ጥረትም ይካሄዳል:: በዚህ በኩል የፕላን ቢሮው ትልቅ አስተዋፅኦ አለው:: ይህ ራሱ አንድ አመቺ ዕድል ነው:: ክልሉ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሀብትም እንደአንድ ትልቅ አመቺ ዕድል አድርገን ነው የምንቆጥረው::

በክልሉ ውስጥ የሚቀረጹት የልማት ፕሮግራሞች ሁሉ በሕዝቡ አንገብጋቢ ፍላጐቶች ላይ የሚመሠረቱ እንዲሆኑ ያስፈልጋል:: መያዶች ምን መሥራት እንዳለባቸውና ምን መሥራት እንደሌለባቸው የሚያሳይ ግልጽ የሆነ መመሪያም ያስፈልጋል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በልማት ሥራቸው ያስገኙትን ለውጥ ለመለካት ሰፋ ያለ ጥናትና የተጠናከረ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት ያስፈልጋል:: አመቺ የሥራ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በየጊዜው የሚዘጋጅ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የውይይት ፎረም መዘጋጀት አለበት:: በአመቺ ዕድሎችና ተፈታታኝ ችግሮች ዙሪያ ብዙ ማለት ይቻላል:: ሆኖም በጽሁፌ ላይ ያልተነሱ ጉዳዮችን በውይይት ሰዓት እናነሳለን ብዬ አምናለሁ:: ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ::

CCRDA

2.1.5 አጠቃላይ ውይይት

አወያዩ አቶ ፍቅሩ አበበ፣ አቶ ዘሪሁን በየነ ላቀረቡት ሰፊ የውይይት መነሻ ጽሁፍ አመስግነው፣ የፎረሙ ተሳታፊዎች ቀደም ሲል በቀረቡት ጽሁፎች ላይ ተመርኩዘው ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን እንዲያቀርቡ ጋበዙ::

ተሳታፊ:- በቅድሚያ አራቱንም የፓነል አቅራቢዎች ለማመስገን እወዳለሁ:: ሁለም ባቀረቧቸው የውይይት መነሻ ጽሁፎች ላይ ድህነትን ለመቅረፍ በተለያዩ ቦታዎችና በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥረቶችን ገልጸውልናል:: የእኔ አንዱ ጥያቄ፣ ዓለም አቀፍ ነፃ የገበያ ሥርዓትን ወይም ግሎባላይዜሽንን የሚመለከት ነው:: እንደምንሰማው ከሆነ በዚህ የገበያ ሥርዓት ድሃ አገሮች ከበለፀጉ አገሮች ጋር መወዳደር ስለማይችሉ፣ ከመድረኩ ተገፍተው በመውጣት የበለጠ ወደ ድህነት አዘቅት ውስጥ የሚገቡ መስሎ እየታየ ነው:: ታዲያ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ዓይነት አቋም ይኖራቸዋል? ምን ማድረግስ ይገባቸዋል?

ፓነል አቅራቢ:-በመሠረቱ ግሎባላይዜሽን በጣም ትልቅ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ ሁላችንንም ሊያወያይ የሚገባ ጉዳይ ነው:: በርካታ መንግሥታትም በራሳቸው ደረጃ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ አድርገው እያዩት ነው:: በአጠቃላይ መልኩ ስናይ ግሎባላይዜሽን ጠቃሚና ጉጂ ጐኖች ይኖሩታል:: አንደኛውን ወገን ጐድቶ ሌላውን ሊጠቅም ይችላል:: የግሎባላይዜሽን አንደኛው መገለጫው በምርት ልውውጥ ሂደት ነው:: በጣም ቀልጣፋ በሆነ ዘዴና በአነስተኛ ወጪ ብዙ ማምረት የሚችሉ ሀገሮች ምርታቸውን ወደ ታዳጊ አገሮች በማምጣት፣ እነዚህ ታዳጊ አገሮች ውስጥ ያለው ምርት ገበያ እንዳያገኝ የሚያደርጉበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው:: ለዚህም ሀገራችን ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል:: ገበያው ሁሉ ከሌሎች አገሮች በሚመጡ ምርቶች እየተጥለቀለቀ፣ ፋብሪካዎቻችን ብዙ ምርት ማምረት አልቻሉም:: በዚህም ምክንያት ሠራተኞች እየተቀነሱ ነው:: ከሥራ እየተባረሩ ወደ ድህነት እየሄዱ ነው:: የጫማና የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ሠራተኞችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል:: ይሄ አንዱ የግሎባላይዜሽን ተፅዕኖ ወይም ውጤት ነው::

ሌላው የግሎባላይዜሽን መገለጫ ኢንፎርሜሽን ነው:: ኢንፎርሜሽንን ወይም መረጃን በተመለከተ አሁን ዓለም አንድ ትንሽ መንደር የሆነችበት ጊዜ ነው::

CCRDA

እዚህ ሆነን ከአሜሪካ ጋር በሰከንድ ወይም በደቂቃ ግንኙነት ማድረግ እንችላለን። ከዚህ አኳያ የምርት ልውውጥን በተመለከተ፣ በተለይ ትልልቅ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኢንፎርሜሽን ተጠቅመው ሁሉንም ነገር በቁጥጥር ሥር የማድረግ ችሎታ አላቸው። ቴክኖሎጂን በመጠቀምም ራሳቸውን ጠቅመው ሌሎችን ድሆችና ጥገኞች ሊያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ በህንድ አገር ገበሬዎች የሚያመርቱት የተለየ የሩዝ ዘር ነበር። ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ያንን የሩዝ ዘር በጄኔቲክ ምህንድስና ተጠቅመው ከአንድ ጊዜ በላይ ምርት እንዳይሰጥ አድርገውታል። ይህ አካሄድ ቴክኖሎጂው በሌላቸው አዳጊ ሀገሮች ላይ ምን ዓይነት ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ለመገመት የሚከብድ አይሆንም።



ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የዓለም ባንክንና የዓለም የገንዘብ ድርጅትን /አይ.ኤም.ኤፍ./ ከመሳሰሉት የፋይናንስ ተቋማት እንዲሁም ከዓለም የንግድ ድርጅት ጋር በመቀራረብ፣ የአድቮኬሲ ሥራ በመሥራትና ተፅዕኖ በማድረግ ላይ ናቸው። ዋና ትኩረታቸውም ግሎባላይዜሽን በመያዶችና በመንግሥታት ትብብር ላይ ሊፈጥር በሚችለው ተፅዕኖ ላይ ነው።

ተሳታፊ፡- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከዕድሮች ስለሚለዩበት ሁኔታ በቀረቡት ነጥቦች ላይ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተመሠረቱት በፈቃደኝነት ነው ይላል። እኔ እንደሚመስለኝ ግን ዕድሮችም ያለማንም ተፅዕኖ በራሳቸው በአባላቱ ፈቃደኝነት ችግራቸውን ለመፍታት የሚቋቋሙ ናቸው። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሥነ ምግባር መመሪያ አላቸው።

ዕድሮችም ደግሞ የራሳቸው ውስጠ ደንብ አላቸው። ዕድሮች ለትርፍ ሳይሆን የጋራ ችግራቸውን ለመፍታት ብለው የሚሰባሰቡ ናቸው። ዓላማቸውም ግለሰቦችን ሳይሆን ማህበረሰቡን ለማገልገል ነው። እና በፓነል አቅራቢው የቀረቡት ነጥቦች፣ በመያዶችና በዕድሮች ዓላማ መካከል እንደመለያ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ ወይ?

ፓነል አቅራቢ፡- ይህንን ሁኔታ በጽሁፌ ላይ ዘርዘር አድርጌ የገለጽኩት ይመስለኛል። አሁን ከጊዜ አንፃር አጠር አድርጌ ለመመለስ እሞክራለሁ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን «ራሳቸውን ለመጥቀም ወይም ለማገልገል ያልተቋቋሙ» የሚል የዓላማ መግለጫ አለ። ዕድርን የሚያቋቁሙት የአንድ ሠፈር ወይም አካባቢ ነዋሪዎች ናቸው። ዓላማቸውም አንዱ ሌላውን ለማገልገል ብቻ ሳይሆን ለመረዳዳት ነው። አባላቱ ግዴታ አለባቸው። መዋጮአቸውን መክፈል፣ በቀብር ላይ መገኘትና በቅርብ ተገኝቶ ማስተዛዘን አለባቸው። ያልሰጡትን መቀበል ስለማይችሉ፣ ይህንን ማድረግ አለባቸው። ደንብ የወጣለት ውለታ መመላለስ ማለት ነው። በእርግጥ ማህበራዊ ተደጋጋፊነትን በማጠናከር ረገድ ዕድሮች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። የመያዶች አጋር ሆነው ሊሠሩ የሚችሉም ናቸው። ዳሩ ግን ሁለቱም የሚቋቋሙበት ዓላማ የተለያየ ነው።

ተሳታፊ፡- ዕድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ። በቅድሚያ እራቱም የፓነል አቅራቢዎች ለውይይት መነሻ ያቀረቡትን ጥናታዊ ጽሁፍ በጣም ነው የማደንቀው። የእኔ ጥያቄ በሌሎች መድረኮችም ተደጋግሞ የቀረበ ጥያቄ ነው። ይሁን እንጂ አጥጋቢ መልስ ያላገኘ ስለመሰለኝ፣ በድጋሜ ላነሳው ወድጄአለሁ። ጥያቄዬ የመያዶችን ሚዛናዊ ያልሆነ ሥርጭት የሚመለከት ነው። መያዶች በልማት አጋርነት የሚያካሂዷቸውን ሥራዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም ራቅ ባሉ አካባቢዎች ለማዳረስ ያላስቻላቸው ችግር ምንድነው?

ፓነል አቅራቢ፡-በሀገራችን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሥርጭትን በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ አጠር ብሎ የቀረበና እጅግ ጠቃሚ የሆነ ጥያቄ ነው። መልሱ ግን ሰፋ ያለ ማብራሪያ መስጠትን የሚጠይቅ ነው። የመያዶችን ሥርጭት በተመለከተ፣ እያንዳንዱ መያድ የራሱ የሆነ ፖሊሲና አሠራር ሊኖረው ይችላል የሚል እምነት አለኝ። ለምሳሌ እኔ የመጣሁበት ድርጅት አክሽን ኤድ፣ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀሰው አገር በቀል ከሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ነው። ድርጅቱ ካሉት 13 የረዥም ጊዜ የልማት ፕሮግራሞች ውስጥ ሁለቱን ብቻ ነው ራሱ በቀጥታ የሚያካሂዳቸው።

CCRDA

እነዚህም በዳውሮ ዞን የሚገኘው የዋካው ፕሮግራምና በስልጢ ዞን የለው የዳሎቻ የልማት ፕሮግራም ናቸው። ሌሎቹን 11 ፕሮግራሞች አገር በቀል ከሆኑ መያዶች ጋር ሆኖ ነው የሚያካሂደው። አክሽን ኤድ ቀደም ሲል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያልገቡባቸውን ቦታዎችም እየመረጠ በመግባት ይሠራል። በዳውሮ ዞንና በዳሎቻ የልማት ፕሮግራሞችን የጀመረው የመያዶች ስርጭትን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በአሁኑ ሰዓት የም ውስጥ የልማት ፕሮግራም ለማካሄድ ጥረት አድርገናል። የም አንድም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ያልገባበት አካባቢ ነው። እንግዲህ የመያዶችን ሥርጭት በሚመለከት በአክሽን ኤድ በኩል የተደረገው መጠነኛ ጥረት ይህንን ይመስላል። ሌሎች ተናጋሪዎች ተጨማሪ መልስ ይሰጡበታል ብዬ አምናለሁ።

ሌላ የፓነል አትራቢ፦ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሥርጭትን በሚመለከት በየመድረኩ ለሚነሱ ጥያቄዎች አጠቃላይ የሆነ ማንዛቤ የመስጠት ሙከራ ሲደረግ ቆይቷል። ዳሩ ግን የመልስ አሰጣጡ ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ እየሆነ ጥያቄው በተደጋጋሚ ሲቀርብ ይታያል። አብዛኛውን ጊዜም፣



መያዶች እንደ መንገድ የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች ያላቸውንና በቀላሉ ሊደረስባቸው የሚችሉ አካባቢዎችን ይመርጣሉ የሚል አስተያየት አለ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ መያዶች የመንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች የአገልግሎት መዋቅሮች በሌሉባቸው አካባቢዎች የልማት ፕሮጀክቶችን በማካሄድ እገዛ ሊያደርጉ የሚታይበት ሁኔታ አለ። ተደጋግሞ እንደሚነገረውም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመንግሥትንና የሕዝቡን ጥረት የሚያግዙ እንጂ እነሱን

ተክተው የሚሠሩ አይደሉም። መያዶች የልማት ፕሮግራም የሚያካሂዱባቸው አካባቢዎች ወይም የፕሮግራሞቹ ዓይነት በአንድና ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ይወሰናል። ለሁሉም ደግሞ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ማገናዘብ አስፈላጊ ይሆናል። በሀገራችን በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የገጠር መንደሮች አሉ። የሕዝቡ የአሠፋፈር ሁኔታም የተበታተነ ነው። ውጤታማ ለሆነ የልማት ሥራ አያመችም። ዳሩ ግን፣ አሠፋፈሩ ለልማት አያመችም ተብሎ ሕዝቡ ከልማት ተገልሎ ይቅር አይባልም። ምክንያቱም የመያዶች ዋና ዓላማ ከልማት ለተረሱ ወገኖች እገዛ ማድረግ ነው። ከድሆች ጋር ሠርቶ ድህነትን ማስወገድ ነው። እንዲያም ሆኖ፣ በገጠር የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ የሚሠሩ መያዶች፣ ለምሳሌ የምንጭ ማጐልበት ሥራ የሚሠሩ ከሆነ፣ በአካባቢው ምንጮች መኖር አለባቸው። የጥልቅ ጉድጓድ የመጠጥ ውሃ ቁፋሮ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ብዙዎች የሚመርጡት የእጅ ጉድጓድ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶችን ማካሄድ ይሆናል። ስለሆነም፣ ብዙዎች በእጅ ጉድጓድ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ላይ ይሰማሩና የሥራ ድግግሞሽ የሚፈጠርበት ሁኔታ ይኖራል። የመያዶችንም ስርጭት ይወስናል። በገጠር ልማት ፅንሰ ሃሳብ ወይም በመርህ ደረጃ፣ ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ተጠቃሚው ሕዝብ ቅድሚያ በሚሰጠው ችግር ላይ ተመሥርቶ መቀረፅ አለበት። ስለሆነም፣ አንድን የልማት ፕሮጀክት የሚያቅዱ ድርጅቶች ይህንን መርህ እንዲከተሉ የግድ ይላቸዋል። ዳሩ ግን፣ ይህ የማይሠራበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል። አንዳንዴ የለጋሹ ፍላጐት ልቆ የሚታይበትና ተፅዕኖ የሚያሳድርበት ሁኔታ ይኖራል። ይህ ሲሆን ደግሞ፣ «ከባዱ እጅ ትንሽ ነገር ይሻላልሜ በሚል እምነት፣ ትንሽም አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚረዳ ከሆነ፣ ለጋሹ የመረጠውን የልማት ፕሮጀክት ማካሄድ አይጐዳም እየተባለ የሚገባበት ሁኔታ ይኖራል። ይህ ደግሞ በቦታና በሥራ ዓይነት ምርጫ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። የመያዶች ቁጥር ማነስም ሥርጭታቸውን በዚያው ልክ ይወስነዋል። የመያዶችን ሥርጭት በሚመለከት አንድ ራሱን የቻለ ዓውደ ጥናት አዘጋጅቶ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ቢወያዩበትና ቢመካከሩበት፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ተደጋግሞ ለሚነሳው ጥያቄ በቂ መልስ ማስገኘት ይቻላል ብዬ አምናለሁ። አመሰግናለሁ።

ፓነል አቅራቢ /ደቡብ ክልል/- እኔ ተጨማሪ መልስ ለመስጠት የምሞክረው የመያዶችን ሥርጭት በሚመለከት ነው። የሥርጭቱ ችግር መነሻው ምንድነው? ቀደም ሲል በሌላው ፓነል አቅራቢ እንደተገለጸው በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። እንደሚታወቀው አብዛኞቹ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

CCRDA

በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች እንዳደረጉት ሁሉ፣ ደቡብ ክልል የገቡት የድርቅ አደጋ በተከሰቱባቸው ወቅቶች የዕለት ደራሽ ያእርዳታ ሥራዎችን ለማካሄድ ነው። ከዚያም ወደ ልማት ሥራ ሲሸጋገሩ፣ አብዛኞቹ እዚያው የዕለት ደራሽ እርዳታ ሲያካሂዱባቸው በነበሩት አካባቢዎች ቀጠሉ። ሌሎች ደግሞ፣ መንግሥት ሳያውቅ በክልሉ ውስጥ ሥራ ጀምረው የፕሮጀክት ውል ለመፈራረም ሲመጡ ብቻ ስለታዩ፣ እንሥራ ብለው ከመጡ ምን ይደረግ ተብለው እንደምንም ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ተደረገ።

በክልላችን 104 ወረዳዎች አሉ። በእኛ በኩል እስካሁን ድረስ አንድን መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ ጌድኦ ውስጥ በሚገኝ አንድ ወረዳ መሥራት ትችላለህ ወይም ኪንዶ ኮቻ ውስጥ ወይም ወላይታ ውስጥ በሚገኝ ወረዳ ትሠራለህ ብለን ምርጫ ውስጥ ለማስገባት፣ የዚያን አካባቢ ችግር በውል ለይተን ያሳየንበት ጊዜ የለም። ይህንን አላሟላንም። ስለሆነም፣ መያዶች ቦታውን ራሳቸው ይመርጡና፣ የፕሮጀክት ውል ሰነዳቸውን መንግሥት ተቀብሎ እንድንፈራረም ነው የሚጠይቁን። በቅድሚያ የሚደረግ ምክክር የለም። እና ለመያዶች ስርጭት መዛባት ዋና ዋና ከሚባሉት ምክንያቶች ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው። አዲስ ባዘጋጀነው መያዶችን የሚመለከት መመሪያ፣ የፕሮጀክቱ ባህሪ የሚገድበን ካልሆነ በስተቀር፣ በአንድ አካባቢ አንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በአንድ ሥፍራ የሚቆይበት የልማት ዘመን 5 ዓመት ነው። ከ5 ዓመት በኋላ ፕሮጀክቱን አስረክቦ፣ በሌላ አካባቢ አዲስ ፕሮጀክት ለመጀመር ራሱን ማዘጋጀት አለበት። ለወደፊቱ አንድ መያድ ለመግባት ያሰበበትን አካባቢ ለመንግሥት አቅርቦ፣ በመንግሥት የቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ቦታዎች ዝርዝር ውስጥ ያለ አካባቢ ከሆነ ነው እንዲገባና ሥራውን እንዲጀምር የሚፈቀድለት። በእርግጥ እስካሁን ድረስ በየአካባቢው የሚገኙ መያዶችን ሥርጭታችሁ ተዛብቷልና አንደኛህ ከዚህ ወረዳ ተነስተህ ወደ ሌላ ወረዳ ሂደህ ሥራ ልንል አንችልም። እንደ ልብ ሄዶ መሥራት የማይቻልባቸው ሥፍራዎች ለመሄድም በአብዛኛው በምክክር የሚፈጸም ይሆናል እንጂ ግዴታህ ነው የሚባልበት አይሆንም። ምክክር የመንግሥትንና የመያዶችን አጋርነት ይበልጥ ያጠናክራል ብለን እናምናለን።

ተሳታፊ፡- ብዙ መያዶችና ሌሎች ድርጅቶች የኤች አይ ቪ ኤድስ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። ያም ሆኖ ግን እስካሁን ድረስ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ለውጦች ያመጡ አይመስለኝም። በተለይም የባሕሪ ለውጥ ሊመጣ የቻለ አይመሰለኝም። ይህም የሆነው ሁሉም መያዶች

GCPDA

በተናጠል ስለሚሠሩ ነው ብዬ አምናለሁ። ይህንን በተመለከተ የፓነል አቅራቢዎች ምን አስተያየት አላቸው?

የፓነል አቅራቢ፡-ብዙ መያዶችና ሌሎች ድርጅቶች በኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ላይ ይሠራሉ። የእኛ ቤተክርስቲያን፣ መካነየሱስ እ.ኤ.አ ከ1988 ጀምሮ የኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራም ታካሂዳለች። ይሁን እንጂ በአጭር ጊዜ የታሰበውን የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት አስቸጋሪ ሆኖ ተገኝቷል። የባህሪ ለውጡ ለረዥም ጊዜ ከሚካሄድ ጥረት የሚመጣ ነው። ቀደም ሲል የኤች አይ ቪ ኤድስን የሚመለከት ፖሊሲ አልነበረም። አሁን ግን ፖሊሲው ስለወጣ፣ በፖሊሲው ላይ ተመሥርተን የተቀናጀ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ከሠራን፣ ለውጥ ማምጣት እንችላለን ብዬ አምናለሁ።

ተጨማሪ መልስ ከተሳታፊ፡- ቅድም ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተለይ በጌድኦ የሚካሄደውን ጥረት አስመልክቶ ለተሰነዘረው አስተያየት መልስ ለመስጠት ነው። እኔ ከቫይረሱ ጋር የምኖርና የተስፋ ጐህ ኢትዮጵያ ማህበር የደቡብ ቅርንጫፍ አስተባባሪ ነኝ። የተስፋ ጐህ ኢትዮጵያ ማህበር ደቡብ ቅርንጫፍ፣ በክልላችን ውስጥ የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብና ችግሩ ጐልቶ የሚታይበትን ዲላን በመምረጥ ለፓክት ኢትዮጵያ ፕሮጀክት አዘጋጅቶ አቀረበ። ፓክት ኢትዮጵያም ገንዘብ ሰጥቶን ለማስተማር ወደ ዲላ ሄድን። እዚያም ገብተን፣ ከቫይረሱ ጋር ለምትኖሩ ሰዎች የምክር አገልግሎት እንሰጣለን፣ በጣም ለተቸገራችሁም መጠነኛ የገንዘብ ዕርዳታ እናደርጋለን። ስለዚህ ወደ ማህበራችን መጥታችሁ እንድትመዘገቡ የሚል ማስታወቂያ በከተማው ውስጥ ለጠፍን። ነገር ግን በዚያ ወቅት ከጌድኦ ዞን ማንም ሰው አልመጣልንም። በዚያ አካባቢ በርካታ ፀረ-ኤድስ ክበባት አሉ። እያስተማሩም ነው። ሕብረተሰቡ ግን ራሱን አላነሳሳም። ከቫይረሱ ጋር የምንኖር ሰዎች በየአካባቢው እየተዘዋወርን ትምህርት በመስጠት ላይ እንገኛለን። ትምህርት ከሚሰጥባቸው የመጀመሪያው ጌድኦ ዞን ነው። የእኛ አባላት በየገበያው እየተዘዋወሩ «በእኛ ይብቃ ትውልድ ይዳን» እያሉ ያስተምራሉ። ጥሪያቸውን ያስተጋባሉ። ፓክት ኢትዮጵያ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ 20 ሰዎች እንክብካቤና ድጋፍ ይሰጥልናል። ለማስተማር ሥራው እነዚህ 20 ሰዎች አሉን። ሌሎችም ከአዋሳ እየሄዱ ያስተምራሉ። ፓክት ለ10 ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንዴት እንደሚኖሩና ትምህርቱን እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው የ5 ቀን ሥልጠና ሰጥቶልናል። በደቡብ ክልል ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን አስመልክቶ በተስፋ ጐህ ከፍተኛ ሥራ የተሠራው አዋሳና ጌድኦ ዞን ውስጥ ነው። በዚህ ሥራችን የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ሴክሬታሪያት፣ የክልሉ ጤና ቢሮ ሆስፒታሉ ከፍተኛ እገዛ አድርገውልናል። ህብረተሰቡ ግን ምንም ያህል አልተባበረም። የተለያዩ

CCRDA

አወያዩ አቶ ፍቅሩ አበበ የፓነል አቅራቢዎችንና ተሳታፊዎችን በአዘጋጅ ኮሚቴውና በራሳቸው ስም አመስግነው፣ የፎረሙ ዝግጅት አስተባባሪ አቶ ፀጋዬ ቸርነት አጭር ማጠቃለያ እንዲሰጡ ጋበዙ። አቶ ፀጋዬም የሚከተለውን የማጠቃለያ ንግግር አደረጉ።

ወርቃማ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ የዚህ ፓነል ውይይት ተሳታፊ በመሆናችሁ በፎረሙ አዘጋጅ ኮሚቴ ስም ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን። በተለይ የፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣናት፣ የክልሉ ባለሥልጣናትና በተለያየ የእርከን ደረጃ ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ዛሬ ከእኛ ጋር መሆናቸው ደስታ ይሰጠናል። ከአራት ወይም ከአምስት ዓመት በፊት ከአክሽን ኤይድ ጋር ሆነን፣ መንግሥታዊ የሆኑ ድርጅቶችና የመንግሥት አካላት በአንድ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበን በተወያየንበት ወቅት፣ በውይይቱ ተካፋዮች የነበሩና አሁን በመሀከላችን የማያቸው ሰዎች አሉ። በዚያ ስብሰባ ላይ ግማሽ ቀን፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተወካዮች ስለ መያዶች ያለመታመን ሁኔታ ብቻ ነበር በአብዛኛው የተናገሩት። እንደገና ግማሽ ቀን ደግሞ፣ የመያዶች ተወካዮች በበኩላችን በተለያየ የእርከን ደረጃ ላይ ያሉ የሥራ ኃላፊዎች የሚበድሉንን በደል ስናወራ ነበር የዋልነው። ዛሬ ግን ያ ሁሉ የለም። እና ይሄን ሁኔታ አለማየታችን፣ የወደፊት ራዕያችንን መግለፃችን ራሱ ታላቅ ተስፋ የሚሰጥ ነው። የነፃነት ፋና ወጊ ሆነን፣ ለእነሱ ነፃነት በታገልንላቸው የአፍሪካ አገሮች ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ አገልግሎቶችን ሲሰጡ፣ እኛ ግን የዛሬ 10 ዓመት በ40 መያዶች ብቻ ተወስነን ነበር። ዛሬም 300፣ 350 እያልን እዚያው ላይ ተወስነን ነው የምንገኘው። ቢሆንም የዛሬው ሁኔታ ተስፋ የሚሰጥ ነው። በክልሉ ፕሬዚዳንት በኩል ጠዋት የተነገረው አጋርነትን የማጠናከር ሁኔታና በተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ይህንኑ አመለካከት በማጠናከር የተሰጠው አስተያየት፣ ለመያዶች ተስፋ የሚሰጥ ነው።

በተለይ ክልሉን ወክለው በፎረሙ ላይ የውይይት መነሻ ጽሁፍ ያቀረቡት አቶ ማዕረጉ፣ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ፣ በመንግሥታዊ ድርጅቶች በኩል ያለው ችግር ይህንን ይመስላል፣ በመያዶች በኩል ያለው ችግርም ይህንን ይመስላል፣ በማለት ያቀረቡት አስተያየት፣ መንግሥትና መያዶች ይበልጥ ተቀራርበን በመወያየትና በመመካከር እንደንሠራ የሚያበረታታ ሆኖ አግኝተነዋል።

በሌሎች አገሮች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በርካታ የልማት ሥራዎችን ይሠራሉ። ቁጥራቸውም የዚያኑ ያህል ብዙ ነው። ለምሳሌ፣ በባንግላዴሽ 34 ሺ ትምህርት ቤቶች ያለው አንድ መያድ አለ። 30 ሺህ አስተማሪዎች አላልኩም። 30 ሺህ ተማሪዎችም አላልኩም። 30 ሺህ ትምህርት ቤቶች ያለው አንድ መያድ ነው ያልኩት። ስለዚህ ለእኛም የተመቻቸ ፖሊሲ ከወጣና ያንን ደግሞ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ የምናደርግ ከሆነ፣ ወደእዚያ የማንደርስበት ምክንያት የለም።

CCRDA

በአጋጣሚ እዚህ ካሉ አንድ የፌዴራል መንግሥት የሥራ ኃላፊ ጋር ሆነን አንድ ጊዜ ወደ ፊሊፒንስ ሄደን ነበር። እዚያች ሀገር የመያዶች ምዝገባ ለ50 ዓመት ያገለግላል። ባንግላዴሽም እንዲሁ ምዝገባ የሚያገለግለው ለ5 ዓመት ነው። እዚህ ሀገር ግን ምዝገባችንን በየዓመቱ ማደስ አለብን።

እንዲያውም በደቡብ አፍሪካ፣ ምዝገባ የሚያስፈልገው ከመንግሥት ድጋማ ለማግኘት ብቻ ነው። መያዶች የሚመሩት በሕግ የበላይነት በሚያምኑ፣ ግልጽነት ያለው አሠራር በሚከተሉና ለሕብረተሰቡ ጥቅም በቆሙ አባላት በመሆኑ፣ መንግሥት ከፍተኛ እምነት አለው። በእኛም ሀገር ይሄ ሁኔታ የማይፈጠርበት ምንም ምክንያት አይታየንም። ስለሆነም በአጭር ቀን ይህ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ።

እንደ ሕንድና ባንግላዲሽ በመሳሰሉት አዳጊ ሀገሮች ለመያዶች ከማዕከላዊ መንግሥትም በጀት እየተመደበላቸው ነው ሥራቸውን የሚሠሩት። እና ቅድም ስናነሳ የነበረው የመያዶች ሥርጭት መዛባት ምናልባት ወደፊት በቅንጅት ከሠራን፣ መንግሥት በጀት ከመደበልን፣ እንዲህ ያለ ቦታ ሂዱና ሥሩ ከተባለ፣ ችግሩ ሊቃለል ይችላል ብዬ አምናለሁ። እንደ ኢንዶኔዥያና ታይላንድን በመሳሰሉ ሀገሮችም ማዕከላዊ መንግሥት ገንዘብ እየመደበላቸው ይሠራሉ። ይህ በተለይ በምዕራቡ ዓለም የተለመደ ነው። በምሳሌነት እንደጠቀስናቸው ያሉ አዳጊ ሀገሮችም ቢሆን፣ ማዕከላዊ መንግሥት ተገቢውን ቁጥጥር እያደረገ ገንዘብ እየሰጠ የሚያሠራበት ሁኔታ አለ። ይህንን ሁኔታ በተለያየ የሥራ ኃላፊነት ያለን ሰዎች ለወደፊት ልናየው የሚገባን ነው።

በትርፋማ ሥራ ላይ የመሠማራቱም ጉዳይ እጅግ አስፈላጊና የፖሊሲ ድጋፍ ሊሰጠው የሚገባ ነው። ትልቁ ጥያቄ ከዚህ የተገኘው ገቢ የት ነው የሚውለው? ለሕዝብ ነወይ? የሚለው ብቻ ነው። ራሳችንን የምንጠቅምበት እንዳይሆን ነው ቁጥጥር መደረግ ያለበት። በዚህም በኩል እንግዲህ ብዙ ሥራ ይበጠቅብናል ማለት ነው። ለድሆች አነስተኛ የገንዘብ ብድር በመስጠት ሠርተው እንዲኖሩ የሚያደርገውን ግራሚን ባንክን ብንወስድ፣ ባንግላዴሽ ውስጥ በጣም እጅግ ደሃ የሆኑ ድሆች ሰዎች፣ ብድር ወስደው በሥራ ላይ በማዋል በወቅቱ መመለስ የሚችሉ፣ ታማኝ ተበዳሪዎች መሆናቸውን ያመላከተ ፕሮግራም ነው። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተጠቃሚዎች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ ወደ 99 ከመቶው የተበደሩትን ገንዘብ በወቅቱ መልሰው ይከፍላሉ። ስለዚህ በሌሎች አገሮች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲህ ያለ የሚያስደንቅ ሥራ ሲሠሩ፣ እኛ ለብዙ ሺህ ዓመታት በነፃነት የኖርን፣ ነፃነት ምን እንደሆነና መደጋገፍ ምን እንደሆነ የምናውቅ ሰዎች ደግሞ፣ ከዚህ የተሻለ ድንቅ ሥራ ለመሥራት እንደምንችል ተስፋ አደርጋለሁ። አመሰግናለሁ።

CCRDA

የሁለተኛው ቀን የፓነል ውይይት

ዐቢይ ርዕስ፡- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ

ቀን፣ ታህሣሥ 6 ቀን 1994 ዓ.ም

ጊዜ፣ ከ3:00 - 6:30 /ጠዋት/

የፎረሙ አስተባባሪ፣ አቶ ሉልሰገድ አስፋው

አወያይ፣ አቶ ከበደ አሥራት

የፓነል አቅራቢዎች፣

ወሐሮ ሮማን ተስፋዬ /ከደቡብ ክልል መስተዳድር/

አቶ አህመድ አሊ /ከአክሽን ኤድ/

ዶክተር ሺመልስ ተሐዳዲቅ /አማካሪ ባለሙያ/

አቶ ጌታሁን ታፈሰ /ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ሪሰርች ኢኒስቲትዩት/

አወያዩ አቶ ከበደ አሥራት የፎረሙን ተሳታፊዎችና የፓነል አቅራቢዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ ብለው፣ የዕለቱን የመወያያ ርዕስና የፓነል አቅራቢዎቹን ካስተዋወቁ በኋላ፣ የመጀመሪያውን ተናጋሪ ዶክተር ሺመልስ ተክለዓዲቅን ጋበዙ:: ዶክተር ሺመልስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ነው::

2.2 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- የድህነት ቅነሳ ሰነድና ድህነትን መቋቋም

እኔ የተጠየቅኩት የድህነት ቅነሳ ስልት ፅንሰ ሃሣብን ለመግለፅ ነው:: ግን፣ በመጀመሪያ ደረጃ የድህነት ቅነሳ ስልት ፅንሰ ሃሳብ ምን ያህል እንደሚጠቅመን አይገባኝም:: ፅንሰ ሃሳቡን ለመረዳት ብዙ ሁኔታዎችን መዘርዘር ያስፈልጋል:: ካለው ጊዜና መድረክ አንፃር ግን ይህ ሊደረግ የማይቻል ነገር ነው::

የዚህ ስብሰባ ዓላማ በድህነት ላይ አተኩሮ፣ በአገራችን ይሄ አዲስ የድህነት ቅነሳ ስልት ምን ሊያደርግልን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ መመለሱ የሚሻል ነው የሚመስለኝ:: ይህ እስከሆነ ድረስ፣ ትንሽ ስለድህነት አንዳንድ ነገር ልበልና ከዚያ ወደ ድህነት ቅነሳ ስልቱ እሄዳለሁ::

ድህነት በኢትዮጵያ ሁለት ዓይነት መልክ አለው:: አንደኛው፣ የማይወራውና አጀንዳ ተይዞለት ምንም ውይይት ውስጥ ሲገባ የማላየው፣ ዳሩ ግን እኔ በአገራችን በግልጽ የማየው የመንፈስ ድክመትና ቅኝት ማጣት፣ ከኃላፊነት የመሸሸና ተስፋ የመቁረጥ ዝንባሌ፣ እንዲሁም ፍራቻ የሚነበቡበት የመንፈስ ድህነት ነው:: ይሄ ዓይነቱ ድህነት መንስኤው ምናልባት፣ እንዲያውም እርግጠኛ ነኝ፣ በ1966 የየካቲቱ አብዮትና ከዚያም

ተከትሎ በመደብ ትግል ሰበብ የተካሄደው ግድያ፣ እስራት፣ ስቃይ፣ መፈናቀል፣ ያስከተሉት ድህነት ነው። አሁንም ቢሆን መጠራጠሩ፣ ፍራቻው፣ እርስ በርስ መናቆሩ አላቆመም። አንዳንድ ቦታም ግድያውም ይካሄዳል። እና ገና ከራሳችን ጋር አልታረቅንም። ይሄንን የመንፈስ ድካም ያልኩትን የሚያቆም፣ ሂደትም አላየሁም። ይሄ ታዲያ የእኛ የኢትዮጵያውያን ብቻ የሆነ፣ ራሳችን የፈጠርነው ችግር ነው። የዓለም ባንክም ሆነ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ሊያዩትም፣ ሊያውቁትም አይችሉም። ኢትዮጵያዊ ዜጐች ሁሉ ይህንን ከልብ ብንገነዘብና መፍትሔ ብናስገኝለት ትልቅ ነገር ይመስለኛል።

ሌላው ዓይነት ድህነት በአሃዛዊ ስሌት ወይም በቁጥር የሚታወቀው ነው። የዚህ ዓይነቱ ድህነት በሦስት ዓይነት ይከፈላል። በአንደኛው ዓይነት ድህነት የሚሰቃዩት፣ እራሳቸውን ለመርዳት ምንም አቅም የሌላቸውና በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኙት ናቸው። ይሄ በመሠረቱ በየከተማው የምናያቸውን፣ በልመና የሚተዳደሩ ጠዋሪ ያጡ ሽማግሌዎች እና ባልቴቶች እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን ያካትታል። ይሄ እንግዲህ ከሥርዓቱ ከፍተትም ይሆናል። ወይም ከሕዝብ ድካምም ሊሆን ይችላል። የዚህ ዓይነቱ ድህነት ቁጥሩ እስካሁን በደንብ አይታወቅም። ይህ ሁለተኛው ዓይነት ድህነት ከሥርዓቱ አፈጣጠር የሚመነጭ ነው። አሁን እኛ ካፒታሊዝምን እንከተላለን ነው የሚባለው። ካፒታሊዝም ውስጥ ሁለት ዓይነት የድህነት አፈጣጠርና አመጣጥ አለ። አንደኛው በገጠር ውስጥ እና በግብርናው ሥርዓት ውስጥ ነው። ሁለተኛው በከተሞች ውስጥ ነው።

በገጠሩ ኢኮኖሚ በአንድ ወይም በጥቂት ሰብሎች ላይ ብቻ አተኩረው፣ በቴክኖሎጂና በሳይንሳዊ ዕውቀት በመጠቀም አምርተው ለገበያ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች፣ በበዙ ቁጥር፣ በራሱ ጉልበትና ምናልባትም በእንስሳት ጉልበት ብቻ ተጠቅሞ ለራሱ ኑሮ ብቻ የሚያመርተውን ገበሬ ቦታውን ያጣብቡበታል። ያለውን የገበያ አቅምም ያዳክሙበታል። በዚያን ጊዜ ገበሬው መሬቱን ለቆ ወደ ከተማ ይፈልሳል። ወይም ደግሞ እዚያው ሥራውን አቁሞ ለእነዚህ በስፋት አምርተው ለገበያ ለሚያቀርቡት ባለሀብቶች መቀጠር ይጀምራል። በዚህም እየተገፋ ወደ ድህነት ይገባል።

ይህ ደግሞ በቀጣይ መልኩ የሚፈጥረው ከተማ ውስጥ የሚስፋፋውን የድሃና የሥራ አጥ ቁጥር ነው። ከገጠር የሚፈልሰው፣ የከተማ ኑሮ ተሞክሮ የሚያንሰው፣ አቅምና ልዩ ዓይነት ችሎታ ኖሮት መተዳደር የማይችለው፣ ከተማ ውስጥ እንደሥራ አጥ ይጠራቀማል።

CGRDA



የእኛ አገር የከተማ ነዋሪ ብዛት በዓመት 6 በመቶ ይጨምራል። የሕዝቡ ቁጥር በግምት 3 በመቶ ይጨምራል። ይህም የከተማውን ሁኔታ ያጣብበዋል። የካፒታሊስት ሥርዓት ደግሞ ድህነትን የሚቀንስ ወይም ለድሃው የሚሆን ገቢያን በመፍጠር ረገድ ፍላጐትም፣ ሥርዓታዊ ግፊትም አይኖረውም። የሥርዓቱ ባህሪ ትርፍ ማካበት ነው። ትንሽ ሰው ቁጥር፣ በቴክኖሎጂና ባለው ዕውቀት ተጠቅሞ፣ ለገቢያ ማቅረብ ነው። ገቢያው ውስጥ ገብቶ ገዢ እስካገኘ ድረስ ደግሞ፣ የድሃው የመግዛት አቅም ይሄን ያህል ነው ብሎ ለማስተካከል ምንም ዓይነት መነሻ የለውም። እንዲያውም ፉክክሩ እርስ በርስም፣ ከዓለም ገቢያ ከሚመጣው ጋርም ስለሆነ፣ ከእውነቱ ባለሀብቱ ይሄን ያደርግልን ብሎ መጠየቅ አይቻልም። ሎጂኩም እንደዛ አይሠራም። ይሄ አሁን በሁለቱም በኩል የጠቀስኩት ችግር በሀገራችን ለጊዜው ጅምሯል እንጂ ይሄን ያህል አልተስፋፋም። የአውሮፓ ካፒታሊዝም ሲጀምር በ18ኛውና በ19ኛው መቶ ዘመን፣ እንደዚህ ዓይነት ችግር፣ ረሃብ፣ የበሽታ እልቂት፣ የከተማ ሕዝብ ቁጥር መናርና የሥራ አጥ ብዛት በጣም ግልፅ በሆነ መንገድ የተስፋፋ ነበር። እኛም አገር ወደፊት የሚሆን ነገር ነው። ታዲያ እንግዲህ የድህነት ቅነሳ ስልት እንዴት አድርጐ ሊጠቅመን ይችላል? መጀመሪያ ነገር የድህነት ቅነሳ ስልት ምንድነው? ይሄ ስልት በመሠረቱ የምዕራባዊያን የኢኮኖሚ ቀኝ እጅ የሆኑት የዓለም ባንክና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ፕሮግራም ነው። እኛ አላወጣነውም። ይህንን ሰነድ የተቀበሉት በተለይ ድህነት የሚያጠቃቸው የደቡብ እስያና በአፍሪካም ውስጥ ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር ከሰሃራ በስተደቡብ የሚገኙት አገሮች ናቸው።

CRDA

እነዚህ ሀገሮች ድሆችና የኢኮኖሚ ጥገኞች ናቸው። ብዙ የገንዘብ ብድር ያለባቸውና የብድራቸውን መጠን እንክፈል ቢሉም፣ አሁን ባላቸው ውጥረትና የእድገት ደረጃ መክፈል የማይችሉ ናቸው። የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለሦስተኛው ዓለም ብለው ያመጡት የመዋቅር ማሻሻያ፣ የሕዝብ መሠረታዊ ፍላጐት ለማሟላት የሚል ፕሮግራም ነበራቸው። መጀመሪያ ላይ፣ እነዚህ ሁሉ ተሳክተው የሠሩበት ቦታ ቢኖር በጣም ጥቂት ነው። በአብዛኛው ግን፣ በግልጽ የሚታየውን ማህበራዊ ቀውስ ፈጥረው፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት ተስፋፍቶ፣ ሀገሮቹን ከመቸውም በበለጠ ለናረ ዕዳ ዳርገው ነው የሄዱት። ታዲያ አሁን ይሄ ስልት ለምን የበለጠ ተስፋ አለው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ማንም የሚችል አይመስለኝም። ሆኖም፣ ወደድንም ጠላንም ተቀብለነው ተግባራዊ ለማድረግ እየሞከርን ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ይህ ፕሮግራም የሚቆየው ለአንድ ለሦስት ዓመት ብቻ እንዳይመስላችሁ። እኔ እርግጠኛ ነኝ፣ ብዙ ዓመታት የሚቀጥል ነው የሚመስለኝ። ቢሆንም መቀበላችን የግድ ሆኗልና ምን እናድርግ?

ስልቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲካሄድ ያሉትን ችግሮችና ገደቦች አውቆ፣ በተቻለ መጠን ተፈጻሚነቱና ውጤቱ የተሻለ እንዲሆን መታገሉ ተገቢ ነው። ድህነትን ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት በሕዝብና በሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች ታቅፎና ተደግፎ በመጠኑም ቢሆን ከተከናወነ፣ ለመስተዳድሩ መሻሻል፣ ለኢኮኖሚ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ጥሩ መነሻ ይሆናል።

ዋናው ነገር፣ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ በሚዘጋጅበት ሂደት ውስጥ ትብብሩ መኖር ያለበት በመንግሥት፣ ይህንን ሃሳብ በጠነሰሱት ሁለቱ የገንዘብ ተቋማትና መንግሥታዊ ባልሆነው ማህበረሰብ መካከል ነው። ስለሆነም፣ በአደባባይ ከሚካሄድ ምክክር የሚገኝ መረጃ ያለአንዳች ገደብ ልውውጥ ሊደረግበት ይገባል። ምክክሩን በአደባባይ ያልኩበት ምክንያት፣ ስልቱ ካቀረበው መንደርደሪያ በመነሳት ነው። ይኸውም በመጀመሪያ ሥራው ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት መሆን ይገባዋል፤ የእያንዳንዱ ተግባር ሂደትና ውጤትም መገምገም አለበት በመባሉ ነው። ለዚህ ደግሞ፣ ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆነው ማህበረሰብ የተውጣጣ አገራዊ የሆነ ወይም በፌዴራል ደረጃ የሚንቀሳቀስ አንድ ግብረ ኃይል መቋቋም አለበት። በየክልሎቹና በአዲስ አበባ ተጠሪነታቸው ለዚህ ኮሚቴ የሆነ ተመሳሳይ ኮሚቴዎችም መቋቋም ይኖርባቸዋል። ይህም ሕዝቡን ሙሉ በሙሉ ለማሳተፍ ይጠቅማል። የዚህን ስልት ሰነድ ዝግጅት የተሳካ ለማድረግ፣ ብሎም የዓለም አቀፍ አበዳሪዎቹን ይሁንታ ለማግኘት መንግሥት የሕዝብ ትብብርና አመኔታ ማግኘት ያስፈልገዋል። በስልቱ ላይ የተሟላ ስምምነት እንዲኖር፣ የስልቱን ጥቅምና ጉዳቱን ለሕዝብ በግልጽና በዝርዝር ማስረዳትና ማሳወቅ ያስፈልጋል። መንግሥታዊ

CCRDA

ያልሆኑ ድርጅቶች በክርስቲያን በጎ አድራጎትና የልማት ድርጅት አሰባሳቢነት እንደነዚህ ባሉ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጓቸው ጥረቶች አስደሳችና የሚያበረታቱ ናቸው። እንግዲህ ያዘጋጀሁት ጥናታዊ ጽሁፍ ረዥም ሆኖ የተሰጠኝ ሰዓት አጭር በመሆኑ፣ አንዳንድ የውይይት መነሻ ነጥቦችን ለማንሳት ብቻ ነው የሞከርኩት። በጥያቄና መልስ ጊዜ የቀሩትን አንዳንድ ነጥቦች ለማንሳት እሞክራለሁ። አመሰግናለሁ።

አወያዩ አቶ ከበደ አሥራት፣ ዶክተር ሽመልስ ላቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ አመስግነው፣ የሚቀጥሉትን የፓነል አቅራቢ ወሐሮ ሮማን ተስፋዬን ጋበዙ። ወሐሮ ሮማን ያቀረቡት ዝግጅት የሚከተለው ነው።

2.2.1 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልል

እኔ የማቀርበው ጽሁፍ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ መንግሥት ሕዝቡን በማሳተፍ የሚካሄደው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ውይይት በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? በዚህ ውይይት ሂደት ሕዝቡን በምን ሁኔታ ነው እያሳተፍን የቆየነው? የሚለውን ለማብራራት የሚሞክር ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የራስዋን ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት ከገቢዋ ልትሸፍን ያልቻለች አገር ሆና ኖራለች። ይህን ጉድለት ለመሸፈን ሲባል በውጪ ብድርና እርዳታ መደገፍ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ጉድለት የሚባባሰው የተከማቸ ዕዳ ለመክፈል ሲባል፣ በየዓመቱ ከሚገኘው የውጪ ምንዛሪ ግኝት ላይ ከስልሳ በመቶ በላይ ለክፍያ መዋሉ ነው። የዚህን ብድር ጫና ለማስቀነስና ተጨማሪ ብድሮችን ማግኘት እንዲቻል፣ ዓለም አቀፍ አበዳሪ ድርጅቶች የሚያስቀምጡትን ሁኔታዎች ማሟላት አስፈላጊ በመሆኑ፣ የዚህ ሰነድ ዝግጅትም አንዱ ዓላማ ይኸው ነው። ሌላው የሰነዱ ጥቅም ለምንከተለው ግብርናጠመር ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ ወይም ስልት ሆኖ ማገልገል ነው።

ከዚህ በፊት የተዘጋጀው ጊዜያዊ ሰነድ በድርጅቶቹ ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘቱ፣ ይህ አሁን የሚደረገው ሂደት ሰነዱን የመጨረሻ ይዘት እንዲኖረው ያደርገዋል። ስለዚህም ነው መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ሕብረተሰቡና መንግሥታዊ ድርጅቶች በሰነዱ ዝግጅት ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርገው እንዲያዳብሩት እያደረገ ያለው።

በክልላችን የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነዱን ለማዘጋጀት የቢሮ ኃላፊዎች፣ የጽሕፈት ቤት ኃላፊዎችና የድርጅት ሥራ አስኪያጆች አባል የሆኑባቸው፣ አንድ በበላይነት የሚያስተባብር ኮሚቴና የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁመዋል። የሴክሬታሪያት ጽሕፈት ቤትም ተቋቁሟል።

CCRDA

የበላይ አስተባባሪው ኮሚቴ ዋና ተግባር፣ ሥራውን በበላይነት መቆጣጠርና ለቴክኒክ ኮሚቴው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ነው። የፕላንና ኢኮኖሚ ቢሮ ኃላፊ የቴክኒክ ሰብሳቢ ሲሆኑ፣ ሌሎች የኮሚቴው አባላት ከየመሥሪያ ቤቱ የተውጣጡ ናቸው። የቴክኒክ ኮሚቴው የሥራ ድርሻ፣ ውይይቱ የሚካሄድባቸው ሂደቶችን ማቀድ፣ ውይይቱን ማካሄድና ሪፖርት ማድረግ እንዲሁም አጠቃላይ የቴክኒክ ድጋፎችን መስጠት ነው።

የሴክሬታሪያት ጽሕፈት ቤት አንድ ዋና እና ሦስት ረዳት አስተባባሪዎች ያሉት ሲሆን፣ ሁሉም የፕላንና ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ናቸው። የሴክሬታሪያቱ የሥራ ድርሻ የጽሕፈት ሥራዎችን ጨምሮ የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ማከናወንና በጀት ማስተዳደር፣ እንዲሁም አስፈላጊውን መረጃ ለፌዬራሉ ማስተላለፍ ወዘተ. ይሆናል።



የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት በደብረዘይት ማኔጅመንት ተቋም በተካሄደው አገር አቀፍ ሴሚናር ተካፍለዋል። በሴሚናሩ ላይ ድህነትን አስመልክቶ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች የቀረቡ ሲሆን፣ ውይይቶች ስለሚካሄዱባቸው አጠቃላይ ሁኔታዎችም ስምምነት ላይ ተደርሷል። ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ የወረዳዎች ቁጥርና የሚመረጡበት መስፈርት፣ የተሳታፊዎች ቁጥርና የሕብረተሰብ ውክልና መጠን፣ ውይይቱ ዮት ቦታ ይካሄድ? ለስንት ቀናት? የሚሉ ናቸው።

ሦስት፣ ሦስት ባለሙያዎችን ያቀፉ አራት ቡድኖች፣ በነሐሴ መጨረሻ የመስክ ስምሪት አድርገዋል። ቡድኖቹ ቀደም ሲል በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት በቴክኒክ ኮሚቴው የተደረገውን የወረዳ ምርጫ ከሠን ኮሚቴዎች ጋር በመሆን አፅድቀው፣ ስለሰነዱ ይዘት ለሚመለከታቸው አካላት ገለጻ አድርገዋል። ከትምህርት፣ ከጤናና ከግብርና ተወካዮች ጋር ሆነው በየወረዳው አንድ አወያይና ሁለት ሪፖርተሮች አስመርጠዋል። ከዚያም የውይይት ሰነድ አንድንና ሰነድ ሀለትን አሰራጭተዋል።

ለውይይቱ የተመረጡት ወረዳዎች 18 ሲሆኑ 6 ክፍፍል አላቸው:: እነዚህም

- የወጪ ምርት የሚያመርቱ - አለታ ወንዶ፣ አማሮ፣ ወናጎና የኪ
- ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለባቸው - ሸበዲኖ፣ ዳሞት ጋሌ፣ አንጋጫና የም
- በቂ ዝናብ የሚያገኙና እህል አምራች የሆኑ - ሊሞ፣ ጨንቻና ገዋታ
- ዝናብ አጠር እህል አምራች የሆኑ - ዳሎቻ፣ ቾሃና ሎማ
- በተደጋጋሚ በድርቅ የሚጠቁ - ኮንሶና ሁምቦ
- አርብቶአደር አካባቢዎች የሆኑት የሐመርና ሱርማ ወረዳዎች ናቸው::

በመስከረም ወር 1992 ዓ.ም የአወያዮችና ሪፖርተሮች ሥልጠና ለሦስት ተከታታይ ቀናት ተካሂዷል:: ከተመረጡት 18 ወረዳዎች ውስጥ ከእያንዳንዱ ወረዳ ሦስት ሦስት ተወካዮች ተገኝተዋል:: ሥልጠናው የተሰጠው ከፌዴራልና ከክልል ቴክኒክና ሴክሬታሪያት ጋራ በጋራ ነው:: በሥልጠናው ላይ የድህነት አጠቃላይ ጽንሰ ሃሳብን በተመለከተ ግንዛቤ የሚያስገኝ ትምህርት ተሰጥቷል:: የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርና፣ የመንገድና የሴቶች ጉዳይን በመሳሰሉ ርዕሶች ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል:: ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮችም ሰፊ ግንዛቤ ያስገኙ ውይይቶች ተካሂደውባቸዋል::

ከሥልጠናው በኋላ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅቱን የሚመለከቱ ውይይቶች በተመረጡት ወረዳዎች ውስጥ ተካሂደዋል:: የተወያዮች ስብጥር ዕድሜን፣ ፆታን፣ የሥራ ዓይነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነበር:: ከ50ው ቢያንስ 30 የሚሆኑ ሴቶች፣ እንደገናም ከ50ው ከ30 እስከ 35 የሚሆኑት ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች፣ አዛውንቶች፣ የቤት እመቤቶች፣ ሥራ አጥ ወይም ተማሪ ወጣቶች ሲሆኑ፣ ቀሪው ከ10 እስከ 15 የተመረጠው ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የሃይማኖት ድርጅቶችና መንግሥታዊ ካልሆኑ አገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ነው::

የምክክሩ አጀንዳዎች፣

- የድህነት ምንነት ከወረዳው ተጨባጭ ሁኔታና ከሕዝቡ የሕይወት ልምድ አንፃር በሕብረተሰቡ እንዴት ይገለጻል? መለኪያዎቹስ ምንድናቸው?
- ሕብረተሰቡ በአጀንዳ አንድ ላይ ድህነትን ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን መለኪያዎች መሠረት በማድረግ፣ ድህነት ባለፉት ዓመታት ምን ይመስላል?
- ለድህነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉት ምክንያቶች በቅደም ተከተል እንዴት ይገለጻሉ?
- የሕዝቡ ኑሮ የተመሠረተው በምን ላይ ነው? ከዚህ አንፃር ያሉት መሠረታዊ ችግሮችና ይህንን ለመቅረፍ በሕብረተሰቡ፣ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተወሰዱና ወደፊት ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድናቸው?

CCRDA

ድህነትን በመቀነስ የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በማህበራትና በሕብረተሰቡ የተወሰዱ እርምጃዎች ምን ይመስሉ ነበር?

በወረዳው የሚገኙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋሞች ለሕብረተሰቡ እየሰጡ ያሉት አገልግሎት ምን ይመስላል? ምን ዓይነት ችግሮች አሉ?

በወረዳው ድህነትን ለመቀነስ ወይም ለመቅረፍ ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው ጉዳዮች በቅደም ተከተል ምንና ምን ናቸው?

ድህነትን የማያባብሱ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና የግል ባሕሪያት ምንድናቸው?

በተለያየ ደረጃ ያሉ አስተዳደራዊ መዋቅሮች ለሕብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምን ይመስላል? ምን ችግር አለ?

የኤች አይ ቪ ኤድስ እያስከተለ ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ምን ይመስላል? ለድህነት የሚያደርገው አስተዋፅኦስ ምን ያህል ነው? የሚሉ ነበሩ::

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት ሂደት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው እናምናለን:: ድህነት የጋራ ችግር ነው:: ስለዚህ በአንድነት ስንታገለው እንደቆየን ሁሉ፣ ወደፊትም ትብብራችንን አጠናክረን በዚሁ መቀጠል ይኖርብናል:: መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቶች ከፍተኛ የሆነ ልምድ አካብተዋል:: ይህም በመሆኑ ለድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት ከወረዳ ጀምሮ እስከ ፌዴራል ደረጃ በሚካሄዱ ውይይቶች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው::

በአጠቃላይ፣ የሕዝቡን መሠረታዊ ችግሮች በዘለቄታ የመፍታት ዓላማን ተከትሎ መሥራት ይጠበቃል:: በእኛ በኩል በክልላችን ውስጥ ለልማት ሥራ አመቺ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል:: የመንግሥት ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ድሃውን ለማገልገል የሚያስችሉ እየሆኑ ተሻሽለዋል:: በተለይም የገጠር ልማት ፖሊሲ ላይ ትኩረት ተሰጥቷል:: ልማትን ማካሄድ ወይም ድህነትን መቀነስ ሲባል ያለህብረተሰቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊታሰብ የማይቻል ስለሆነ፣ በዚህ ዓመት የሕዝብ አደረጃጀትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በአዋጅ ተቋቁሟል:: ይህ መዋቅር እስከ ወረዳ የሚዘረጋ ይሆናል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚመለከት መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል:: ሕዝቡ ከድህነት ለመውጣትና በማንኛውም የልማት ሥራ ለመሳተፍ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተነሳሽነትን አሳይቷል::

ችግሮች ከምንላቸው ውስጥ ደግሞ፣ የአቅም ውስንነት ማለትም የካፒታል፣ የሠለጠነ የሰው ኃይልና የመሬት ጥበት ይጠቀሳሉ:: እንዲያም ሆኖ ግን፣ ያለንን ሀብት በወጉ በብቃት ያለመጠቀም፣ ሌላው አስከፊ ችግር ነው ብዬ አምናለሁ:: እንደሚታወቀው፣

GCRDA

የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ወይም አበዳሪ ድርጅቶች ያስቀመጠልን ቅድመ ሁኔታ ነው:: ግን ይህ የኛ አጀንዳ ነው ወይስ አይደለም? ያልመሰለን ካለን ጊዜው ሳይሄድብን አጋጣሚውን ተጠቅመን የራሳችን አጀንዳ በማድረግ፣ ድህነትን ለመቀነስ ብርቱ ጥረት በማድረግ የበኩላችንን ድርሻ እናበርክት:: ምክንያቱም፣ ድህነት በአገራችን ከኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት ጋር ተዳምሮ አድማሱ እጅግ ሰለሰፋ፣ ሁሉም ወገን ካልተባበረ የሚፈለገው የድህነት ቅነሳ እውን ሊሆን አይችልም:: አመሰግናለሁ::

አወያዩ አቶ ከበደ አሥራት ወሐሮ ሮማን በክልላቸው የድህነት ቅነሳ ስልት ዝግጅት ሂደትን አስመልክተው ላቀረቡት ዘርዘር ያለ የውይይት መነሻ ጽሁፍ አመስግነው፣ የሚቀጥለውን ተናጋሪ አቶ አህመድ አሊን ጋበዙ:: አቶ አህመድ ለውይይት መነሻነት ያቀረቡት ጽሁፍ የሚከተለው ነው::

2.2.2 የፓነል አቅራቢው ርዕስ:- የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚኖረው ጠቀሜታና ሚና

እኔ የማተኩርበት ርዕስ፣ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚኖረው ጠቀሜታና ሚና ምንድነው? የሚል ነው:: ሁለት ንዑሳን ጥያቄዎች ላይ ነው በተለይ የማተኩረው:: አንደኛው መያዶች ለምንድነው ለድህነት ቅነሳ ስልት ትኩረት የሚሰጡት? ምን የሚመለከታቸው ነገር አለ? የሚል ይሆናል:: ሁለተኛው፣ በሌሎች ሀገሮች የሚገኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም በአጠቃላይ የሲቪል ማህበረሰቡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው የተሳትፎ ልምድ ምን ይመስላል? የሚል ይሆናል:: የማቀርበው ሃሳብ በአብዛኛው ከራሴ የመነጨ አይደለም:: በተለያዩ እትሞችና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ከቀረቡ አስተያየቶች ያገኘሁትን ሃሳብ በማሰባሰብ ነው ያቀረብኩት::

ለመንደርደሪያ እንዲሆነኝ ሌሎች ያሉትን አንዳንድ ነገር በአዕንአት ብደግም ደስ ይለኛል:: አንደኛ፣ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ማዘጋጀት ያስፈለገው ለምንድነው? የሚለውን ሁላችንም በአዕምሮአችን መያዝ የሚገባን ይመስለኛል:: ለእኔ ሁለት ምክንያት አለው:: አንደኛ፣ ብድር ስለሚያስፈልገን፣ ሁለተኛ፣ ቀደም ሲል የተበደርነውን መክፈል ስላለብን ነው:: የብድርና የዕዳ ጉዳይ ነው:: አብዛኞቹ በአፍሪካም ይሁን በእስያ ወይም በላቲን አሜሪካ የሚገኙ አዳጊ ሀገሮች በሙሉ ባለዕዳ ናቸው:: በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ደረጃ ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያን ብንወስድ በጣም ከፍተኛ ዕዳ ካለባቸው አገሮች መካከል ቀዳሚዋ መሆኗን መረጃዎች ያመለክታሉ:: ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ዕዳ አለብን:: ምን ማለት ነው? በነፍስ ወከፍ እያንዳንዳችን 175 ወይም 170 ዶላር በላይ ባለዕዳ ነን ማለት ነው:: ስለዚህ ዕዳን መክፈል ራሱ አንድ ትልቅ ችግር ነው::

CGRDA

አፍሪካ ውስጥ አብዛኞቹ ሀገሮች ከፍተኛ ባለዕዳ በመሆናቸው፣ መክፈል የተቸገሩበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ያለብድር ልማትን ማካሄድ ደግሞ በጣም ከባድ ሆኗል። አብዛኞቹ አዳጊ አገሮች የልማት ብድር ካላገኙ በስተቀር፣ ልማትን አቅድው ለማካሄድ በጣም የሚቸገሩበት ሁኔታ ነው ያለው። ስለዚህ የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሚያወጡትን መመሪያ ተከትሎ የሚፈልጉትን ማቅረብ፣ ለብድር ቅነሳም ሆነ አዲስ ብድር ለማግኘት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል እየተባለ ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያ ወደፊት ለልማት ሥራ አዲስ ብድር ለማግኘት እንድትችል ወይም ደግሞ እስካሁን ካለብን ዕዳ ላይ ቅነሳ እንዲደረግልን፣ ይህንን የተጠየቀውን የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ አዘጋጅተን ማቅረብ ይኖርብናል።

ባሁኑ ጊዜ በዓለም ውስጥ 42 አገሮች ናቸው ይህንን የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ አዘጋጅተው የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው። ከ42ቱ ውስጥ ኢትዮጵያን ጨምሮ 25ቱ በአፍሪካ ነው የሚገኙት። 5ቱ በላቲን አሜሪካ፣ 8ቱ በአውሮፓና በመካከለኛ እስያ፣ 3ቱ በእስያ፣ እንዲሁም አንዱ በመካከለኛው ምሥራቅ ነው የሚገኙት።

ሁኔታው ይህን ሲመስል በአንዳንዶች ዘንድ፣ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ የመንግሥት ጉዳይ ነውና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ምን አገባቸው? የሚል ጥያቄ ይነሳል። ይህ ጥያቄ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ አይደለም የተነሳው። ሌላም አገር ላይ የሚነሳ ጥያቄ እንደሆነ ሰነዶችን ሳገላብጥ አይቻለሁ። ይሄ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ መያዶችን ይመለከታቸዋል። መያድ ስል በአጠቃላይ የሲቪል ማህበረሰቡ አካል መሆናቸውን እያሰብኩ ነው። የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ የሚናገረው ስለድሆችና ስለድህነት ነው። ጥያቄው ድህነትን እንዴት ነው መቀነስ የሚቻለው የሚል ነው። አገሮች ምን ቢያደርጉ ነው ይህን እግር ተወርች ያሠራቸውን ድህነት መቀነስ የሚችሉት የሚል ጥያቄ ላይ የሚያነጣጥር ሰነድ ነው። ዓለም ባንክም አለው፣ አገሮች ራሳቸውም አሉት፣ ዞሮ ዞሮ ስልቱ የሚያወሳው ስለድህነት ጉዳይ ነው። የድህነት ተጠቂ ስለሆኑ አገሮች ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ መያድ ለምን በየአገሩ ይኖራል? ቢባል፣ መልሱ ድህነት ስላለ ነው የሚል ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ለምሳሌ፣ እኔ የምሠራበት ድርጅት አክሽን ኤድ ለምንድነው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖረው? ብትሉኝ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ድህነት ስላለ ነው፣ የድህነት ተጠቂ ወገኖች ስላሉ ነው ብዬ እመልስላችኋለሁ። መያዶች ራሳቸው እንደሚሉትና ሌሎችም ሥራቸውን አይተው እንደሚገመግሙት፣ የበጎ ፈቃደኛ ድርጅቶቹ በኢትዮጵያ ከድሃው ጋር የመሥራት ታሳፊነትም፣ የሞራል ግዴታም ይዘው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ሁሉም ባይሆኑ የድሃውን ብሶት፣ የድሃውን ችግርና የዕለት ተዕለት ሁኔታ በቅርብ የሚገነዘቡ ናቸው ብዬ እገምታለሁ። እና ስለድህነት ቅነሳ የሚያወሳና የሚዘክር ሰነድ ይዘጋጅ ሲባል፣ መያዶች በዚህ ጉዳይ ውስጥ ያገባቸዋል፣ ይመለከታቸዋል ብዬ አምናለሁ። ይሄ የመጀመሪያው አንዱ ዋና ምክንያት ነው።

CCRDA

በውይይት ወቅት የበለጠ ሊሰፋ የሚችል ነው። ምን ያህል መደዶች በድህነት ዙሪያ በቅርብ ይሠራሉ? ድሃውንስ ምን ያህል ይወክላሉ? የሚለው የውይይት መነሻ ሆኖ ሊታይ ይችላል።

የድህነት ቅነሳ ስልት ስለፖሊሲ ምርጫም ነው። ድህነትን እንዴት እንቅረፍ? እንዴት እናስወግደው? እንዴት እንዋጋው? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የተለያዩ አማራጮችን ስለማየት ነው። የፖሊሲ ምርጫ ስለማድረግ ነው። በዚህ አቅጣጫ እንሂድ፣ ይሄኛው ያዋጣናል ስለማለት ነው። እና በኢትዮጵያ ደረጃ እኔ በግሌ እንደምገነዘበው፣ መደዶች ብዙ ለፖሊሲ መጠናከር ወይም ለፖሊሲ መሻሻል ወይም ለፖሊሲ አፈጻጸም የሚረዱ አያሌ ልምዶችን የፈጠሩ ይመስለኛል። በየሴክተሩ ብናየው ለምሳሌ፣ በምግብ ዋስትና፣ በጤና፣ በትምህርት ወዘተ. መደዶች የራሳቸው የሆነ ሰፊ ልምድ አካብተዋል።

እታች ከድሃው ወገን ጋር አብሮ በመሥራት፣ እላይ የሚቀየሱ ፖሊሲዎች ምን ቢያደርጉ፣ ምን ላይ ትኩረት ቢሰጡ የተሻሻለ ነገር ሊፈጠር እንደሚችል የራሳቸው የሆነ ሃሳብ አላቸው። ስለዚህ የድህነት ቅነሳ ስልት የፖሊሲ ምርጫ የማድረግ ጉዳይ ከሆነ፣ መደዶችም በዚህ ላይ ብዙ በጎ የሆነ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብዬ እገምታለሁ።

የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድን ማዘጋጀት በዘፈቀደ የሚካሄድ ሥራ እንዳልሆነና የተወሰኑ መርሆችን መከተል እንዳለበትም ተገልጿል። ለዚህም፣ ሕዝባዊ ተሳትፎና የድሆች ድምፅ ተሰሚነት ማግኘት ዋናው መርህ ሆኖ ተቀምጧል። ቅድም እንዳልኩት ስልቱ ስለድሆችና ስለድህነት ስለሆነና ጥያቄውን እንዴት ምላሽ እንስጠው ማለት ስለሆነ፣ ተሳትፎ ወሳኝ እንደሆነ ተመልክቷል። ተሳትፎ ሲባል ደግሞ ብዙ ትርጉም አለው። ብዙ አፈጻጸም አለው። ዋናው የተሳትፎ መገለጫ ግን በውሳኔ ሂደት ውስጥ መሳተፍ ነው። ተሳትፎ በስብሰባ ላይ ስለመገኘት ብቻ አይደለም። ተሳትፎ ሰዎችን ይህንን አድርጉ ስለማለትም አይደለም። ተሳትፎ በአንድ ጉዳይ ላይ በጋራ መወያየትን፣ መመካከርን እና ሃሣብ ለሃሳብ መለዋወጥን፣ የችግሩን አቅጣጫ በጋራ ለማየት መሞከርንና በየት እንሂድ በሚለው ጥያቄም ላይ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስን የሚያረጋግጥ ነው። የድሆች ድምፅ ይሰማ ሲባል፣ ድሆች ብዙ ነገር ሊሉ ይችላሉ። እና መርሆውም፣ ያ ነገር ምን ያህል ነው ወደ በጀት የሚመነዘረው? ምን ያህል ነው የፖሊሲ አቅጣጫው ላይ የሚካተተው የሚለውንም ነገር የሚመለከት ነው። ስለዚህ፣ ሕዝባዊ ተሳትፎና የድሆች ድምፅ ተሰሚነት ማግኘት ዋና መርህ ነው። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሲቪል ማህበሩ አንድ ወገን ናቸው። ግማሽ አካል ናቸው። ስለዚህ በንቃት ቢሳተፉ፣ ሃሳባቸውን ቢያካፍሉ፣ በውሳኔ አሰጣጡ ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ቢያደርጉ ጠቃሚ ይሆናል። እንግዲህ በዚህ ምክንያት ነው የድህነት ቅነሳ ስልት መደዶችን የሚመለከተው።

CCRDA

ከዚሁ ጋር አብሮ የተቀመጠው ሌላው መርህ፣ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ በጋራ ትብብር አጋርነትን በመፍጠር መዘጋጀት አለበት የሚል ነው። ይኸው መርህ፣ ሰነዱ ከግል ባለሀብቱ ጋር፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር፣ ከአጠቃላይ የሲቪል ማህበሩና ከለጋሾችም ጋር በመተባበር ይዘጋጅ የሚል ስለሆነ፣ መያዶች በቀጥታ እንዲተባበሩ የሚያደርግ ነው።

የመያዶች ተሳትፎ እንደየሀገሩ ይለያያል። የሚለያየው በሁለት ምክንያቶች ነው። መያዱ ያልጠነከረበት አገር ካለ ተሳትፎው ያንሳል። ጠንካራ የሆነበት አገር ካለ፣ ተሳትፎው እንደዛው ይጠነክራል። ሌላው ደግሞ፣ የመንግሥቱ የፖለቲካ ሥርዓት ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን የሚያራምድ መሆን አለመሆኑም በተሳትፎው መጠን ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል። ለዚህም በአፍሪካ ውስጥ በምሳሌነት በመጠቀስ ላይ ያሉ አገሮች አሉ። ተሳትፎአቸው በጣም የተዋጣ ነው ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ ዩጋንዳ ነች። ዩጋንዳ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ አዘጋጅታ ካስረከበችና ተግባራዊ ወደ ማድረጉ ከተሸጋገረች ቆይታለች። በዚህ የመጀመሪያዋ አገር ነች። በዩጋንዳ የሚገኙ መያዶች በራሳቸው የተሰባሰቡበት በጣም የተጠናከረ መድረክ አላቸው። እና መንግሥት የስልቱን ሰነድ ለማዘጋጀት ባዋቀራቸው መዋቅሮች ከላይ እስከታች ድረስ የአባልነት ቦታ ተሰጥቷቸውና ተንቀሳቅሰው ነው ሰነዱ የተዘጋጀው። እና ይህ እንደጥሩ ምሳሌ ተደርጐ በብዙ ወገኖች ዘንድ ይጠቀሳል። ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

አወያዩ አቶ ከበደ አሥራት፣ አቶ አህመድ ላቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ በተሳታፊዎችና በራሳቸው ስም አመስግነው፣ የሚቀጥለው ተናጋሪ አቶ ጌታሁን ታፈሰ ዝግጅታቸውን እንዲያቀርቡ ጋበዙ። የአቶ ጌታሁን ዝግጅት ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

2.2.3 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- የሲቪሉ ማህበረሰብ በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት የሚኖረው የተሳትፎ ፅንሰ ሃሳብ

እኔም ባጭሩ ዋና ዋና መሠረታዊ ነጥቦች ላይ አትኩሬ ለማቅረብ እሞክራለሁ። የተሰጠኝ ርዕስ «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂው ሰነድ ዝግጅት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ምን መምሰል አለበት» የሚለው ነው። መቼም ይሄ አዲስ ዓይነት የስልት ሰነድ አዘገጃጀት ሂደት ነውና የሕብረተሰቡ ተሳትፎ በሰነዱ ዝግጅት ላይ ይኑር ሲባል፣ በመጀመሪያ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን በትንሹ ለማንሳት እሞክራለሁ። ከእኔ በፊት የተናገሩት አቶ አህመድም ይህንን አንስተውታል።

CCRDA

የሕብረተሰቡ ተሳትፎ ሲባል አገሪቱ በምትከተለው የልማት አቅጣጫ፣ የፖሊሲ ይዘት፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባሮችን በመለየትና በሀብት ድልድል አፈጻጸም ላይ ሕብረተሰቡ ወሳኝ ሚና ይጫወት ማለት ነው:: ወሳኝ ሚና ይጫወት ሲባል ደግሞ፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ የራሱ የኃላፊነት ድርሻ ይኑረው ማለት ነው:: ወሐሮ ሮማን በደቡብ ክልል፣ ስልቱ በምን መልኩ እየተዘጋጀ እንደሆነ ገልጸውልናል:: መንግሥት የተለያዩ መድረኮችን በወረዳ ደረጃ ፈጥሮ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት አድርጓል:: ይሄ ጥሩ ነገር ነው:: አንድ አዎንታዊ ርምጃ ነው:: ግን ተሳትፎ የሚለውን በተሟላ መልኩ የሚይዝ አይደለም:: በቃሉም እንደተጠቀሙት ምክክር ነው ያሉት:: ስለዚህ በክልሉ የሰነድ ዝግጅቱን ሂደት በሚመለከት የተካሄደው ውይይት በተሳትፎ ሳይሆን በምክክር ነው የተካሄደው ነው የሚባለው::

መንግሥት የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጠርቶ ሃሣብ ሲተበል እንደ ተሳትፎ ላይታይ ይችላል:: ተሳትፎ አለ የሚባለው በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ሕብረተሰቡ ተሳትፎ ሲያደርግ ነው:: ታዲያ ይሄ በምን መልኩ ተግባራዊ ይሆናል? ለሁሉም አገር የሚሠራ አንድ ዓይነት ወጥ የተሳትፎ ሥርዓት የለም:: ሁሉም እንደየአገሩ ነባራዊ ሁኔታ የሚለያይ ነው:: ሆኖም ግን አንዳንድ መሠረታዊ መርሆዎች ሊኖሩት ይገባል:: ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን እጠቅሳለሁ:: አንደኛ፣ የሲቪል ሕብረተሰቡ ተሳትፎ፣ በዓላማ ወይም ውጤት በማምጣት ላይ ማተኮር አለበት:: ስለሆነም የተለያዩ መያዶችና የሕብረተሰብ ክፍሎች በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት ይሳተፉ ሲባል፣ የሰነዱ ዝግጅት እንደ ዋና ዓላማ መሆን የለበትም:: ዋና ዓላማው ሕብረተሰቡ ድህነትን በዘላቂነት እንዴት እንዲቀንስ ማድረግ ይችላል ብሎ፣ ውጤት በማምጣት ላይ ያተኮረ ተሳትፎ የሚያደርግበት መሆን አለበት:: ስለዚህ ሰነዱ እንደአንድ ውጤት የሚታይ እንጂ የመጨረሻ ውጤት ወይም ግብ መሆን የለበትም::

በዚህ ምክንያት፣ መንግሥት ሕብረተሰቡን ሲያሳትፍ እንደቅድመ ግዴታ ሳይሆን፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መሳተፋቸው የሰነዱን ዝግጅት ውጤታማ ሊያደርግ የሚያስችል ስልት አድርጉ በማየት መሆን አለበት:: ሕብረተሰቡም ተሳትፎ ሲያደርግ በዚሁ መልኩ መሆን አለበት:: ተሳትፎ በአንድ ወቅት ብቻ ተካሂዶ የሚቋረጥ መሆን የለበትም:: እንደዚህ ዓይነት ስብሰባዎች በተለያየ ጊዜ በተለያየ ወቅት ይካሄዳሉ:: ብዙ ጊዜ ግን ተከታታይነት ስለማይኖራቸው ውጤታማ ሳይሆኑ ይቀራሉ:: ስለዚህ የሕብረተሰብ ተሳትፎ ሲጀምር ተከታታይነት በሚኖረው መልኩ እንዲካሄድ ትኩረት መሰጠት አለበት::

CGRDA

በሌላም በኩል፣ የሕብረተሰቡ ተሳትፎ በራስ ተነሳሽነትና ፍላጐት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት:: መንግሥት ብቻ መድረኩን ፈጥሮ ኑ ተሳተፉ እስከሚል መጠበቅ ሳይሆን፣ መያዶችና ሌሎችም የሲቪል ማህበረሰብ ክፍሎች ጠንካራ ሚና ለመጫወት ተነሳሽነቱ ከራሳቸው መምጣት አለበት:: እነዚህን አንዳንድ መሠረታዊ መርሆዎች ከጠቃቀስኩ፣ በዚህ ሰነድ ዝግጅት የህብረተሰቡ ተሳትፎ ለምን ያስፈልጋል? የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት እሞክራለሁ:: በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት፣ ሕብረተሰቡ እንዲሳተፍ የሚያደርጉ የተለያዩ መነሻ ምክንያቶች አሉ:: የልማት ትርጉም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀያየረ ሄደ፣ በአሁኑ ወቅት፣ ልማት ማለት አጠቃላይ የሕዝብ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል ነው፣ የሚል አጠቃላይ ግንዛቤ ላይ ተደርሷል:: ከዚህ በፊት ልማት ማለት የኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ተደርጐ ነበር የሚታሰበው:: አሁን ግን ሕዝቡን ያሳተፈ፣ ህብረተሰቡ የተሰማማበትና የሕብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ የሚዳስስ አጠቃላይ የኑሮ መሻሻል ተደርጐ ነው የሚወሰደው:: ስለዚህ ልማት ከዕድገት በተጨማሪ ፍትሐዊነትን ይህም ማለት፣ የማህበራዊ ፍትህን፣ የትምህርት፣ የጤናና የዲሞክራሲ ጉዳዮችን ያካተተ ነው::

ስለሆነም፣ የልማት ባለቤት ሕዝቡ ራሱ እየሆነ የመጣበት አካሄድ ነው ያለው:: ለዚህ ነው እንግዲህ ሕብረተሰቡ ልማትን በማምጣት ረገድ በፖሊሲ ደረጃ ሚናውን መጫወት ያለበት:: ከዚህ ቀደም የሲቪል ማህበረሰቡ በተለይም በጎ አድራጊ ድርጅቶች በፖሊሲ ቀረፃ ለመሳተፍ ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርቡ ቆይተዋል:: ልማትም ሰብአዊ መልክ እንዲይዝ፣ መያዶች ለረጅም ጊዜ ብዙ ግፊት ሲያደርጉ ቆይተዋል:: ስለዚህም፣ ይሄ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ሲመጣ፣ እነዚህን መርሆች ያካተተ በመሆኑ፣ መያዶችም፣ ሕብረተሰቡም፣ በዚህ ላይ ለመሳተፍ ጥረት ማድረግ አለብን:: ሕብረተሰቡም ለረጅም ጊዜ ጥያቄዎችን ሲያቀርብ የቆየ በመሆኑ፣ በዚህ ሰነድ ዝግጅት የሚያደርገውን ተሳትፎ በሦስት ሂደቶች ማየት ይቻላል:: አንደኛው፣ በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመገምገምና ፖሊሲ ሆኖ እንዲወጣ በማድረግ ይሆናል:: ሁለተኛው፣ ሰነዱ ከተዘጋጀ በኋላ በአፈጻጸም ማለትም በበጀት አመዳደብ፣ በፕሮጀክት ቀረፃ፣ በቦታ አመራረጥ፣ ድልድል ወዘተ ይሆናል:: ሦስተኛው፣ በሰነዱ አፈጻጸም ላይ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ይሆናል:: ይሄ አሁን የሚዘጋጀው ሰነድ ለሦስት ዓመት ሲሆን፣ መንግሥት በየዓመቱ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለዓለም ባንክና ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሚያቀርብ ይሆናል:: ስለዚህ መያዶችም በተመሳሳይ መልኩ፣ ሰነዱ ምን ያህል ተግባራዊ እየሆነ ነው የሚለውን ክትትል ማድረግ አለባቸው:: ውጤት ስለማምጣቱም የራሳቸውን ጥናት ማካሄድ አለባቸው:: ድህነት እየጨመረ ነው ወይስ እየቀነሰ? የሚሉ ጥያቄዎች ላይ ተመስርተው ምላሽ የሚሰጡ ሪፖርቶች መዘጋጀት አለባቸው:: ህብረተሰቡ በዚህ ሰነድ ዝግጅት ተሳትፎ ሲያደርግ፣ ተሳትፎው በተለያየ

CCRDA

ደረጃ መሆን ነው ያለበት:: ተሳትፎው በፈዴራል፣ በክልል፣ በወረዳና ከተቻለም ወርዶ በቀበሌ ደረጃዎች ሆኖ፣ ትኩረቱ ትምህርትና ጤና የመሳሰሉትን ብቻ ሳይሆን፣ አጠቃላይ የመንግሥት የልማት አቅጣጫ አካሄድ ምን መሆን አለበት? የታክስ መጠን ምን መሆን አለበት? የበጀት ጉድለቱ ምን ያህል መሆን አለበት? የወለድ መጠን ምን ያህል መሆን አለበት? በሚሉትም ላይ መሆን አለበት::

እንደዚህ ዓይነቶችን ተሳትፎ ለማድረግ የተለየዩ የተሳትፎ ማስፈፀሚያ ዘዴዎች አሉ:: የጋራ የውይይት መድረኮች አንድ ዓይነት የተሳትፎ መገለጫ ናቸው:: ሆኖም፣ ሕብረተሰቡ ይሳተፍ ስንል የመረጃ ልውውጥ ያስፈልጋል:: ይህም የኢንፎርሜሽን ስትራቴጂ የሚባል ነው:: ይህ ደግሞ ከሲቪል ማህበረሰቡ ለመንግሥት ብቻ የሚቀርብ መረጃ ሳይሆን፣ መንግሥትም ለህብረተሰቡ መረጃን በማስተላለፍ ከሁለት አቅጣጫዎች የሚፈስስ የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያስፈልጋል::

ሌላው ደግሞ ተደጋጋፊ ጥናቶችን ማካሄድ ያስፈልጋል:: ስለድህነት ሁኔታ ሲጠና መንግሥት ለብቻው፣ መያድ ለብቻው ሳይሆን፣ ቢቻል የጋራ ጥናቶችን በማካሄድ መረጃውን በመለዋወጥና የጋራ ትንተና በማካሄድ፣ በድህነት ጉዳይ ላይ አንድ ዓይነት ስምምነት ለመድረስ የሚያስችል አካሄድ መከተል ይቻላል:: ከዚህ ውጭ ለምሳሌ፣ መንግሥት ያካሄዳቸው ጥናቶች ካሉ፣ መያዶች እነዚያን የሚያጠናክሩ ተጨማሪ ጥናቶችን በማካሄድ፣ ሕዝቡ ስለድህነት ሁኔታ ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር ማድረግ ይችላሉ:: ስለሆነም፣ የሲቪል ማህበረሰቡ ጥናቶችን በማካሄድና ውጤቶቹ ለፖሊሲ ቀረፃ እንዲውሉ በማድረግ ተሳትፎውን ማጠናከር ይቻላል::

የተለያዩ አገሮች የድህነት ቅነሣ ስልት ሰነድ ሲያዘጋጁ፣ መንግሥትና ሲቪል ማህበረሰቡ አንድ ዓይነት መዋቅሮች በመዘርጋት አብረው በጋራ የሠሩበት ሁኔታ ታይቷል:: ስለዚህ ከውይይቱ በተጨማሪ እንደዚህ ዓይነት ሥራዎችን መንግሥትና የሲቪሉ ማህበረሰብ በጋራ ቢሠሩ የልማት አጋርነትን ያጠናክራል::

ሕብረተሰቡ በዚህ ሰነድ መሳተፉ የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣል:: የድሃው ድምፅ ተሰሚነት እንዲያገኝና በየአካባቢው ያሉ አንገብጋቢ ችግሮች እንዲታወቁ ማድረግ ያስችላል:: ሕዝቡ ስለድህነት ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል:: የተለያዩ ጠቃሚ ልምዶችን በማካፈል፣ ሕብረተሰቡ ድህነትን ለመዋጋት እንዲነሳሳ ለማድረግ ይረዳል:: በመንግሥት፣ በመያዶች፣ በለጋሾችና በሕብረተሰቡ መካከል ትብብርን በመፍጠር ጠቃሚ አስተዋፅኦ ያበረክታል:: በመጨረሻም ሰነዱ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሲሆን ገንዘብ ስለሚያስፈልግ፣ ገንዘብ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ሕብረተሰቡ በተለይም መያዶች ሊጠቁሙ ይችላሉ::

CCRDA

የአንድን አገር መንግሥት ምንነት ወይም ማንነት ለማወቅ ፖሊሲውን ሳይሆን በጀቱን ተመልከቱ ነው የሚባለው። በፖሊሲ ላይ ብዙ ነገር ሊባል ይችላል። በተግባር ምን እየሆነ ነው የሚለውን የሚያሳየን ግን በጀቱ ነው። ስለዚህ የሲቪል ማህበረሰቡ ድርጅቶች የመንግሥት በጀትን በማወቅና ክትትል በማድረግ ጥሩ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። የዚህ ዓይነት እንቅስቃሴ በደቡብ አፍሪካ አለ። በደቡብ አፍሪካ፣ መንግሥት የዓመታዊ በጀቱን ካወጣ በኋላ ይህንን የሚከታተሉ የሲቪል ቡድኖች አሉ። መንግሥት የበጀት ዝርዝር ዕትሙን በተለያየ ቦታ እንዲለጠፍ በማድረግና ለሕብረተሰቡ በማሳወቅ፣ ሕዝቡ ስለመንግሥት በጀት አመዳደብና አጠቃቀም በግልጽ እንዲያውቅ ይደረጋል።

በጋናና በህንድም ተመሳሳይ ነገሮች አሉ። በኢትዮጵያም እንደዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ያስፈልጋል። መንግሥት ዓመታዊ በጀት፣ ማለትም የካፒታልና የመደበኛ በጀት ሲያዘጋጅ በመጨረሻ በአዋጅ ይወጣል። ነገር ግን ያ በአዋጅ የሚወጣው በጣም በጥቅል ስለሆነ፣ ትኩረቱ የት አቅጣጫ ነው? ምን ምን ሥራዎችን፣ ምን ምን የልማት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ የተመደበ ነው? የሚለውን በዝርዝር አያሳይም። ለወደፊት የሲቪሉ ማህበረሰብ ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር በመወያየት፣ ይሄ የበጀት መግለጫ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆንና ለምን ዘርፎች ቅድሚያ ትኩረት እንደሚሰጥ ክትትል መደረግ ይኖርበታል። መንግሥት በሚያወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ላይ ክትትል በማድረግም፣ የተዘጋጀው ሪፖርት በትክክል የነበረውን ሁኔታ የሚያንፀባርቅ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ጥረት መደረግ አለበት።

የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ለረጅም ጊዜ በሕብረተሰቡ ይጠየቁ የነበሩትን ጉዳዮች እንደመርህ በመያዝ የመጣ በመሆኑ፣ በዚህ ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ሕብረተሰቡ በንቃት መነሳሳት አለበት። ይሄ እንደ ጥሩ አጋጣሚ ነው መወሰድ ያለበት። በተለይ መያዶች ለድህነት ጉዳይ ትኩረት በመስጠት አርአያ መሆን አለባቸው። ለልማት መሠረት የሆኑ መርሆችን፣ ግለት ተጠያቂነትን፣ ግልጽነትን መያዶች ራሳቸው በተግባር በመግለጽ፣ አርአያነት ማሳየት አለባቸው። ይህ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት እስከ 500 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በመያዶች አማካይነት እንደሚገባ ስለሚገመት ነው። ኢትዮጵያ ይህን የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ አዘጋጅታ ወደፊት የዕዳ ቅነሳ ብታገኝ፣ በዓመት ወደ 90 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነው። በመያዶች አማካይነት ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገባው ገንዘብ ጋር ሲታይ በጣም አነስተኛ ነው። ስለዚህ ራሳችን ያለንን ሀብት ድህነትን በመቀነስ ላይ እንዲውል በማድረግ፣ መያዶች አርአያ መሆን ይችላሉ። በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

CCRDA

2.2.4 . አጠቃላይ ውይይት

አወያዩ አቶ ከበደ አሥራት፣ አቶ ጌታሁን ታፈሰን ላቀረቡት ጠቃሚ የውይይት መነሻ ጽሁፍ አመስግነው፣ ተሳታፊዎች ያሏቸውን ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ጋበዙ።

ተሳታፊ፡- ትናንት በክልሉ የሥራ ኃላፊዎች እንደተገለፀውና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽነሩ እንደተናገሩት መያዶች የመንግሥት አጋሮች ነን። እኛም ራሳችንን የምናየው እንደዚያ ነው። መንግሥት መያዶች የልማት አጋሮቹ መሆናቸውን መግለጹ አንድ ታላቅ እርምጃ ነው። ቢሆንም በቃላት ብቻ ሳይቀር በተግባር ቢታይ ጥሩ ነው። በተለይ በአገሪቷ ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ ችግሮችን ለመንግሥት በግልጽ ማንሳት ብንችልና በፖሊሲ ቀረፃ ላይ ብንሳተፍ መልካም ነው። ይሄ ካልሆነ በስተቀር ወደፊት መሄድ አንችልም። ካሁን በፊት በነበረው ይዞታ መሥራት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ሕጐችንና ደንቦችን አክብረው መሥራት እንዳለባቸው ግልጽ ነው። ዳሩ ግን ሁልጊዜም በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በጐ ፈቃድ ብቻ የሚንቀሳቀሱና ፍጹም በሆነ አጋርነት የማይታዩ ከሆነ፣ የተፋጠነ ልማት ማምጣቱ ተስፋ ብቻ ሆኖ ይቀራል። መያዶችና መንግሥት ፈቃድ ጠያቂና ፈቃድ ሰጪ ብቻ ሆነው መቀጠል አይኖርባቸውም ብዬ አምናለሁ። ተልዕኳችን በልማት ላይ እስከሆነ ድረስ፣ ልማት የሥነ ዜጋንም ትምህርት የሚያጠቃልል መሆን አለበት። ብዙዎች መያዶች ግን ከልማት ጋር አያይዘው የሥነ ዜጋ ትምህርት የማይሰጡት፣ ከመንግሥት ፖሊሲ ጋር ያጋጨናል እያሉ ነው። ምኑ ነው ሊያጣላ የሚችለው? ሰዎችን ስለመብታቸው እንዲማሩ ማድረጉ ችግሩ ምንድነው? ይህ ሁኔታ በውል ሊታሰብበትና ሊጠና የሚገባ ነው። አመሰግናለሁ።

አወያይ፡- አስተያየት ስለሆነ ይህንኑ ተቀብለን እናልፈዋለን።

ተሳታፊ፡- አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኘው እሸት የሕፃናትና ወጣቶች አንድነት ማህበር ነው የመጣሁት። እሸት በወጣቶች ዙሪያ የሚንቀሳቀስ አዲስ አገር በቀል መያድ ነው። የኔ ጥያቄ ወሐሮ ሮማንን ይመለከታል። በደቡብ ክልል የድህነት ቅነሳ ኮሚቴ ተዋቅሯል። ከተለያዩ የሕብረተሰብ አባላት ተውጣጥቶ ነው የተዋቀረው። ነገር ግን የወጣቶች ተሳትፎ ያህን ያህል አይደለም። በልማት ሥራ ያለወጣቶች ተሳትፎ ብዙ ለውጥ አናመጣም እየተባለ

CCRDA

በሚነገርበት ባሁኑ ሰዓት፣ በድህነት ቅነሳውም ሆነ የኤች. አይ. ቪ. ኤድስን በመከላከል ሂደት ላይ ወጣቶች በዋነኛ አጋርነት አይታዩም። ይህ የሆነው ለምንድነው? በኮሚቴ አባልነት ብቻ ሳይሆን አንድ ራሱን የቻለ የወጣቶች የምክክር ቡድንስ ለምን እንዲቋቋም አልተደረገም?

የፓነል አቅራቢ፡- እሺ፣ እንግዲህ እኔ የተቻለኝን ያህል ከመለስኩ በ□ላ፣ በመልሴ ላይ የሚኖረውን ክፍተት አንዳንድ የሥራ ባልደረቦቼ እንደሚሸፍኑልኝ እተማመናለሁ። የወጣቶች የምክክር ቡድን ቢቋቋም ምን ነበረበት? የሚል ጥያቄ ቀርቧል። በጽሁፌ ላይ እንዳቀረብኩት በየወረዳ ምክክሩ ላይ የወጣቶች ተሳትፎ እንዲኖር ጥረት አድርገናል። ስንት እጅ ነው ለማለት አሃዙን አሁን አልያዝኩትም። ወጣቱ ለብቻው ሆኖ ለምን አልተመካከረም? ለሚለው ጥያቄ፣ ይህ በፕሮግራማችን ውስጥ አልተካተተም። እንደዚያ ከተባለ ብዙ ተናጠል ቡድኖች ይፈጠራሉ። ሴቱ ለብቻው ሊወያይ ይፈልጋል። ወጣቱ ለብቻው ሊወያይ ይፈልጋል። ሌላውም ቡድን እንዲሁ። ይህንን ለማድረግ ገንዘቡም፣ ጊዜውም፣ የሰው ኃይሉም የለም።

ሌላ ፓነል አቅራቢ፡- የእሸት ወጣቶችና ሕፃናት ማህበር ተወካይ ወጣቶች ለምን በስልት ሰነዱ ዝግጅት አልተሳተፍንም ብሎ ጥያቄ አንስቷል። የሲቪሉ ማህበረሰብ ጠንካራ ሚና ይጫወት ሲባል፣ ጥያቄው መንግሥት ለምን አላሳተፈንም ብሎ መጠየቅ ሳይሆን፣ የእኛ ጉዳይ እንዴት በፖሊሲ ሊንፀባረቅ ይችላል የሚል መሆን ይኖርበታል። ስለዚህ አንደኛ፣ ለመንግሥት ጥያቄ ማቅረብ፣ አንድ ጠንካራ ሚና የመጫወት አካሄድን ያሳያል። ሌላው ደግሞ ወጣቶች በራሳቸው ተሰባስበው ያሉብን ችግሮች እነዚህ ናቸው። መንግሥት እነዚህን ሊያቃልልልን ያስፈልጋል ብለው ተሰባስበው ሃሳባቸውን በተለያዩ መድረኮች እንዲታወቅ ቢያደርጉ፣ ይህ አንድ ምሳሌ ነው የሚሆነው። በአጠቃላይ የሲቪሉ ማህበረሰብ፣ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ የፈጠረውን ዕድል በመጠም መርሆቹን ራሱ ተግባራዊ በማድረግ መጫወት ይችላል። መንግሥት የሚያወጣው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ገና በመዘጋጀት ላይ ነው። ዝግጅቱ ተጠናቆ ሲወጣ ምን ምን ፖሊሲዎችን እንደሚይዝ ካሁኑ የሚታወቅ ነገር የለም። ዳሩ ግን በሰነዱ አዘገጃጀት ሂደት፣ ቀደም ሲል ባቀረብኩት ጽሁፍ ላይ እንደገለጽኩት፣ በመጀመሪያ የድህነት ትንተና ይካሄዳል። ከዚያ ደግሞ የፖሊሲ ትንተና ይካሄዳል። የፖሊሲ ትንተና ሲካሄድ አሁን በሥራ ላይ ያሉት ፖሊሲዎች የሚታዩበት፣ እስካሁን ያስገኙት ውጤት የሚገመገምበት፣

CCRDA

ክፍተቶች ካሉ መሻሻል ወይም መለወጥ ያለባቸው ነገሮች ካሉ፣ ሕብረተሰቡ ጠቁሞ እንዲካተቱ የሚደረግበት ይሆናል ተብሎ ይታመናል።



ተሳታፊ፡- ዕድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ። ጥያቄዬ አቶ ጌታሁን ቀደም ሲል ባቀረቡት ወረቀት ላይ፣ ህብረተሰቡም ሆነ ሌላው አካል የራሱ የሆነ ሚና ሊጫወት ይገባል፣ መንግሥት ተሳተፉ እስኪል ድረስ መጠበቅ የለበትም የሚል ነገር አንስተዋል። ጥሩ ሃሳብ ነው። ከዚህ አንፃር፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳተፉ እስኪባሉ ድረስ ሳይጠብቁ ለምድነው ስለድህነት ቅነሳ ስልቱ ቀደም ሲል በራሳቸው መንገድ ያልተወያዩት? አሁንስ ተቋቋመ የተባለው ግብረ ኃይል አልዘገየም ወይ? ምክንያቱም ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር አንፃር ስናይ፣ ተሳተፉ የሚል ነገር ሳይመጣ በራሳችው የራሳቸው የሆነ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ አዘጋጅተው እንደአማራጭ ለመንግሥት አቅርበዋል። እና ይህ ከመያዶች አንፃር እንዴት ይታያል?

ፓነል አቅራቢ፡- መያዶች ተሳተፉ እስኪባሉ ድረስ ሳይጠብቁ ለምንድነው ስለስልቱ በራሳቸው መንገድ ያልተወያዩት? የሚል ጥያቄ ቀርቧል። በፌዴራል ደረጃ የክርስቲያን በጎ አድራጐት ድርጅት መያዶችን አስተባብሮ አንድ የድህነት ቅነሳ ስልት ግብረኃይል አቋቁሟል። ከዚያም አልፎ መንግሥት ላይ ግፊት በማድረግ አንዳንድ ጥያቄዎችን እያቀረበ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ቀደም ሲል የተለያዩ ዓውደ ጥናቶችን አካሂዷል። ይሄ ራሱ እንደ ተሳትፎ ሊወሰድ ይችላል።

CCRDA

ተሳታፊ፡- ወ/ሮ ሮማን ያቀረቡት ጽሁፍ ርዕስ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳው ሊጫወቱት የሚገባቸው ሚና ምን ይሁን በሚል ርዕስ ሥር ሆኖ፣ እሳቸው ያቀረቡት የቴክኒክ ኮሚቴው ለአስተባባሪ ኮሚቴው ያቀረበው ሪፖርት ዓይነት ነው። በደቡብ ክልል ያሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምን ምን አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይገባል? የሚለውን ነገር ከነአካቴው አላነሱትም። በየወረዳዎች የመወያየቱ ጉዳይ ተነስቷል። ይሁን እንጂ ጉዳዮቹ ቅደም ተከተል ይዘው አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ ተብለው አልቀረቡም። ሪፖርቱ እንደዚህ በድምሰሳው መቅረብ አልነበረበትም። ምክንያቱም ይሄ አጋጣሚ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ግብረሰናይ ድርጅቶች የተሳተፉበት ስለሆነ ጥሩ አጋጣሚ ነበርና ነው። ታዲያ የአቀራረቡ ጉድለት ከምን የተፈጠረ ነው?

ፓነል አቅራቢ፡- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ ሊጫወቱ የሚገባቸው ሚና በዝርዝር አልቀረበም ተብሎ ለቀረበው አስተያየት፣ ምናልባት ሰዓቱ ተገድቦ ስለተሰጠኝ በዝርዝር ሳልገልጸው ቀርቼ ይሆናል። በውይይቱ ሂደት በሚኖራቸው አስተዋፅኦ በክልል ምክክር ወቅት እንዲሳተፉ ወደ 20 የሚሆኑ የመያዶች ተወካዮችን መርጠናል። እነዚህ ተወካዮች በክልሉ ለሦስት ቀናት በሚካሄደው ምክክር የሚሳተፉ ናቸው። ከዚያ በ□ላም በፌዴራሉ ምክክር ወቅት የመያድ ተሳታፊዎች ቁጥር በጣም ትልቁ እንደሆነ ከሰቅዱ ላይ አይቻለሁ። ማንኛውም የልማት ድርጅት መጀመሪያ ያመነበትን ነገር ነው ወደ ተግባር የሚተረጉመው። በዚህ ረገድ መያዶችን እንደምናሳትፍ ግልፅ ነው። አሚልቼ ያልመለስኩት ካለ በተሳታፊነት የተካፈሉት የሥራ ባልደረቦቼ ሊያግዙኝ ይችላሉ።

ተሳታፊ /ከደቡብ ክልል መስተዳድር/፡- እንግዲህ የዚህ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት ከመጀመሩ በፊት በክልላችን ባለፈው ዓመት በራሳችን ተነሳሽነት የጀመርነው ነገር ነበር። «ሥራ አጥነትና ድህነት በደቡብሚ ብለን፣ በጣም ከባድ ችግር ያሉባቸውን ዞኖች መርጠን፣ እስከ 500 የሚሆኑ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮችን በማሳተፍ ችግሩ የሚቃለልበትን ሁኔታ በክልል ደረጃ ተወያየን። ዶሐር ሽመልስ እንዳሉት የድህነት መገለጫው የኢኮኖሚ ድቀት ብቻ አይደለም። በጣም የሚያሳስበን የመንፈስ ድህነቱም ነው። ከሞራልና ከሃይማኖት ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል የነበረው ማህበራዊ እሴት እየተሸረሸረ በመሄድ ላይ ነው። የመተባበሩና የመደጋገፉ ባህል እየተሸረሸረ ወደ ማህበራዊ ቀውስ የመግባት አዝማሚያ የታየበት ሁኔታ ተከስቶ አይተናል። እጅግ በጣም የሚያስፈራ ሁኔታ ነው።

CCRDA

እንግዲህ ድህነት በምንልበት ጊዜ፣ ከኢኮኖሚና ማህበራዊ ቀውስ ባሻገር፣ ሞራሉ የላሸቀ፣ ክብሩም የወደቀ ደረጃ ላይ የደረሰ ዜጋ ይዞ እንዴት መሄድ ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ የመመለስ ወይም ያለመመለስ ሁኔታ ይኖራል። ይሄንን ይዘን የተወሰኑ ሥራዎችን እየሠራን እያለን ነው፣ የድህነት ቅነሳ ስልት በአገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው። ለእኛ ጥሩ ነገር ነው። ቢያንስ ቢያንስ አንድ አቅጣጫ ይዘን ሥራውን ማካሄድ ጀምረናል። ትናንትም፣ ዛሬም በምናገኘው ብዙ እየተማርን እየተሻሻልን እንደምንሄድ ነው የምንገምተው። አንድ ቦታ አይቆምም። ምክክር ጀምረናል። ወደ ተሳትፎ እንዴት እንሂድ? ነው ጥያቄው። ሕዝብን በተጨባጭ ማሳተፍ ወሳኝ ነው።

መንግሥትም፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በጠቅላላውም የሲቪል ማህበረሰቡ ድርጅቶች በተደራጀ መልክና በግል፣ ተረባርበን መዝለቅ አለብን። ሥራው ተጀምሯልና አንድ ቦታ የሚቆም አይደለም። በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ ነው። መጀመሩ ለሁላችንም እሰይ የሚያሰኝ ነው። መቼም እየሠራን እንማራለን፣ እየተማርን እንሠራለን። በዚህም የልማት አጋሮቻችንን እናሳትፋለን፣ ተሳትፏቸውንም እናጠናክራለን። በዚህ በኩል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም፣ የሲቪል ማህበረሰቦችም፣ የሙያ ማህበራትም አንዱ የአንዱን በር ያንኳኳ፣ የመንግሥትን በር ያንኳኳ፣ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ይህን ቢያደርግ ጥሩ ሥራ መሥራት እንችላለን የሚል እምነት አለኝ። አመሰግናለሁ።

አወያይ፡- ለዚህ አበረታች አስተያየት አመሰግናለሁ። እንደምታስታውሱት በዚህ በመያድ ዓለም ሆነን የዛሬ 3 እና 4 ዓመት በሕልማችን እንኳን የማናስባቸውን ነገሮች፣ ዛሬ በእውነት እያየን ነው ያለነው። ከፌዴራል ደረጃ፣ ከክልል ደረጃ የሚወከሉ ባለሥልጣናት ስብሰባችን ላይ ተገኝተው የሚሰጡትን ሃሣብ የኖርንበት ሰዎች የምናውቀው ነው። እናም ይሄ የዛሬው በጣም አበረታች ይመስለኛል። እንደተባለው ጅምር ነው። ይሄን ጅምር አጥብቀን ይዘን ወደ ጫፍ የማድረሱ ነገር የእኛ ኃላፊነት ነው። አስተያየት ሰጭው እንዳሉት የመያዶች በር መንኳኳት አለበት። እኛም ደግሞ የሌሎችን ሴክተሮች በር ማንኳኳት መቀጠል አለብን። ቁጭ ብሎ በመጠበቅ የሚመጣ ነገር ያለ አይመስለኝም። ቀደም ሲል መያዶች መጠነኛ የግንዛቤ ማነስ ነበረን። ስለሆነም የድህነት ቅነሳ ስልት የሚባለው ነገር ምንድነው? የሚል ጥያቄ ነበረንና ለመነጋገር ዓውደ ጥናቶችን አዘጋጀን። በዚህ ዓመት ሁለት

CCRDA

ዓውደ ጥናቶች ተካሂደዋል። ግንዛቤ በጨመረ ቁጥር የተሳትፎም ይሁን ዕንሰ ሃሳቡን የመረዳት ችግሮች ይቀረፋሉ የሚል እምነት ነው ያለን። የግንዛቤ ማሳደጊያና መያዶች በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት የሚኖራቸው ተሳትፎ የሚሉ ዓውደ ጥናቶችን አካሂደናል። ሪፖርቶቹን የክርስቲያን በጎ አድራጐትና የልማት ድርጅት ቤተመጻሕፍት ውስጥ ወይም እዚህ አዋሳ ውስጥ ከሲ.አር.ዲ.ኤ ሌይዘን ኦፊሰር ቢሮ ማግኘትና ማንበብ ትችላላችሁ።

ተሳታፊ፡- ቅድም የመጀመሪያው አቅራቢ ሁለት ተፈታታኝ ችግሮችን ጠቅሰዋል። አንደኛ የመንፈስ ድህነት አለ ብለዋል። ሁለተኛ ደግሞ የድህነት ቅነሳ ስልት አጀንዳው የእኛ አይደለም ብለዋል። እና እነዚህ ሁለት ችግሮች እያሉ የመያዶች አስተዋፅኦ እንዴት አድርጐ ነው የጎላ የሚሆነው?

ፓነል አቅራቢ፡- የተጠየቅኩት ጥያቄ ስልቱ የእኛ አይደለም ስለተባለው ነው። አሁንም ቢሆን የእኛ አይደለም። እንዲያም ሆኖ ግን ራሴን መድገም ባይሆንብኝ፣ ድህነት በእኛ አገር በከፋ መልኩ ብቸኛ ችግር ነው። ሌላው ከሱ የበለጠ ችግር ወሬና ፖለቲካ ነው። ድህነትን በማስወገድ ላይ የሁላችንም ስምምነት አለ። በአይዶሎጂ ሳይከፋፈል፣ በጐሳ፣ በዘር፣ በዚያ ወጥቶ በዚህ ወርዶ ሳይባል፣ ድህነትን ለመቅረፍ አብረን እንረባረብ ቢባል የሚጠላ ወይም የሚቃወም ሰው አይኖርም። አሁን በመንግሥት በወጣው ጊዜያዊ ሰነድ ላይ ብዙ ሴክተሮች ተዘርዝረዋል። ማዕከላዊው የሆነው የፓርቲው ፖሊሲ መፍትሄ ሆኖ ቀርቧል። የኢኮኖሚ ልማት ከሌለ መሬት አጥ ደሃ ገበሬውንና የከተማውን ሥራ አጥ ሕይወት በምንም አይነት መንገድ ልናሻሽለው አንችልም። የዲሞክራሲውም ጥያቄ ከዚሁ ጋር አብሮ የሚነሳ ይመሰለኛል። ለምሳሌ የተሳትፎን ጥያቄ ስናነሳ የዲሞክራሲን ጥያቄ ነው የምናነሳው። ተሳትፎአችን በደንብ ይሁን፣ እንግባበት እና አብረን እንሥራ የሚል ጥያቄ ይኖራል። ያኔ የመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ መኖር አለመኖር ይረጋገጣል።

ተሳታፊ፡- እኔ የመጣሁት ከሲዳማ ዞን ህብረት ሥራ ጽሕፈት ቤት ነው። መያዶች በጤና ዘርፍ፣ በትምህርት ዘርፍ፣ በግብርና ዘርፍ በአብዛኛው ሲሳተፉ እናያቸዋለን። ይሄ ጥሩ ሆኖ ሳለ የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች በሕብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ሀገሪቷንም ሆነ ራሳቸውን መጥቀም የሚችሉበት ደረጃ ላይ የማድረሱ ሁኔታ የተዘነጋ ይመስላል። የሰዎችን ችግር እናቃል ካልን፣ ልክ እንጨት ተለቅሞ ማሰሪያ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ግለሰቦችን

GCRDA

አደራጅተን ዘላቂ መፍትሄ ሊፈጥሩ በሚችሉበት መንገድ ማደራጀት ይገባናል። ስለዚህ ጉዳይ ሁላችንም የምናውቀው ነገር አለ። መንግሥትም በጣም የተቸገረበት ነው። ብዙ ገበሬ ምርት ያመርታል። ያንን ምርት ግን በጣም ከፍተኛ ርቀት ያለው ቦታ ላይ አምጥቶ በመሸጥ የአባላቶቹን ችግር መፍታት የሚችለው የሕብረት ሥራ ማህበር ነው። ነገር ግን ያ ሁሉ ባለመደራጀቱ ወይም ሌላ መዋቅር ባለመዘርጋቱ፣ መንግሥት ብቻውን ችግሩን ሊያቃልላቸው አልቻለም። ስለዚህ ይህ ችግር በመንግሥት ብቻ ወይም በአደራጁ ብቻ የሚፈታ ችግር ሆኖ አልተገኘም። መያዶች በሌላው ልማት እንደሚሳተፉ ሁሉ በዚህ ላይ ቢሳተፉ ለገበሬው ሕይወት መሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብዬ አምናለሁ። ያቀረብኩት ጥያቄ ሳይሆን አስተያየት ነው። አመሰግናለሁ።

አወያዩ አቶ ከበደ አሥራት «በድህነት ቅነሳ የመያዶች ሚናና አስተዋፅኦ» በሚል ርዕስ በቀረቡት ጽሁፎች ላይ የተካሄደው ውይይት መፈጸሙን ገልጸው፣ የጽሁፍ አቅራቢዎቹንና ተሳታፊዎችን ካመሰገኑ በኋላ የዕለቱ ፕሮግራም በ7:00 ሰዓት ላይ ተጠናቋል።

CCRDA

የሦስተኛው ቀን የፓነል ውይይት

ቀን፣ ታህሣሥ 6 ቀን 1994 ዓ.ም.

ሰዓት፣ ከ3:00 - 6:30 /ጠዋት/

ርዕስ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደርና በሰላም ግንባታ ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ

የፎረሙ አስተባባሪ፣ አቶ ፍቅሬ ዘውዴ

አወያይ፣ አቶ ደሳለኝ ራህመቶ

የፓነል አቅራቢዎች፣

ዶክተር ሙሉጌታ ኢተፋ /ከሰላምና ልማት ድርጅት/

አቶ ዩሱፍ ሀሰን /ከሰላምና ልማት ድርጅት/

ዶክተር ዓለማየሁ አረዳ /ከአዲስ የምክርና የሥልጠና አገልግሎት/

2.3 ዐቢይ ርዕስ፡- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደርና በሰላም ግንባታ ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ

አወያዩ አቶ ደሳለኝ ራህመቶ የፓነል አቅራቢዎቹንና ተሳታፊ እንግዶችን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ፣ ለፓነል ውይይት የቀረበው ጽሁፍ «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመልካም አስተዳደርና በሰላም ግንባታ ያላቸው ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ» የሚል መሆኑን ገለጹ። ከዚያም ዶክተር ዓለማየሁ አረዳ፣ የመጀመሪያው ተናጋሪ በመሆን ጽሁፋቸውን እንዲያቀርቡ ጋበዙ። የዶክተር ዓለማየሁ ያቀረቡት የውይይት መነሻ ጽሁፍ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው።

2.3.1 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- መያዶች ለዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ ያላቸው ሚናና አስተዋፅኦ

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ግንባታ ውስጥ ምን ሚና አላቸው? ብሎ ሲታሰብ፣ የቅርብ ጊዜ ጅማሮ ይመስለኛል። ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር በቁርኝት ሲነሱ ሃያ ዓመት ገደማ ሆኗቸዋል። እነዚህን ጠቃሚ ማህበራዊ እሴቶች ለመገንባትና እንዲዳብሩ ለማድረግ፣ የሲቪል ማህበረሰቡ መሳተፍ አለበት። ሲቪል ማህበረሰቡ የማይተካ ሚና አለው ሲባል የቅርብ ጊዜ አመለካከት ይመስለኛል። ለአፍሪካ፣ በተለይም ለኢትዮጵያ ማለቴ ነው። በሌላው ዓለም ሲቪል ማህበረሰቦች እንዲያውም ይሳተፉ አይሳተፉም ከሚለው ጥያቄ አልፈው፣ በቀጥታ

CGRDA

የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስንል የፅንሰ ሃሳብ መራራቅ እንዳይኖር፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የምንላቸው ምንድናቸው? ዲሞክራሲ ስንል ምን ማለታችን ነው? መልካም አስተዳደር ምንድነው? የእነዚህ ተዛምዶ እንዴት ነው? የት ላይ ነው የሚገናኙት? መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የማይተካ ሚና እንዴት ነው የሚገለጸው? እነዚህን ነጥብ በነጥብ አንስቼ ለመግለጽ እሞክራለሁ።

ሲቪል ማሕበረሰብ የሚለው ንዑስ ሐረግ የሚወክለው ፅንሰ ሃሳብ በመንግሥት አካላትና በግሉ ዘርፍ መካከል ያለውን ሰፊ ሕብረተሰብ ያካተተ እንደሆነ ይገለጻል። ይሄ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጥቅም ዙሪያ በራሱ ፍላጐት ተሰባስቦ የሚገኝ ሕብረተሰብ፣ ለመንግሥትም ሆነ ለግሉ ዘርፍ ደንበኛ ነው። ሁለቱም በሚያቀርቡት አገልግሎትና እቃ ይጠቀማል።

በዚህ ሰፊ ሕብረተሰብ ውስጥ ልማዳዊ የሆኑ ማህበራዊ ተቋማት ይገኛሉ። ስለሆነም የሲቪል ማሕበረሰቡ፣ ልዩ ልዩ ዓላማዎችን የሚያራምዱ ሕጋዊና ልማዳዊ በሆኑ አደረጃጀቶች የተቋቋሙ ድርጅቶችና ማሕበራት ያሉበት ነው። ከእነዚህም መካከል ለኢኮኖሚያዊ ጥቅም የተቋቋሙ፣ ባህልን ለመጠበቅና ለማሳደግ የተቋቋሙ፣ መረጃን፣ ትምህርትን ለማሠራጨት የተቋቋሙ፣ ጥቅማቸውን ለማስከበር የተቋቋሙና ልማትን መሠረት አድርገው የተቋቋሙ ይገኙባቸዋል። ከሲቪል ማህበረሰቡ ውስጥ እየተደራጁ የሚመጡ አካላት አሉ። መደራጀት ለማንኛውም ህብረተሰብ ክፍል መሠረታዊ ጥቅሙን ለማግኘት ትልቅ መሣሪያ ነው። ሕብረተሰብ ካልተደራጀ ለምንም ነገር አይበጅም። መንግሥት ራሱ ሕብረተሰብ የሚፈጥረው አንድ የአደረጃጀት ቅርፅ ሆኖ፣ የማሕበራዊ ትብብር መመሥረቻ እንዲሆን የተፈጠረ መሣሪያ ነው። ስለዚህ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲደራጁ፣ በሕብረተሰብ እድገት ውስጥ እንደአስፈላጊ ነገር የሚመጡ ናቸው እንጂ፣ ጥቂት በጎ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ስላሉ የሚደራጁ፣ በጎ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ከሌሉ የማይደራጁ ዓይነት ነገር አይደሉም።

ስለዲሞክራሲ ስናነሳ ደግሞ፣ ዲሞክራሲን ከነፃነት ጋር እያነፃፀርን ማየት ይኖርብናል። ምክንያቱም ብዙዎቻችን ዲሞክራሲና ነፃነት አንድ ሊመስለን ይችላል። በዲሞክራሲና በነፃነት መካከል ያለው ግንኙነት በሚፈልጉት ነገርና ያንን ነገር ለማግኘት በሚጠቀሙበት መሣሪያ መካከል ያለውን ዓይነት ልዩነት ይታይበታል። ነፃነት፣ ማግኘት ወይም መሆን የምንፈልገው ነገር ነው። ሰብአዊ መብቶቻችን ተጠብቀው፣ ተከብረን መኖር እንፈልጋለን። ሃሳባችንንና እምነታችንን ያለአንዳች ተፅዕኖ መግለጽ እንፈልጋለን። የንብረት ባለቤት መሆን እንፈልጋለን። እነዚህንና ሌሎች ማህበራዊና ግላዊ ፍላጐቶችን

CCRDA

በተሟላ ሁኔታ ማግኘት በራሱ ነፃነት ነው። ዲሞክራሲ፣ ማግኘት የምንፈልጋቸውን ማህበራዊና ግላዊ መብቶችና ጥቅሞች በተነፃፀረና በተቻቻለ ሁኔታ እንድናገኝ የሚያስችለን ሥርዓት ነው። በሌላ አባባል፣ ዲሞክራሲ ነፃነትን ተቋማዊ ማድረጊያ መሣሪያ ነው። የተለያዩ ፍላጐቶችና ጥቅሞች ባሉበት ሕብረተሰብ ውስጥ ፍፁም ነፃነት የለም። ፍፁም ነፃነት ከሌለ ደግሞ፣ የተቻቻለና የተነፃፀረ ነፃነት ነው ያለው ማለት ነው። ዲሞክራሲም ያንን የተቻቸለና የተቀራረበ ነፃነት ነው የሚያረጋግጠው።


ዲሞክራሲ ምንም እንከን የማይወጣለት ንፁህ ሥርዓት ነው ማለት አይደለም። ሰው የሠራው ነገር ሁሉ ትንሽ ድክመት ይኖረዋል። ዳሩ ግን፣ ዲሞክራሲ ምንም ዓይነት ቅዕል ቢሰጠው፣ ምንም አማራጭ የለውም። የብዙሃን የበላይነት አለ፣ ግን የአናሳዎች መብት መከበር አለበት። የመቻቻልና በሰላማዊ መንገድ ችግሮችን የመፍታት ነገር መኖር አለበት። ምክንያቱም ነፃነት ፍፁም አይደለም፣ የተቻቻለ ነው ካልን፣ ማቻቻያ መሣሪያው ዲሞክራሲ ነው። ዲሞክራሲ ከተባለ ግልጽ የሆነና ነፃ ምርጫ መኖር አለበት። አማራጭ ሃሳቦችም መኖር አለባቸው። አማራጭ ፓርቲዎች መኖር አለባቸው። በነፃነት የመደራጀት መብቱ መኖር አለበት። ዲሞክራሲ ሥልጣንን ሕጋዊ ማድረጊያ ብቻ አይደለም። እራሱን ሥልጣንን መቆጣጠሪያ መሣሪያ ነው።

ሌላው ደግሞ፣ ዲሞክራሲ ስንል፣ ሥልጣን ያለምንም ደም፣ ያለምንም ጠብ፣ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲሸጋገር የሚያደርግ ሥርዓት ነው። እነዚህን ካሟላ ዲሞክራሲ ይሆናል። የዲሞክራሲ ባህሪያት በምልዓት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት ደግሞ፣ መብቶቹን በተገነዘበና ለእነሱም መከበር ሳያሠልስ በሚታገል ሕብረተሰብ ነው።

መልካም አስተዳደርን ስናይ ደግሞ፣ መልካም አስተዳደር እኛ በምንነጋገርበት ፅንሰ ሃሳብ መሠረት የሚታይ ነው። አስተዳደርና መልካም አስተዳደር ልዩነት አላቸው። መልካም አስተዳደር አንድ አገር የሚመራበትን፣ የሚተዳደርበትን ጥቅል ማህበራዊ ሥልጣን የሚያመለክት ሲሆን፣ በውስጡም ዜጐች ፍላጐታቸውን የሚገልፁባቸውን፣ ሕጋዊ መብቶቻቸውን የሚያስከብሩባቸውንና ልዩነቶታቸውን አቻችለው የሚኖሩባቸውን ውስብስብ አሠራሮችን፣ ሂደቶችንና ተቋማትን ያጠቃልላሉ። በመሆኑም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሕጋዊ፣ የፍትሕ፣ የማሕበራዊና መስተዳድራዊ ሥልጣናትን አካቶ የሚይዝ ነው። መልካም አስተዳደር በፖለቲካው መልኩ ብቻ በሚታይበት ጊዜ፣ መንግሥትና የመንግሥት አካላት ብቻ ነበሩ የመልካም አስተዳደር ዋነኛ ተወካዩች ተብለው የሚወሰዱት። በኋላ ግን የግሉ ዘርፍ እያየለ ሲሄድ፣ ከእነዚያ ጋር አብሮ እንዲጨመር ተደርጓል። የግሉ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን፣ የሲቪል ማህበረሰቡም በልዩ ልዩ ደረጃ እየተደራጀ ሲመጣና ኃያል መሆኑን ሲያሳይ፣ ሦስተኛ ምሰሶ ተደርጐ ታይቷል።

CGPDA

አስተዳደር የትም ሊኖር ይችላል። በማንኛውም ሥርዓት ሊኖር ይችላል። መልካም አስተዳደር ግን በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ብቻ ነው የሚኖረው። የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ተዛምዶም ይኸው ነው። የዲሞክራሲ አምስት መሠረታዊ ይዘቶች የሚባሉ አሉ። ከእነዚህ አምስት መሠረታዊ ይዘቶች አንዱ መልካም አስተዳደር ነው።



አያሌ ምሁራን፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በአግባቡ እንዲኖር፣ ማህበራዊ ስምምነት መኖር አለበት ይላሉ። ለምሳሌ እዚህ ካለነው ውስጥ አንኳን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይጠቅማሉ፣ አይጠቅሙም በሚለው ላይ አብዛኛዎቻችን ይጠቅማሉ ካልን፣ ስምምነት ወይም ኮንሴንሰስ አለ ማለት ነው። አብዛኛዎቻችን አይጠቅሙም ካልንም አሉታዊ በሆነ መልኩ ቢሆንም፣ ስምምነት አለ ማለት ነው። ይጠቅማሉ፣ አይጠቅሙም የሚለው ዝብርቅርቅ ካለ ግን፣ ስምምነት ወይም ኮንሴንሰስ የሚባል ነገር የለም። ስለዚህ በአንድ አገር ውስጥ አንድ መሠረታዊ የሆነ ጥያቄ ሲነሳ፣ ወሳኝ የሚሆነው በጥሩ ቋንቋ መነገሩ ወይም ሰዎች እንዲቀበሉት ግፊት መደረጉ አይደለም። ጥያቄው አብዛኛው ሰው ያ ነገር እውነት ነው ብሎ ይቀበላል ወይ? ነው። ካልተቀበለ ዋጋ የለውም። ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል። ሌላው የዲሞክራሲ ትልቁ ምሰሶ የሕግ የበላይነት መከበር ነው። ለምሳሌ በአንድ አገር ውስጥ የሕግ የበላይነት አለ ወይ? በሚለው ላይ ማህበረሰቡ ካልተስማማ፣ ማሕበራዊ ስምምነት የለም። አንድ ሥርዓት የሚኖረው ሕብረተሰቡ በሰላም እንዲኖር፣ አምርቶ ችግሮቹን እንዲወጣ እስከሆነ ድረስ፣ ሁሉም የየራሱን ድርሻ ሊያዋጣ የሚችልበት መድረክ አለ ወይ? ሥርዓቱ አሳታፊ ነወይ? ተብሎ ይገመገማል። በኢኮኖሚው ዘርፍም ነፃ ውድድር መኖር አለበት። ይሄ ሌላኛው ምሰሶ ነው። መልካም አስተዳደር ውስጥ ሲቪል ማህበረሰቦች አንዱ ምሰሶ ናቸው። ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ደግሞ የተሳሰሩ ናቸው። ስለዚህ ሲቪል ማህበረሰቡ እዚያ ውስጥ አለ።

CRDA

መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ አብረው ነው የሚሄዱት ካልን፣ አንዳንድ ጊዜ ዲሞክራሲ የመልካም አስተዳደር መንግሥታዊ ቅርጽ ነው ብለን መከራከር እንችላለን። ነገር ግን ማሟላት ያለበት ጉዳዮች አሉ። አሳታፊ መሆን አለበት። ግልጽ መሆን አለበት። ተጠያቂነት መኖር አለበት። ቅልፍጥና መኖር አለበት። እና ደግሞ የሕግ የበላይነት መኖር አለበት። እነዚህ ባሕሪያት ለመልካም አስተዳደር አስፈላጊ ነገሮች የሚባሉት ናቸው። እነዚህ ባሕሪያት ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ነው ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚተሳሰሩት። ከዚያ በተረፈ መልካም አስተዳደር ደግሞ የተለያዩ ገፅታዎች አሉት። የፖለቲካ ገፅታዎች አሉት። የኢኮኖሚ ገፅታዎች አሉት። ማህበራዊ ገፅታዎች አሉት። መስተዳድራዊ ገፅታዎች አሉት። አንድ ነገር ብቻ አይደለም። ከዚህም የተነሳ ሁሉም ሚናቸውን የሚጫወቱት በየገፅታው ነው። ለምሳሌ መያዶችን ብንመለድ፣ በአብዛኛው ማህበራዊው የሆነውን እሴት በማፍለቅና ኢኮኖሚያዊ ልማትን በማምጣት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። መንግሥትና የመንግሥት አካላት ደግሞ በአብዛኛው በፖለቲካው ዘርፍ ሚናቸውን ይጫወታሉ። የግል ዘርፉ ደግሞ ሚናውን በአብዛኛው በኢኮኖሚው ዘርፍ ይጫወታል። መልካም አስተዳደር ሊኖር የሚችለው እነዚህ ሚናዎች አንድ ላይ ሲቀናጁ ነው።

ዲሞክራሲን፣ መልካም አስተዳደርንና ሲቪል ማህበራትን የሚያገናኛቸው መሠረታዊ ነጥብ ደግሞ፣ ማህበራዊ ልማት ወይም ሰብአዊ ልማት የምንለው ነው። ሰብአዊ ልማት ሁሉን የሚያካትት ነው። ኢኮኖሚያዊ ብቻ አይደለም። በኢኮኖሚ መበልፀግ፣ የእለት ገቢ መጨመር ብቻ አይደለም። በመንፈስ መበልፀግ፣ በዲሞክራሲያዊ ነፃነት መበልፀግ፣ እርስ በርስ ተጋግዞ በመኖር መበልፀግ፣ በአብሮነት መበልፀግ፣ እነዚህ ሁሉ የሰብአዊ ልማት አካሎች ናቸው።

ሲቪል ማህበረሰቡ፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚገናኙት ሰብአዊ ልማት ላይ ነው። ትልቁ አንጓ ሰብአዊ ልማት ነው። እናም ዲሞክራሲ በሌለበት መልካም አስተዳደር የለም። ሁለቱ ደግሞ በሌሉበት እውነተኛና ዘላቂ ማህበራዊ ልማት የለም። ዘላቂ ማህበራዊ ተሳትፎ በሌለበት ደግሞ፣ ሁሉም የሉም። ስለዚህ የሲቪል ማህበረሰቦች ትልቁ አስተዋፅኦ ተሳትፎ ነው። በነጠላ ከመሳተፍ ተደራጅቶ መሳተፍ፡ ይሻላል የሚለው አመለካከት እጅግ ጉልቶ የሚታየው መንግሥታዊ ባልሆኑት ድርጅቶች ውስጥ ነው። በመሆኑም ያ ተሳትፎ ሁሉን አቀፍ በሆነ መንገድ ከሌለ በስተቀር፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚባሉት ነገሮች ሁልጊዜ እንደስጠታ የሚጠበቁ ነገሮች ይሆናሉ።

እንግዲህ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሚናና አስተዋፅኦ ከዚህ አንፃር ነው የምንመለከተው። ለዚህም ነው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚና ምትክ የለውም

CCRDA

የሚባለው። መንግሥት እኔ ብቻ ልሥራው ቢል አይችልም። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሲቪል ማህበረሰቡ ውስጥ የፈለቁና የተደራጁ አካላት ናቸው እንጂ ባዕድ ነገሮች አይደሉም። ስለዚህ፣ የአጠቃላዩን ሲቪል ማህበረሰብ፣ በትንሹም ቢሆን በተደራጀ መልክ የሱን ተሳትፎ ይወክላሉ። እንከን የላቸውም፣ ድክመት የላቸውም አላልኩም። ነገር ግን ከአፈጣጠራቸው በተደራጀ መልክ የአጠቃላይ የድምሩን ሕብረተሰብ ማህበራዊ ተሳትፎ ይወክላሉ። እናም ዲሞክራሲን በመገንባት ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው። ዲሞክራሲ የሚገነባው በሬዲዮና በቴሌቪዥን በመንገር አይደለም። ወይም ደግሞ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ስብሰባ እያደረገ ስለተናገረ አይደለም። በእንቅስቃሴ፣ በአስተሳሰብ፣ እንዲሁም ከሌሎች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ዲሞክራሲ ሊበለጽግ ይችላል።

ሲቪል ማህበረሰቦች ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አብሮነትን ያጐለብታሉ። የፍትሕ ሥርዓቱን በማሻሻል ረገድ ይረዳሉ። ድህነትን በመዋጋትም ይረዳሉ። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ድርጅቶች ጠንካራም ደካማም የምንላቸው ጐኖች ሊኖሯቸው ይችላሉ። ጠንካራ ጐናቸው፣ የሲቪል ማህበረሰቡን ንቃተ ሕሊናና ራሱን የመርዳት እንቅስቃሴ ማጐልበታቸው፣ ማህበራዊ ካፒታል ወይም ሶሻል ካፒታል እንዲፈጠርና የተሳትፎ አሠራር እንዲጐለብት ማድረጋቸው ነው። ድክመታቸውን ስናነሳም፣ ያሉበት ሕብረተሰብ ውጤት በመሆናቸው፣ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ድክመቶች እነሱም ጋር ሊኖሩ ይችላሉ። ስለግልጽነት እየተናገሩ በውስጥ አሠራራቸው ግልጽ ላይሆኑ ይችላሉ። ስለተሳትፎ እየተናገሩ፣ ተሳትፎን በወረቀት ወይም በቃል ብቻ ሊገድቡ ይችላሉ። እና እነዚህ ሁሉ ድክመቶቻቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከሁሉም በላይ ግን የአቅም ችግር ነው ያለባቸው። ዘለቅ ባለ ሁኔታ ስንመለከተው፣ ውጫዊም ውስጣዊም የሆኑ ችግሮች አሉዋቸው። ካሉበት ሕብረተሰብ ባሕልና የእድገት ደረጃ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚከሰቱ ችግሮች አሉ። የቢሮክራሲ ጫና ችግር ሊሆን ይችላል። ከሕዝብ ጋር ባላቸው መቀራረብ የተነሳ ተግባራቸው ከፖለቲካ ጋር መፈረጅና አንዳንዴም በጥርጣሬ ዓይን የመታየት ችግር ሊኖርባቸው ይችላል።

እንግዲህ እስካሁን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ መልካም አስተዳደር፣ ሰብአዊ ልማት፣ ማህበራዊ ተሳትፎ እንዴት እንደተቆራኙ ለማሳየት የሞከርኩ ይመስለኛል። የሲቪል ማህበረሰቡ ሚና በምንም ዓይነት የማይተካና ሁሉን አቀፍ ወይም ሁለገብ እንደሆነ ለማሳየትም የሞከርኩ ይመስለኛል። ሌሎች ያልተዳሰሱ ነጥቦች ካሉ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ እናነሳቸዋለን። ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

CCRDA

አወያዩ አቶ ደሳለኝ ራህመቶ፣ ዶክተር ዓለማየሁ አረዳ ላቀረቡት ሰፋ ያለ ግንዛቤ የሚሰጥ ጽሁፍ በፎረሙ ተሳታፊዎች ስም አመሰግነው፣ የሚቀጥሉትን ተናጋሪ ዶክተር ሙሉጌታ ኢተፋን ጋበዙ። ዶክተር ሙሉጌታ ያቀረቡት የውይይት መነሻ ጽሁፍ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ነው።

2.3.2 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- ሰላምን በማስፈንና በማዳበር ረገድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚና

እኔ የማቀርበው ጽሁፍ የሚያተኩረው፣ ሰላምን ለማስፈን ወይም ሰላምን ለማዳበር ምን ማድረግ ይገባል? በሚለው ላይ ነው። ሰላምን የማስፈን ሥራ፣ ሕብረተሰቡን በሙሉ በተቻለ መጠን የሚያሳትፍ መሆን ይኖርበታል። ከከፍተኛ ባለሥልጣን ጀምሮ፣ እስከ ተራ ገበሬና ተራ ነጋዴ ያለው ሕብረተሰብ ለሰላም መቆምና ለሰላም መሥራት ይገደዳሉ። ምክንያቱም ሰላም የሁሉም ሰው ፍላጐት ነው። የአንድ ወገን ፍላጐት ብቻ ሊሆን አይችልም። እርግጥ ሁለም ሰላም ፈላጊ ቢሆንም፣ ለሰላም ለመሥራት ዝግጁ የሆኑ ሰዎች ግን የተወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ ሰላምን ለማስፈን መሥራት የሚፈልጉ ሰዎች ሕብረተሰቡን የሚያውቁና በመሀከላቸው ያሉትንም ችግሮችና የችግሮቹን መንስኤዎች የሚያውቁ፣ በሕብረተሰቡም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

ግጭትን እንዲሁ እናቆማለን ማለት አይቻልም። ለግጭት መነሾ የሆኑትን ነገሮች አንድ በአንድ ማየትና መመርመር ያስፈልጋል። ምክንያቱም መንስኤዎቹ የተወሳሰቡ ሊሆኑ ይችላሉ። ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። በሕብረተሰቡ ውስጥ የፍትሕ መኖርን ማረጋገጥና ተጠያቂነት መኖር አለበት። ተጠያቂነት ከሌለ ሰላም ሊኖር አይችልም። የሕግ የበላይነት ከሌለም ሰላም ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም ሁልጊዜም ፍትሕ አጣሁ የሚል ሰው ግጭትን ይፈጥራል። ስለሆነም ፍትሕ የሰላም መሠረት ነው ማለት ይቻላል። የተጋጩ ወገኖች፣ የሰላም መኖር የሁላችንም ጥቅም ነው ብለው ማመን ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ሰላም አይጠቅመንም ካልን፣ ሰላምን ማምጣት አንችልም። ይሄም ሲባል በሰላም መደፍረስ ጥቅም ያላቸው ሰዎች አይኖሩም ማለት አይደለም። በሰላም መደፍረስ ጥቅም እንዲኖራቸው የሚፈልጉትን ግን ሕብረተሰቡ መዋጋት ይኖርበታል። ሰላም ከሌለ የሁላችንም ጉዳት ነው ብሎ የቆመ ሕብረተሰብ ያስፈልገናል።

CCRDA

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለግጭት መንስኤ የሚሆኑትን ችግሮች ለመቅረፍ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህንንም ለማድረግ የሥራ ክፍፍልና ቅንብር መኖር አለበት። ለዚህም ደግሞ፣ ተመሳሳይ ሥራ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጉልበታቸውን፣ ሀብታቸውንና እውቀታቸውን በማቀናጀት በተጠናከረ ሁኔታ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትብብርና ቅንጅት ከማድረጋቸው በፊት፣ ማን ምን እንደሚሠራ መታወቅ አለበት። ይሄ ከተደረገ በኋላ በጋራ በመንቀሳቀስ ውጤት ያለው ሥራ መሥራት ይቻላል። በቅንጅት ከተሠራ፣ ጊዜያዊ የሰላም ሁኔታንና ዘላቂ የሰላም ሁኔታን መለየት ያስችላል።

በአዳጊ አገሮች ውስጥ ሰብአዊ መብቶች ብዙውን ጊዜ በወረቀት ላይ በጥሩ ሁኔታ ይሰፍራሉ። በሥራ የሚተረጐሙባቸው ጊዜያት ግን በጣም ያነሱ ናቸው። ስለሆነም፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እነዚህ በሕገ መንግሥት ውስጥ የተቀመጡት መብቶችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ የሰብአዊ መብቶች ኮንቬንሽኖች እንዲጠበቁ ትልቅ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል። በጦርነትና በግጭት የሚጠመዱ ወገኖች ብዙውን ጊዜ የጋራ ዕድል ያላቸው ወገኖች ናቸው። ግጭት የሚኖረው በአንድ አገር ውስጥ ወይም ከጎረቤት አገር ጋር ስለሆነ፣ በግጭቱ የሚጠመዱ ወገኖች የጋራ ጥፋት ይጠብቃቸዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንግዲህ የትምህርትና የጤና አገልግሎት በተመሳሳይ መልኩ የሚዳረስበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። አድልዎ ባለበት ሕብረተሰብ ውስጥ ሰላም መኖር አይችልም። ሁኔታዎችን በየጊዜው በመመርመር የሰላም እንቅፋቶችን ለመቅረፍ አስፈላጊ የሆኑትን ስልቶች መቀየስ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ፣ የሰው ልጆች አብረው ሲኖሩ ግጭት ይኖራል። ግጭቶቹ እንዳይባባሱና ከፍተኛ ጉዳት እንዳያደርሱ፣ ወደ ጦርነትም እንዳያመሩ ነው እንቅስቃሴ የሚያስፈልገው። በሰላም መኖር፣ በሰላም ወጥቶ መግባት የሁሉም መብት ነው። የማንም ስጦታ አይደለም። ስለሆነም፣ ይሄን መብት ማሳወቅ ግዴታ ነው። ሰላም፣ ልማትና ፍትሕ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። ሰላም ከሌለ ልማት አይኖርም፣ ፍትሕ ከሌለ ደግሞ ሰላም አይኖርም። እንዲሁም የዲሞክራሲ አለመኖር፣ የሰው ልጆች መብት መረገጥ ካለ፣ የግጭት አዝማሚያ አለ ማለት ነው። ይሁን እንጂ የግጭት አዝማሚያን የሚያመለክቱት ነገሮች በጥናት፣ በምርምር ሊደረስባቸው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በግልጽ ይታያሉ።

እኛን የማይመስሉ፣ የእኛን ሃይማኖት የማይከተሉ፣ ጠላቶቻችን ናቸው ብሎ ማመን የጦርነትና የግጭት አዝማሚያን የሚያመለክት ነው። ሰላምን ማስፈን የጋራ ጥረት ውጤት በመሆኑ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጋራ ተንቀሳቅሰው ምንጊዜም የሰላም ግንባታ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። አመሰግናለሁ።

CCRDA

አወያዩ አቶ ደሳለኝ ራህመቶ፣ ዶክተር ሙሉጌታ ኢተፋ ላቀረቡት የውይይት መነሻ ጽሁፍ አመስግነው፣ የመጨረሻውን ተናጋሪ አቶ ዩሱፍ ሀሰን ዝግጅታቸውን እንዲያቀርቡ ጋበዙ። አቶ ዩሱፍ ያቀረቡት ጽሁፍ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው።

2.3.3 የፓነል አቅራቢው ርዕስ፡- የሰብአዊ መብትን ትምህርት በማስፋፋትና ሕግጋቱን ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ያላቸው ሚና፣ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦና የሚያጋጥሟቸው ችግሮች

የእኔ ርዕስ በሰብአዊ መብት ድርጅቶች ላይ ያተኮረ ነው። ሰብአዊ መብት ስንል በተፈጥሮ ያገኘነው፣ የተጐናፀፍነው ነፃነት ወይንም መብት ማለት ነው። ተፈጥሯዊ ሕግ ነው። በተፈጥሮ የተሰጠን እንጂ የሰው ችሮታ አይደለም። ስለሆነም አንዳንድ ሥርዓቶች ድሮውንም ያልነበሩትን ነገሮች አይደለም የሚሰጡን። አንዳንድ ጊዜ ሰብአዊ መብትን እንካ የሚልህ የለም፣ ራስህ በራስህ በትግልህ ታገኘዋለህ ነው የሚባለው። ለምሳሌ እሩቅ ሳንሄድ በአገራችን የሴቶች መብት በየጊዜው እየተሻሻለ መምጣቱን በደስታ የምንገነዘበው ነው። እና እንዲህ ዓይነት መብትና ነፃነት የሚገኘው ሴቶችና ሌላውም የሕብረተሰብ ክፍል ተደራጅተው በተቀናጀ መልክ በሚያደርጉት ትግል እንጂ፣ ማንም ፈልጐ እንደስጦታ የሚያቀርብላቸው ነገሮች አይደሉም። ይህም የሚያስገነዝበን ለነፃነታችንና ለመብታችን የተቀናጀና ያልተቋረጠ ትግል እንደሚያስፈልገን ነው።

በአፍሪካ የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብት ከጐለበቱባቸው አገሮች እንደሞሪሽየስ፣ ቦትስዋና እና ደቡብ አፍሪካ ያሉ ሀገሮች በሞዴልነት እየተወሰዱ ብዙ ጊዜ ይጠቀሳሉ። በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ መድብለ ፓርቲ ሐየብዙሃን ፓርቲዎችሐአሉ። ምርጫ በነፃና በሀቅ ይከናወናል። የምርጫ ቦርዶችም የሚታዘቡትን ነገርና ስህተቶችን እንዲታረሙ ያደርጋሉ። የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በነፃነት ተንቀሳቅሰው ደጋፊዎቻቸውን ማሰባሰብና ተወዳድረው የማሸነፍ ዕድል ይኖራቸዋል። በመገናኛ ብዙሃን ላይ ቀርበው ሃሳባቸውን የመግለጽ ሙሉ ነፃነት አላቸው። የሲቪል ሕብረተሰብ እንቅስቃሴ በደንብ የዳበረበት አካባቢ ነው። በአጭር አነጋገር፣ ሕብረተሰቡ ምርጫ ይቀርብለታል። ዲሞክራሲ ደግሞ ያለምርጫ ሊታሰብ አይችልም። ያለምርጫ ዲሞክራሲ አለን ማለት አይቻልም። ያለተቃዋሚ ፓርቲ ዲሞክራሲ አለ ማለትም አይቻልም። ይሄ ደግሞ በቃል ሳይሆን በተግባር መተርጐም ይኖርበታል። እና በእነዚህ እንደሞዴልነት በተወሰዱት አገሮች፣ የሲቪል ማህበረሰቦች ሕብረተሰቡን እያደራጁ ለነፃነቱና ለመብቱ እንዲታገል ያደርጋሉ። ድህነትን ለመቅረፍ፣ ልማትን ለማፋጠን፣ ዲሞክራሲን ለማጐልበት፣ የሕብረተሰቡን ንቃተ ሕሊና ለማዳበር፣ ሰፊ ሚና ይጫወታሉ። እንቅስቃሴያቸው በመመሪያና በአዋጅ አይገደብም። እና በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ የአፍሪካ አገሮች አሉ።

CCRDA

እነዚህ አገሮች ወደኋላ መመለስ አይችሉም። ከእንግዲህ ወደፊት ነው የሚገሰግሱት። ወደኋላ የሚጐትታቸው ምንም ነገር የለም። ሕብረተሰቡ አንድ ወሳኝ ዲሞክራሲያዊ ደረጃ ላይ ደርሷል።



በሌላም በኩል፣ በአፍሪካ፣ በማያቋርጥ የእርስ በርስ ግጭት ተወጥረው የሚኖሩ ሀገሮች አሉ። እንደ አንጐላ፣ ሞዛቢክ፣ ሴራሊዮንና ላይቤሪያን የመሳሰሉ ሀገሮች። እና በእንደነዚህ ያሉ አካባቢዎች ዲሞክራሲም ሆነ መልካም አስተዳደር ወይም ሰብአዊ መብት ጨርሶ ሊታሰብ አይችልም። ከእነዚህም ውጭ ደግሞ አምባገነን መሪዎች ያሏቸው የአፍሪካ አገሮች አሉ። በእነዚህ አካባቢዎች ሰብአዊ መብት ወይም ዲሞክራሲ ወይም መልካም አስተዳደር ጨርሶ ሊታሰብ አይችልም። ለምሳሌ ብንወስድ፣ ዑጋንዳ ውስጥ መድብለ ፓርቲ የሚባል ሥርዓት አይፈቀድም። ሚስተር ሙሰቨኒ የሚመሩት «ናሽናል ሬዚስታንስ ሙቭመንት» ነው ለሕብረተሰቡ ሁሉንም ነገር አስቦ የሚያቀርበው። በመሪዎቹ ፍልስፍና መሠረት መድብለ ፓርቲ ወይም የብዙሃን ፓርቲ ማለት ሕብረተሰቡን የሚከፋፍል ነው። ፓርቲዎች ሲበዙ ሕዝቡ ለአንድ ዓላማ፣ ለአንድ ግብ እንዳይሠራ እንቅፋት ይሆናሉ ብለው ያምናሉ። እና ነፃ ምርጫ የለም፣ የፖለቲካ ፓርቲ የለም፣ ለሕብረተሰቡ የሚቀርቡ የምርጫ ሃሳቦችም የሉም። በእንደዚህ ዓይነት አካባቢዎች የሰብአዊ መብት ድርጅቶች እንዲኖሩ፣ ቢኖሩም እንደልብ እንዲንቀሳቀሱ አይፈቀድም። ስለዚህ የዜጐችን መብት ተከታትሉ፣ ይሄ ተጓደለ ብሉ ለመብታቸው የሚቆም የሰብአዊ መብት ድርጅት አይታይም ማለት ነው። የሲቪል ማህበረሰቦች ወይም የመያዶች ዋና ተግባር፣ የሕብረተሰቡን ፍላጐት፣ የሕብረተሰቡን ችግር፣ የሕብረተሰቡን ብሶት ለመንግሥት አቅርበው፣ ሕዝቡን አደራጅተው፣ ጥያቄው ለመንግሥት ቀርቦ ችግሩ የሚፈታበትን ዘዴ ማስገኘት ስለሆነ፣ በእንደነዚያ ያሉ ሀገሮች ይህንን እንቅስቃሴ ለማድረግ ጨርሶ ቦታ የላቸውም።

CGRDA

ይሁን እንጂ በአንዳንድ የአፍሪካም ሆነ ሌሎች አዳጊ ሀገሮች ሰብአዊ መብቶች ሲረገጡ፣ ዓለም በሙሉ ዝም ብሎ ይመለከታል ማለት አይደለም። በየትኛውም አገር የሚካሄዱ የሰብአዊ መብት ረገጣዎችን እየተከታተሉ፣ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ድርጅቶች አሉ። እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎችና እንደአምነስቲ ኢንተርናሽናል የመሳሰሉት በማንኛውም አገር የሰብአዊ መብት ጉዳይ ገብተው መግለጫ ይሰጣሉ። የተባበሩት መንግሥታት መድረክ ላይ ያጋልጣሉ። ለሰብአዊ መብት ድርጅት ኮሚሽንም ሪፖርት ያቀርባሉ። የሕዝቡን መብት ለሚደፍር መንግሥት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕርዳታ እንዳይሰጥ ይሚገታሉ። ድርጅቶቹ ይህን ሁሉ ግፊት የሚያደርጉት፣ የሰብአዊ መብት ሁኔታ እንዲሻሻል ነው።

አገር ውስጥ ያሉ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ተግባርም መረጃ ሰብስቦ ለመንግሥት ሪፖርት ማቅረብና ሁኔታው እንዲሻሻል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ነው። እኔ የጓደኛዬ ሰብአዊ መብት ሲነካ አይቼ ዝም ካልኩ፣ የእኔ መብት እስካልተነካ ድረስ ግድ የለኝም የምል ከሆንኩ፣ ሰብአዊ መብት ምን እንደሆነ አልተረዳሁም ማለት ነው። የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ሕግ የወጣው በ1948 ዓ.ም. ነው። ይህ ሕግ፣ ፈራሚ በሆኑት የዓለም አገሮች ሁሉ ተፈጻሚ እንዲሆን የተደነገገ ነው። ሁሉም አገሮች ተፈጻሚ እንዲያደርጉ የውዴታ ግዴታ ገብተዋል። በአገራቸው ሕገመንግሥት ሲቀርፁ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎቹን መሠረት ያደርጋሉ። ስለሆነም በአንድ አገር ብሔራዊ ሕገ መንግሥትና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ መካከል ክፍተት ቢኖር፣ ተፈጻሚ የሚሆነው የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌው ነው። እኔ በአገሬ ሕገ መንግሥት ውስጥ አላካተትኩምና ይሄንን መብት አላውቀውም ማለት አይቻልም። ሰብአዊ መብት ዛሬ ዓለም አቀፍ እየሆነ ነው። ስለዚህ ዛሬ አንድ አገር በሩን ዘግቶ፣ ዜጎቹ ላይ የፈለገውን ነገር ማድረግ አይችልም። ጊዜው አልፏል።

የሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች አንዳንድ መርሆችን መከተል ይኖርባቸዋል። በአንድ አካባቢ፣ በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የአካባቢውን ባህል፣ እምነት፣ አመለካከት፣ የኑሮ ዘይቤ ማክበር ይኖርባቸዋል። አይ፣ እነዚህ ኋላቀር ናቸው ብለው የሚያጥላሉ መሆን የለባቸውም። አኗኗራቸው፣ ባህላቸው፣ ኋላቀር ከሆነ፣ አስተምረን ተገቢው የኑሮ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ማበረታታትና ማነቃቃት ነው ያለባቸው።

የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ነው ሪፖርት ማቅረብ ያለባቸው። ትችቶችና ወቀሳዎች በሚቀርቡበትም ጊዜ አሉባልታ መሆን የለባቸውም። በተገቢው ማስረጃ መደገፍ መቻል አለባቸው። የተሟላ መረጃ ይዘው ነው ለማንኛውም ለሚመለከተው መንግሥታዊ አካልም ሆነ፣ ለሌላ ለሚመለከተው ቡድን

CGRDA

ማቅረብ የሚኖርባቸው። እዚህ ላይ ልጠቅስ የምፈልገው፣ ሰብአዊ መብትን የሚጥሱ መንግሥታት ብቻ አለመሆናቸውን ነው። ሰብአዊ መብትን ሕብረተሰብም ይጥሳል። ለምሳሌ የአካል ትልተላ ወይም የሴቶች ልጆች ግርዘት የሚከናወነው በሕብረተሰቡ ነው። ስለዚህ ሕብረተሰቡን ማስተማር ይኖርብናል። ሕብረተሰቡን ማንቃት ይኖርብናል።

በተጨማሪም የሰብአዊ መብትን የሚደፍሩ ወይም የሚገፉ መንግሥታት ወይም ሕብረተሰብ ብቻ ሳይሆኑ ግለሰቦችም ናቸው። ስንቶቻችን ነን የሠራተኞቻችንን መብት የምንገፈው? ሕጉን እያወቅን፣ ከተማ እየኖርን፣ የተማርን የምንባል ሰዎች ከመብት ማክበር አኳያ ምን እያደረግን ነው? ስንቶቻችን ነን በቤታችን ውስጥ የሠራተኞቻችንን መብት የምንገፈው? ለእኛ ጥሩ የሆነውን ለሌላው አያስፈልገውም ልንል አይገባንም። ነፃነት ለሁሉም እኩል አስፈላጊ ነው። እና እነዚህን መርሆች ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል። ምንጊዜም መረጃ በምናቀርብበት ጊዜ፣ ዝም ብሎ በአሉባልታ መሥራት የለብንም። ወይም በመላምት መሥራት የለብንም። እዚህ አካባቢው ድሮ እንዲህ ይደረግ ነበር፣ አሁንም እየተደረገ ነው ልንል አንችልም። ሁኔታዎች ተሻሽለው፣ ተስተካክለው፣ ሊገኙ ይችላሉ። መረጃን በትክክል ማቅረብ ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ትልቅ የሥነ ምግባር መለኪያ ነው።

ለሰብአዊ መብት ስንከራከር ወገናዊ መሆንም የለብንም። አንድ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ሁሉንም ወገኖች በእኩል ዐይን ማየት ይኖርበታል። ይሄ ወዳጄ ነው፣ ይሄ ጠላቴ ክፉ ነው፣ ይሄ የሚሠራው ሥራ ሁሉ መጥፎ ነው። ይሄ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ጥሩ ነው እያልን ከፈረጅን ትክክል አይሆንም። ለምሳሌ በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ፍትሕ ሲዛባ፣ ዳኞች በወገናዊነት ወይም በጉቦ ሲሠሩ ሲታይ፣ ከሕብረተሰቡ ጋራ ሆነን አብረን መታገል አለብን እንጂ፣ እኛ የሰብአዊ መብት ድርጅት ሆነን ምን አገባን? ገለልተኞች ነን ልንል አይገባም። ገለልተኝነትና ወገናዊ አለመሆን ይለያያሉ። ገለልተኝነት አደገኛ ቃል ነው። ማንኛውም ነገር አይመለከተኝም፣ አያገባኝም ማለት ነው። እኔን ሲነካኝ ብቻ ነው የሚመለከተኝ ማለት ነው።

ወገናዊ አለመሆን ግን፣ ሁለቱ ግለሰቦች ለእኔ እኩል ናቸው። ይሄኛው ጥሩ ከሠራ ጥሩ ሰርቷል እላለሁ። ነገ ደግሞ በተገላቢጦሽ ጥሩ የሠራው መጥፎ ከሠራ እተቸዋለሁ። ወዳጄ ነው ብዬ አልተወውም። መጥፎ የሠራው ደግሞ ተሻሽሎ ከተገኘ ጥሩ ሪፖርት እጽፍለታለሁ የሚያሰኝ አቋም ነው። በተለይ የሰብአዊ መብት ድርጅት የምንመራ ወይም በዚህ ዓይነቱ ድርጅት ውስጥ የምንሠራ ሰዎች ይህንን ጠንቅቀን መከተል ይገባናል።

CCRDA

ሌላው መርህ ደግሞ፣ የመንግሥት አሠራር ግልጽ እንዲሆን መደረጉ ብዙ ትግል እንደምናደርግ ሁሉ፣ ልማና ከቤት ይጀምራል ይባላልና እኛም ደግሞ በቤታችን ውስጥ ግልጽ አሠራር፣ ተጠያቂነት ያለው አሠራር መኖር አለበት። ስንቶቻችን መደረጉን ሠራተኞቻችንን በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የምናሳትፈው? ስንቶቻችን ነን ተጠያቂነት ያለብን? ስንቶቻችን ነን በአሠራራችን ግልጽ የሆንን? ታዲያ እኛ ራሳችን ግልጽ ካልሆንን፣ እኛ ራሳችን በቤታችን ተጠያቂነት ከሌለ፣ እኛው ራሳችን እዚያው በኮሚቴ ተደራጅተን እዚያው ተሰባስበን የሃሳብ ፍጭት ተደርጐ፣ በዲሞክራሲ መልክ ብዙ ድምጽ የተገኘበት አሸናፊ ሆኖ ውሳኔ የምናሳልፍ ካልሆነ፣ እንዴት አድርገን በሌሎች ላይ ጣታችንን መቀሰር እንችላለን? ሌላው ላይ ጣት መቀሰር ቀላል ነው። ግልጽ አይደለም፣ ተጠያቂ አይደለም፣ አሠራሩ እንደዚህ ነው፣ እንደዚያ ነው ማለት በጣም ቀላል ነው። እኛስ እንዴት ነን? ብለን ራሳችንን መፈተሽና ግልጽ መሆን አለብን። ግልጽ ካልሆንን ሕብረተሰቡ አንቅሮ ይተፋናል። ግልጽ መሆን አለብን። ምንም የምንፈራው ነገር የለም። ዓላማችን ግልጽ ነው። የአሠራራችን ዘይቤ ግልጽ ነው። ከሕብረተሰቡ ጋር በግልጽ እንገናኛለን። እንደዚህ ዓይነት የሥልጠናና የፓነል ውይይት ላይ እንገናኛለን። ስለሆነም ሃሳባችንንም፣ የአዲት ሪፖርቶቻችንም፣ የእንቅስቃሴ ሪፖርቶቻችንም፣ ለሕብረተሰቡ ግልጽ አድርገን ማቅረብ ይኖርብናል። ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

2.3.4 አጠቃላይ ውይይት

አወያዩ አቶ ደሳለኝ ራህመቶ፣ አዋሳ ውስጥ በተከበረው የመያዶች ቀን የፓነል ውይይት፣ የመጨረሻው ጽሁፍ አቅራቢ የሆኑት አቶ ዩሱፍ ሀሰን በተሰጣቸው ርዕስ ሰፋ ባለ ትንታኔ ላቀረቡት ዝግጅት አመስግነው፣ ተሳታፊዎች ጥያቄዎችና አስተያየቶችን እንዲያቀርቡ ጋበዙ።

ተሳታፊ፡- የሰብአዊ መብትን አስመልክቶ የተናገሩትን ጽሁፍ አቅራቢ አስመልክቼ የማቀርበው ጥያቄ አለኝ። የሰብአዊ መብትን አስመልክቶ እንደችግር በመጨረሻ ላይ ካቀረቡት ነጥብ ላይ ነው የምነሳው። የሰብአዊ መብት ገፀ በረከት አይደለም፣ እንካ ተብሎ የሚሰጥ አይደለም፣ መብት የተፈጥሮ ሕግ ነው ብለዋል። ይህ መሆኑን በኢትዮጵያ ያለው የተለያየ የሕብረተሰብ ክፍል እንዲያውቀው የተደረጉ ሙከራዎች ግን በጣም አናሳ ናቸው። ሕብረተሰቡ መብትን፣ መንግሥት ወይም አንድ የተደራጀ ክፍል እንካ ብሎ ቆርሶ የሰጠው ነው የሚመስለው። ይህ ከሆነ የወንድሜ ድርጅት ይሄንን በማሳወቅ ረገድ የተጫወተው ሚና ምንድነው?

CCRDA

ፓነል አቅራቢ፡- የመሥሪያ ቤቴ መጠሪያ እንደሚያመለክተው እኛ የሰላምና ልማት ድርጅት እንደመሆናችን መጠን፣ ሥልጠናና ትምህርት ከምንሰጥባቸው ዘርፎች መሃከል አንዱና ዋነኛው ምክንያት ሰብአዊ መብት ነው። ትምህርቱ እንዲስፋፋ እንንቀሳቀሳለን። የተሰለፍንበት ዓላማ ትምህርት በመስጠት ላይ ብቻ የተገደበ ነው። የሰብአዊ መብትን መከበር ተከታትለው፣ አስፈላጊም ከሆነ ሪፖርት አቅርበው፣ የአድቮከሲ ሥራ የሚሠሩ ሌሎች ድርጅቶች አሉ። እና የሥራ ክፍፍል ጉዳይ ነው። አንዱ ትምህርት ይሰጣል፣ እዚያ ላይ ያቆማል። ሌላው ደግሞ የግለሰቦችን ወይም የቡድኖችን የሰብአዊ መብት ሁኔታ በአገር ውስጥ እየተከታተለ፣ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትም ሆነ በዓለም አቀፍ ድንጋጌ መሠረት፣ ሰብአዊ መብት ተከበሯል ወይ? ብሎ መረጃ በማሰባሰብ፣ ሪፖርቱን ለአገሪቱ መሪዎች፣ እንዳስፈላጊነቱ፣ ለዳኞች ያቀርባል።

ተሳታፊ፡- የእኔ የመጀመሪያው ጥያቄ የዲሞክራሲንና የመልካም አስተዳደርን ፅንሰ ሃሳብ የሚያስተምር በአገራችን በአብነት የሚጠቀስ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት አለ ወይ? የሚል ነው። ሁለተኛው ጥያቄዬ ደግሞ፣ ቀደም ሲል አንደኛው ጽሁፍ አቅራቢ የሲቪል ማህበረሰቡን የመያዶች አካል አድርገው ነው የጠቀሱት። እና ለምሳሌ እንደ መምህራን ማህበር፣ እንደጋዜጠኞች ማህበር፣ እንደሴቶች ማህበር ያሉ ቢኖሩ፣ ከመንግሥት ተፅዕኖ የራቁ መያዶች ናቸው ማለት ይቻላል ወይ? በተጨባጭ ስናየው እንደዚያ ስለማይመስል ነው።

ፓነል አቅራቢ፡- ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን እንደቅስቀሳና እንደ መደበኛ ትምህርት ካየነው፣ በኢትዮጵያ ለዚህ ተብሎ የተቋቋሙ ድርጅቶች የሉም። ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን በሚመለከት ትምህርት ቤት ከፍቶ መደበኛ ትምህርት ወይም ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል ማለት ከሆነ፣ ይሄ በጣም ጠባብ ይመስለኛል። እኔ ቅድም ስናገር ዲሞክራሲንም፣ መልካም አስተዳደርንም እንደ ሂደት ነው ያየሁትና የገለጽኩት። እኔ ሁሉም መያዶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎችም በየዕለቱ በሚሠሩት ሥራ ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን ያስተምራሉ ብዬ ነው የማስበው። ማህበራዊ ተሳትፎ በሌለበት ሁኔታ፣ ዲሞክራሲም፣ መልካም አስተዳደርም ምኞት ብቻ ነው የሚሆኑት ብያለሁ። ይህ የእኔ እምነት ነው። መያዶችና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በየጊዜው ስለማህበራዊ ተሳትፎ ያስተምራሉ። ስለዚህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መልካም አስተዳደርን

CCRDA

እያስተማሩ ነው:: የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ትምህርት ቤት ተብሎ የተቋቋመ ግን የለም:: ምንጭ በማጐልበት ሥራ የተሰማራን መያዶች፣ ምንጩ የሚጐለብትበትን ምክንያት በመግለጽ፣ ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ ሕብረተሰቡን በፕሮጀክቱ አፈጻጸምና ግምገማ ላይ ካሳተፍነው፣ የሴቶች ሚና ጐልቶ እንዲወጣ ካደረግን፣ እኔ በበኩሌ ተግባራዊ የሆነ የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ትምህርት አለ ብዬ ነው የማምነው:: በጥያቄው ላይ የተጠቀሱት ማህበራትና ድርጅቶች ከመንግሥት ተዕዕኖ ነፃ ናቸው ወይ? ስለተባለው ይህ ራሱ ብዙ የሚያወያይ ነው:: ተዕዕኖ ማለት በቀጥታ ላይሆን ይችላል:: ቢሆንም ተዕዕኖውን መከላከል የአንድ ድርጅት ግዴታ ነው:: መብትን ማረጋገጥ ማለት ነው:: ከሕግ ውጪ የሆነ ተዕዕኖ ሲደረግ፣ ተዕዕኖው ተደረገብኝ ብሎ መከላከል እንደ መብት መታየት ያለበት ነገር ነው::

ተሳታፊ:- የመጣሁት ፕሮጃይኒስት ከተሰኘ መያድ ነው:: ፕሮጃይኒስት የሴቶችን አቅም የሚያጐለብት አገር በቀል ድርጅት ነው:: ስለዲሞክራሲና አስተዳደር አንስተን፣ መያዶች ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን በሚመለከት እስካሁን ድረስ ምን ሠርተዋል? የሚለውን ከመተንተናችን በፊት፣ በመሠረቱ መያዶች እራሳቸው በምን ሁኔታ ላይ ነው ያሉት? የሚለውን ጥያቄ ነው እኔ ማንሳት የምፈልገው:: በመጀመሪያ ነገር፣ እንደ መያድ ስንመዘገብ፣ ከፖለቲካ ነፃ የሆነ፣ ከሃይማኖት ነፃ የሆነ፣ ለትርፍ ያልቆመ ብለን ነው የምንመዘገበው:: ይህም ማለት፣ በራሳችን ላይ ዙሪያችንን ሰንሰለት ጠምጥመን ነው ከፍትሕ ሚኒስቴር ጋር የምንፈራረመው ማለት ነው:: ከፖለቲካ ነፃ የሆነ ማለት ምንድነው? ስለዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር መናገር የማይችል ማለት ነው:: ምክንያቱም ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር በመሠረቱ የፖለቲካ ዕንሰ ሃሳቦች ናቸው:: መልካም አስተዳደር ራስን በራስ የማስተዳደር ዕንሰ ሃሳብ ነው:: እና ከፖለቲካ ነፃ ነን ካልን፣ ራሳችን ሸብበናል ማለት ነው:: እንግዲህ በዚህ ላይ ተመስርተን ፍትሕ ሚኒስቴር ጋር ስንፈራረም፣ ራሳችንን አስረን በተመዘገብንበት መብት ዙሪያ እናስተምር ብንልና ይህም ጥያቄ ቢያስነሳብን፣ ተዕዕኖ ደረሰብን ልንል ነው ማለት ነው:: የራሴ ድርጅትጭምር የተመዘገበው በዚህ ሁኔታ ነው:: እና ይህ እርስ በራሱ የሚጋጭ ስለሆነ ግልጽ ማድረግ ያለብን ይመስለኛል:: አመሰግናለሁ::

CCRDA



ፓነል አቅራቢ፡- ይህ ጥያቄ ሁላችንንም የሚመለከት ነው። ጠያቂው መንግሥታዊ ያልሆንን ድርጅቶች ከፖለቲካ ነፃ እንደሆንን ቃል የገባንበትና ራሳችን በራሳችን የተበተብንበት ነው ያሉት፣ ትንሽ ግልጽ የሆነ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ይመስለኛል። ፖለቲካ አናራምድም ሲባል፣ የፖለቲካ ትምህርት አንሰጥም ማለት አይደለም። ሁለቱ መሀል ልዩነት እንዳለ መረዳት ያስፈልገናል። ሰብአዊ መብት፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶችንና ሌሎች መብቶችንም ብንወስድ፣ ፖለቲካዊ ባህሪ አላቸው። እሱን አታስተምሩ የሚለን የለም። ትምህርቱን፣ ግንዛቤውን በማዳበር ረገድ፣ የሕብረተሰቡን ንቃተ ሕሊና ከፍ በማድረግ ረገድ ገደብ ሊኖር አይገባም። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችውና ግዴታ ያደረገችው የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ አካል እስከሆነ ድረስ፣ እያንዳንዱን ዜጋ መብትህ፣ ግዴታህ ይሄንን ይመስላል ብሎ ማስተማር ግዴታችን ነው። እና እዛ ላይ ጠብ የለም፤ ግጭት የለም። ምዝገባ ላይ ከፖለቲካ ነፃ ነን ማለት፣ ለፖለቲካ ሥልጣን ትግል አናደርግም ማለታችን ነው። የፖለቲካ ፕሮግራም የለንም ማለታችን ነው። መንግሥታዊ አይደለንም ማለታችን ነው። ፖለቲካ አናርምድም ስንል፣ ለፖለቲካ ሥልጣን ታጥቀን የተነሳን አለመሆናችንንና ዓላማችን በምንተዳደረው ደንብ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው። አለዚያማ የተምታታ ዓላማ ይኖረናል።

በሌላም በኩል የፖለቲካ ድርጅት መሆን ክልክልነት የለውም። የፖለቲካ ድርጅት መሆን የሚፈልግ በምርጫ ቦርድ ተመዝግቦ፣ የፖለቲካ ፕሮግራም ቀርጾ፣ ደጋፊ ፈልጐ፣ ለፖለቲካ ሥልጣን በየአራት ዓመት ወይም በየአምስት ዓመት ተወዳድሮ፣ ሥልጣን ከያዘው መንግሥት ላይ በድምጽ ብልጫ አሸንፎ

CGRDA

ሥልጣን መረከብ ይችላል። ግልጽ መሆን ያለበት፣ መንግሥታዊ ያልሆንን ድርጅቶች ስንመዘገብ በዓላማችን ለሥልጣን ታጥቀን የተነሳን አለመሆናችንን ለማስገንዘብ፣ ከፖለቲካ ነፃ ነን እንላለን። እና እኛ ልክ እንደገባን ከዓላማችን አንፃር ተርጉመን እንቀበለው።

ሌላ ፓነል አቅራቢ፡- እንግዲህ እኔም እዚያው ላይ ነው አስተያየት የምሰጠው። መቼም ቀደም ሲል መልስ ሰጭው እንዳሉት ቢሆን አይከፋኝም። እኔ ደግሞ አንድ እምነት አለኝ። ሕግን ተርጉሜ መረዳት የለብኝም። ምክንያቱም ሕግ የመተርጐም ሥልጣን የእኔ አይደለም። የፖለቲካ ፓርቲ አለመሆን ነው ከተባለ፣ እዚያው ሕጉ ላይ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኜ አልሠራም ብለህ ፈርም ማለት ይቻላል። ከፖለቲካ ነፃ ነኝ በል ማለት ግን ለእኔ በጣም ግልጽ ያልሆነ ነው። እና ቀደም ሲል የተሰጠው መልስ አያረካኝም። ምክንያቱም ዲሞክራሲ ነው። ዲሞክራሲ ደግሞ የሃሳብ ልዩነትን መቀበል ነው። ስለዚህ ሕግ ሲጻፍ፣ ሕግ የማላውቀው ተራው ሰው እንዲገባኝ ተደርጐ ነው መጻፍ ያለበት።

ተሳታፊ፡- በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በተመለከተ ምን ዓይነት የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ አለ? ፖሊሲው ምን ይመስላል? የሕጉ አንቀጾችስ ምን ይመስላሉ?

ፓነል አቅራቢ፡- ለመያዶች የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ አለወይ? ለተባለው፣ ይህንን ከመንግሥት መጠበቅ ብቻ አይበቃም። ሕብረተሰቡም፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር ሚና አላቸው ብዬ ነው የምገምተው። ሆኖም የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ሲፈጠርላቸው መያዶች የበለጠ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። መያዶች፣ እንደዚህ ባሉ መድረኮችና በሌሎችም አመቺ መንገዶች የመንግሥት አካላት የሚሳተፉባቸው ውይይቶችን የሚያካሂዱት የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

ሌላ ፓነል አቅራቢ፡- የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ስለተነሳ፣ ትንሽ የምለው ነገር አለኝ። የተመቻቸ የሥራ ሁኔታ ከአገር አገር፣ ከዲሞክራሲና ከሰብአዊ መብት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። የአገሪቱ የሰብአዊ መብትና የዲሞክራሲያዊ መብት እድገት ደረጃ ከፍ ካለ፣ የተመቻቸ የሥራ ሁኔታውም ጥሩ ይሆናል። በአንፃሩ ደግሞ የሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብት እድገቱ ደካማ ከሆነ፣ የተመቻቸ የሥራ ሁኔታው ጨርሶ የለም። አንዳንድ መንግሥታት እኛው ብቻ ነን ሁሉንም ችግር መፍታት ያለብን ከሚል ግንዛቤ ይነሳሉ። ይህ ብዙ ተሞክሮአል። የዓለም ባንክ፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ምዕራብ አገሮችም፣ ከመንግሥታት ጋር ሙሉ በሙሉ ለመሥራት

CCRDA

ሞክረው፣ ውጤቱ አመርቂ ሳይሆን ቀርቷል። አሁን ያንን ለማሻሻል በማሰብ፣ የተወሰኑ ግዴታዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየሞከሩ ነው። የሲቪል ማህበረሰቡ መረጃ አለው፣ አቅሙ አለው፣ ልምዱም አለው። ቢሆንም ለመንግሥት እገዛ አድርጉ የሚሠራ እንጂ መንግሥትን ተክቶ የሚሠራ አይደለም። እና መንግሥትም ይህንን ግንዛቤ ከወሰደ፣ አጋር ማግኘት ይጠ ቅማል እንጂ አይጐዳም። አንድ ሰው ላግዝህ ሲልህ አንተ አታግዘኝም፣ እኔ ነኝ ሁሉን ነገር የምሠራ ማለት አይበጅህም። ለምን? አንድ ሰው አንድ ነው። እና አሁን አጋርነቱ የሲቪል ማህበረሰቡን፣ መንግሥትንና የግል ሴክተሩንም ጨምሯል። የግል ሴክተሩ ትልቅ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሚና አለው። እና ፖሊሲዎች ሲቀረፁ፣ እርዳታዎች ሲጠየቁ፣ መንግሥታት የሲቪል ማህበረሰቡንና የግል ሴክተሩን እንዲያማክሩ እየተጠየቀ ነው። እንደ አውሮፓ አንድነት ያሉት፣ የገንዘብ እርዳታ ለመስጠት ሲያስቡ፣ የሲቪል ማህበረሰቡ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አለው? ምን ብሏል? ምን ትችት አለው? ምን ድጋፍ አለው? ብለው ጠይቀው ነው እንጂ፣ እንደዚሁ መንግሥት የእርዳታ ጥያቄውን ስላቀረበው ብቻ አይሰጡም። አመሰግናለሁ።

አወያዩ አቶ ደሳለኝ ራህመቶ የፓነል አቅራቢዎቹንና ተሳታፊዎቹን አመሰግነው፣ የበኩላቸውን የማጠቃለያ አስተያየት ሰጥተዋል።

በመጀመሪያ ተሳታፊዎችን በራሴ ስምና በአደራጆቹ ስም ሆኜ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። ያሳያችሁት ቅን ፍላጐት የሚያበረታታ ነው። ያነሳችኋቸው ጥያቄዎችም አንገብጋቢዎች ናቸው። ተናጋሪዎቹ ስላቀረቡት ውይይትና ስለመልሳቸውም በጣም ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ። የተነሱት ጥያቄዎች ሁሉ በጣም ጠቃሚዎች ናቸው። የተሰጡትም መልሶች እንዲሁ። እና በዛሬው ውይይት ሙሉ በሙሉ መልስ አግኝተው ከዛሬ ወዲህ አንመለስባቸውም ማለት አይደለም። እኔ እንደሚመስለኝ በሌላ ጊዜ፣ በሌላ መድረክ እንደገና ተነስተው ሰፊ ውይይት የሚካሄድባቸው ናቸው። ለዛሬው ግን አንዳንድ ጥያቄዎችና አንዳንድ ሃሳቦች ተፈንጥቀዋል። አንዳንድ ጥያቄዎች ቀደም ሲል ከተካሄዱት የፓነል ውይይት ጽሁፎች ጋር ብቻ ግንኙነት ስላላቸው፣ ወይም ተደጋጋሚ በመሆናቸው ቀጥተኛ መልስ አልተሰጠባቸው ይሆናል። ቢሆንም ተወያይተንባቸዋል። በየግላችንም ሆነ በየድርጅቶቻችን እነኚህን ጥያቄዎችና ሃሳቦች ማብላላት የራሳችን ሩጫ ነው። በጣም እናመሰግናችኋለን።

የፓነል ውይይቱ 7:00 ሰዓት ላይ ተጠናቀቀ። በዚህም አዋሳ ውስጥ የተከበረው «መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንሜ አከባበር ተፈጸመ።

//----------//

CCRDA

ከከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ንግግሮችና ከፓነል ውይይቶች ነጥረው የወጡ አስተያየቶች

- የሚፈለገውን የባህሪ ለውጥ ለማምጣት ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር መርሐግብች ላየ ቅንጅታዊ አሠራር ተግባራዊ ይሁን፣'
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን በየክልሎቹ በዙር እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ለመያዶች እንቅስቃሴ የሚፈጠረውን አመቺ የሥራ ሁኔታ ይበልጥ ለማሻሻል ይረዳል፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቀን በክልል ደረጃ ማዘጋጀት፣ ተጨባጭና ፍሬያማ የሆኑ የልምድ ልውውጦችን በማካሄድ፣ ሚዛናዊ የሆነ ክልላዊ ልማትን ዕውን ለማድረግ ያስችላል፣
- መያዶች የልማቱ ባለቤት የሆነው ሕዝብና የመንግሥት የልማት አጋሮች ናቸው፣
- በርካታ የልማት ችግሮችን ለማቃለል፣ በርካታ የልማተ አጋሮች ያስፈልጋሉ:: ስለሆነም፣ እንደሌሎች ሀገሮች ሁሉ በኢትዩጵያም የመያዶች ቁጥር እንዲበዛ፣ በመያዶች አመዘጋገብ የተቀላጠፈ አሠራር እንዲኖርና የኘሮጀክት ውል በአጭር ጊዜ እንዲፈጸም ከመንግሥት ልዩ ትኩረት ይሰጥ፣
- ዘላቂ ልማትን ለማስፈን ይቻል ዘንድ፣ መንግሥት ለመያዶች የልማት ገቢ ማስገኛ ዝግጅቶች ፈቃድ በመስጠት እገዛ ያድርግ፣

CCRDA

- ግልጽና ውጤታማ የሆነ የልማት ስልት ለመንደፍ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶ መካከል ጠንካሪ የሥራ ትብብርና አጋርነ ያስፈልጋል፣
- የሕብረተሰብ ተሳትፎ ሲባል፣ አገሪቱ በምታካሂደ የልማት አቅጣጫ፣ የፖሊሲ ይዘት፣ ቅድሚ የሚሰጣቸው ተግባሮችን በመለየትና በሀብት ድልድል የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሕብረተሰቡን ማሳተፍን ይጨምራል፣
- መያዶች ለሥነ ምግባር መመሪያቸው ተገዢ በመሆን ተጠያቂነትንና ግልጽነትን በተግባር በማሳየት አርአ መሆን አለባቸው፣
- ዲሞክራሲ በሌለበት መልካም አስተደደር የለም: ሁለቱ በሌሉበት ደግሞ እውነተኛና ዘላቂ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት የለም፣
- መረጃን በትክክል ማቅረብ፣ ለሰብአዊ መብ ተሟጋቾች ትልቁ የሥነ ምግባር መለኪያ ነው፣
- የሕግ የበላይነተ ከሌለ ሰላም ሊኖር አይችልም:: ፍት የሰላምና የልማት መሠረት ነው፣
- የረመጅቸ የሥራ ሁኔታ ሲፈጠርላቸው መያዶች የበለጠ የልማት አስተዋፅአ ያደርጋሉ፣

CCRDA

- የሥራ ድግግሞሽንና እንደልብ የማይገኘውን ሀብት ብክነት ለማስወገድ፣ የተቀናጀ አሠራር ይስፈን፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ተሳትፏዊ የዕቅድ አወጣጥ ሂደትን በማራመድና ተሳትፏዊ የልማት አሠራርን በማመቻቸት ረገድ ወሳኝ ሚና አላቸው፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር መብዛት ስርጭታቸውን ለማስፋት ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትልቁ ራዕይ ድህነትን መቀነስና ልማትን ማስፈን ነው፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት ሂደት ወሳኝ ሚናና አስተዋፅኦ አላቸው፣
- የድህነት ቅነሳ ያለሕብረተሰብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ዕውን ሊሆን አይችልም::

CCRDA